ኒኮሎ ማኪያቬሊ

# ልዑሉ



THE

# PRINCE

ጆርጅ ቡል ወደ እንግሊዘኛ እንደተረጎመው
አና ፍራንክ ወደ አማርኛ እንደመለሰችው

## ኒኮሎ ማኪያቬሊ

# ልኡሉ

# THE PRINCE

<The prince is the bible of real politics>

ጆርጅ ቡል ወደ እንግሊዝኛ እንደተረጎመው

አና ፍራንክ ወደ አማርኛ እንደመለሰችው

2005ዓ.ም

© የተርጓሚዋ መብት በህግ የተጠበቀ ነው

አንደኛ እትም - ታህሳስ 2005ዓ.ም

NICCOLO MACHIAVELLI
THE PRINCE

Translated with an introduction by GEORGE BULL

Copyright © George Bull

First published 1961

Reprinted 1963, 1964, 1966, 1967, 1968, 1970, 1971 (twice), 1972, 1973, 1974
Reprinted with revisions 1975, 1981
Reprinted 1976, 1977 (twice), 1978, 1979 (twice), 1980 (twice), 1982, 1983 (twice), 1984, 1985, 1986

Made and printed in Great Britain
By Richard Clay (The Chaucer press) Ltd,
Bungay. Suffolk
Set in Monotype Centaur

በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱት የቀን አቆጣጠሮች በሙሉ እንደ አውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ነው

# ማውጫ


መግቢያ ........................................ 5

ከኒኮሎ' ማካቬሊ

ለግርማዊ ሎሬንሶ ደ' ሜዴቺ የተጻፈ ደብዳቤ .................... 23

የግዛቶች አይነትና አመሠራረታቸው .................... 25

- የውርስ ግዛቶች .................... 26
- ቅይጥ የመሳፍንት ግዛቶች .................... 27
- በራሳቸው ህግጋት የሚመሩ ግዛቶች .................... 44
- በገዛ ራስ ጦርና በገዛ ራስ ጀግንነት የሚመሠረቱ ግዛቶች....... 46
- በእድልና በውጭ ኃይሎች/በሌሎች እርዳታ የሚመሰረቱ ግዛቶች...... 51
- በትረ ስልጣንን በወንጀል መጨበጥ .................... 62

ህገ መንግስታዊ አገዛዞች .................... 69

- የቤተ-ክህነት አገዛዞች .................... 74

ወታደራዊ ተቋማትና ቅጥረኛ ወታደሮች .................... 79

- የእርዳታ ጦርና ሌሎች ወታደራዊ አመሰራረቶች .................... 86
- አንድ ልኡል ሠራዊቱን ማዋቀር ያለበት እንዴት ነው?..... 91
- ሰዎች፣ የሚወደሱባቸውና የሚወገዙባቸው ባህሪያት .................... 94
- ለጋስነትና ንፉግነት .................... 96
- ጭካኔና ርህራሄ፡ ከመወደድና ከመፈራት የትኛው ይበጃል?... 100
- ልኡላን ቃላቸውን ማክበር ያለባቸው በምን መልኩ ነው?...... 105

የህዝብ ጥላቻንና ንቀትን የማስወገድ ጠቀሜታ.............. 109
- የተለያዩ የአገዛዝ ስልቶች.................................... 124
- አንድ ልኡል ከበሬታን መጎናጸፍ የሚችለው እንዴት ነው?... 129
- የልኡሉ ባለስልጣናት.......................................... 134
- ከከንቱ ውዳሴና አሉባልታ እራስን መከላከል............... 136
- ስለምን የጣሊያን ልኡላን ግዛታቸውን ተነጠቁ?............ 139
- እድል በሰዎች ህይወት ላይ የላት የበላይነት እስከምን ድረስ ነው? እድልን መቃረን የምንችለው እንዴት ነው?............ 142
- ጣሊያንን ከአረመኔዎች ነጻ የማውጣት ተማጽኖ............ 146

# መግቢያ

በዘልማዳዊው ንግርት ‹ልኡሉ› ከእርኩሳዊ መንፈስ የፈለቀ መጽሐፍ ነው፡፡ በማኪያቬሊ ዙሪያ የተንሰራፋው ውጉዝ አፈ ታሪክ የመጽሐፉ የመጀመሪያው የእንግሊዘኛ ትርጉም ከመታተሙ ከ1640ዓ.ም ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ ማኪያቬሊ ለኤልሳቤጥያውያን ድራማ ጸሐፊዎች አስከፊ ሁነቶችን መግለፅ የሚያስችላቸው አንድ የተለመደና ጠቃሚ ቃል አበርክቶላቸው ነበር፡፡ ያኔ ሰይጣን ማለት ኒኮሎ ማኪያቬሊ ማለት ሆኖ ነበር (ምንም እንኳ ይህ የሰይጣናዊነት ቅጽል ስም የማኪያቬሊ ርኩስ ዝና ሀገራቱን ከማዳረሱ ቀድሞ የነበረ ቢሆንም)፡፡ እናም ሰይጣን - ማኪያቬላዊ፤ ማኪያቬሊን ሰይጣናዊ ማለት መሆኑ ተቀባይነት አገኘ፡፡

የእንግሊዙ ካርዲናል (ሊቀ-ጳጳስ) ፖል የማኪያቬሊ ቀደምትና ቀንደኛ ነቃፊዎች መካከል አንዱ ሲሆኑ የማኪያቬሊን እርኩስ መንፈስ ነቅሶ በማውጣት የመጀመሪያው እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ሆኖም በማኪያቬሊ እርኩስ የልኡላን አማካሪነት ስለፈለቁ ሀጥያቶች የሚነዙ አፈ ታሪኮች መደመጥ የጀመሩት በካትሪን ደ ሜዲቺ አገዛዝ ከተማረሩ ፈረንሳውያን ነበር፡፡

ከጅምሩ ኒኮሎ ማኪያቬሊ የሀይማኖታዊ ሰጣ ገባዎች ግምባር ቀደም ሰለባ ነበር፡፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ቀኖናዎች ዘልፎ ባያውቅም ለካህናቱ አሰራር የመረረ ተቃውሞ ያንጸባርቅ ነበር፡፡ በጽጽስና ሥርዓቱ ላይ የሚያወርዳቸው የሰላ ትችቶች የፀረ-ተሃድሶ አቋም ያላቸው ካቶሊኮች የማይታገሱት አይነት ነበር፡፡ ለፕሮቴስታንቶቹ ደግሞ ማኪያቬሊ የካቶሊክ ንጉሶች የሰይጣናዊነት አስጠኚ ነበር፡፡ እንዲያውም በቅዱስ በርተሎሜዎስ ዕለት ለተፈፀመው ጅምላ ዕልቂት ተጠያቂ ያደርጉታል። ከዚህ አኳያ የማኪያቬሊ አፈታሪካዊ ዝና ሰውዬውንና ስራውን ቢያደበዝዙት የሚገርም አይሆንም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እዚህ ‹ልኡሉ› የተሰኘው መጽሐፍ ላይ የሰፈሩ አንዳንድ አመለካከቶች ከጠቅላላ ዐውዱ ውጪ በሆነ መልኩ በቁንፅል እየተጠቀሱ ጸሀፊውን ያስኮንኑት ነበር፡፡ በርግጥ በዚህ መጽሐፍ ላይ የተካሄዱ መጠነ ሰፊ ውግዘቶች የሰውዬውን ትክክለኛ ማንነት ግልብ በሆነ መንገድ እንዲዛባ በር ከፍተዋል፡፡

“ልኡሉ” የተሰኘው መጽሐፍ መጀመሪያ አካባቢ ነገሬ ያለው ማንም አልነበረም። እውነት ለመናገር መጽሐፉ የነበረው ተቀባይነት ‘ተወዳጅ’ ወይም በ‘ተቃራኒው’ ሊባል የሚችል አልነበረም፡፡ በስፋት ታትሞ እስኪሰራጭ ድረስ እንደተለመደው ከታዳሚ ዘንድ የደረሰው በዝግታ ነበር፡፡ ከዚያም ሀይማኖት ድምጽዋን አሰምታ የውግዘትና የማጥላላቱን በር ከፈተች፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ በበጎ ጎኑ የተነሳሱ፣ ግን እኛ እንደምናምነው የተሳሳቱ ደጋፊዎች ‘መጽሐፉ ምስጢራዊ ትርጉም አለው’ በሚል መላምት መጽሐፉን ለመታደግ ብዙ ጥረቶች አደረጉ፡፡ ከዛም ነቀፋው ወደ ጸሐፊው (ማኪያቬሊ) ዞረ። ይሄም ለጸሐፊው የጥርጣሬና የክፋት ምናባዊ ምስልን ፈጠረበት፡፡

"ልኡሉ" የተሰኘው መጽሐፍ በአንድ በኩል ሲወርድ ሲዋረድ በቆየው ንግርት በመበረዙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በብዙሀኑ ዘንድ ከመነበብ ይልቅ በብዙ ቦታዎች ላይ የሚጠቀስ አይነት መጽሐፍ በመሆኑ አሁንም ድረስ ዝናው የጎደፈ ነው:: የዚህ ምክንያቱ ደግሞ መጽሐፉ ልክ እንደ ዘጋቢ ጽሑፍ ሁሉ ለዘመኑ የተፃፈ ጠንካራ ስሜት ገላጭ በራሪ ጽሑፍ ከመባል ይልቅ፣ ለብቻው የተነጠለ የፖለቲካ ፍልስፍና ተደርጎ መወሰዱ ነው:: በርግጥ ከጋዜጣዊ ዘገባ ይበልጣል፤ ግን እንደ ጋዜጣ ጽሑፍ ሁሉ መጽሐፉን ለመረዳት የተጻፈበትን ዘመን ነባራዊ ሁናቴ ማጣቀስ ያስፈልጋል:: በመጽሐፉ ዙሪያ ከሚጠረቁ አፈ ታሪኮች ባሻገር ጣሊያን በማኪያቬሊ ዘመን የነበረችበትን ሁናቴና መጽሐፉ በጥድፊያ የተፃፈበትን መንፈስና ድባብ ከግንዛቤ መክተት ያስፈልጋል::

የሆነው ሆኖ ይህ መጽሐፍ ከግላዊና ሀገራዊ ሰቆቃ የመነጨ፣ ግን በተስፈኝነት መንፈስ የታጀበ የስቃይ ተረፈ ምርት ነው:: በማኪያቬሊ ዘመን ጣሊያን ጭካኔ በተሞላበት በማያቋርጥ ጦርነት ትታመስ ነበር:: የጣሊያን ግዛቶች (በማኪያቬሊና በብዙዎች አመለካከት ምክንያት፣ በገዢዎቿም ደካማነት የተነሳ) ተቀናቃኝ ፍላጎት ባላቸው የውጭ ሀይሎች ታምሰው፣ ተጨፍልቀው ነበር::

በማኪያቬሊ የልጅነት ዘመን ሀገሪቱ አንጻራዊ መረጋጋት ይታይባት ነበር:: በ1469 ማኪያቬሊ በተወለደበት አመት፣ ሎሬንሶ ደ ሜዴቺ የፍሎረንስ ሀገረ ገዥ ሆኖ ተሾመ:: የዲፕሎማሲ ችሎታና አስተውሎት የተላበሰ ስለነበር ሀገሪቱ በበርካታ ግዛቶች ብትከፋፈልም ሰፋ ያለ ይዞታ በነበራቸው

አምስት ሀያላን መንግሥታት ቁጥጥር ስር በሰላም እንድትተዳደር ለማድረግ አስችሏት ነበር፡፡ አምስቱ ሀያላን ግዛቶች ፍሎሬንስ፣ ቬኒስ፣ ሚላን፣ ኔፕልስና የጳጳሱ ግዛት ነበሩ፡፡ በ1492 ሎሬንሶ አለፈና በ1494፣ የጣሊያን ቀውስ ጅማሮ እንደሆነ በሚታመንበት አመት፣ ንጉስ ቻርልስ 8ተኛ በኔፕልስ ላይ የዙፋን ይገባኛል ጥያቄ አንስቶ ሰራዊቱን እየመራ ወደ ጣሊያን ምድር ገባ፡፡ የርሱ ተተኪ የነበረው ሉዊ 12ተኛ ደግሞ ኔፕልስን ከአራጎኑ ፈርዲናንድ ጋር ለመቀራመት በማሰብ የስፔይንን ሀይል አስከተለ፡፡ በጥቂት አመታት ውስጥ ስፔይን የጣሊያንን ደቡባዊ ክፍል ተቆጣጠረች፡፡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ሩብ አመት ላይ የጣሊያን ግዛቶች አንዱን ገዢ በሌላው ላይ በማነሳሳት ጠላቶቻቸውን ለማስወጣት ቢሞክሩም በመካከላቸው ብርቱ ህብረት መፍጠር አልተቻላቸውም፡፡ በ1527 ማኪያቬሊ በሞተበት አመት፣ ጣሊያን ሙሉ ለሙሉ ተዳክማ ሮም በነጻ አውጪ ነን ባይ እብሪተኛ ወታደሮች ወደመች፡፡ በመጨረሻም ስፔይን ሚላንን፣ ኔፕልስና ሲሲሊን ተቆጣጥራ፣ የፍሎሬንስ የበላይ ጠባቂ ሆና፣ መላውን ፔኒንሱላ ከነጦር ቀጠናዎቹ ለመቆጣጠር በቃች፡፡

በወቅቱ ኒኮሎ ማኪያቬሊ በሀገራቸው ጣሊያን ደካማነትና ውርደት የሀፍረት ማቅ ከተከናነቡ ዜጎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ሆኖም በጣሊያንና አረመኔ በሚላቸው በውጪ ሀይሎች መካከል ያለውን ልዩነት ቢያውቅም ለሀገሩ ያለው አመለካከት ከብሄርተኝነት ይልቅ በዘረኝነት ላይ የተመረኮዘ ነበር፡፡ ቬኒስንና ኔፕልስን በዋናነት እንደ ጣሊያን ግዛቶች አድርጎ አያስብም ነበር፡፡ ለማኪያቬሊ መላዋ ሀገሪቱ ፍሎሬንስ ብቻ ነች፡፡ የተቀሩት

ግዛቶች ሀገር ወዳድነቱን መጠቀሚያ አጀንዳዎች ነበሩ፡፡ ኒኮሎ ማኪያቬሊ ማንኛውም አይነት አስተዳድር ቢከሰት ያለምንም ወለም ዘለም በጽናት ለማገልገል የሞከረው፣ ሲያገለግልም የኖረው ፍሎረንስን ነው፡፡ ሆኖም አለመታደል ሆነና ፍሎረንስ እንደ ነጻ ግዛት የነበራት ታላቅነት ማኪያቬሊ ለአቅመ አዳም በደረሰ ጊዜ አክትሞለት ነበር፡፡

በግዛቲቱ ላይ የተካሄዱት ወረራዎች ፍሎረንስን ከመጀመሪያ መደብ የጣሊያን ሀያል ግዛትነት በስፔይን ቁጥጥር ወደ ምትመራ ሁለተኛ መደብ ግዛትነት አውርዷት ነበር፡፡ ፈረንሳዮች በ1494 ወደ ፍሎረንስ ሲመጡ የሎሬንሶ ልጅ ፒዬሮ ደ ሜዴቺ በፍርሃት በርግጎ ከቻርልስ ጋር ለመደራደር በወጣበት ከዳተኛ ተብሎ ተፈረጀ፡፡ ፒዬሮ ካገር ከወጣ በኋላ ቻርልስ ወደ ሮም ሲያመራ በፍሎረንስ ህዝባዊ አስተዳደር ተመሰረተ፡፡ ሳቮናሮላ እንደ መለኮታዊ በቀል አድርጎ ቻርልስን ከፍተኛ አቀባበል አደረገለት፡፡ መጀመሪያ ላይ በርሱ መሪነት ተጽዕኖ ለንግድና ልምድ ለመቅሰም በሚል እሳቤ ሪፐብሊኩ ከፈረንሳይ ጋር ወዳጅነት የመፍጠር አዳጋች ፖሊሲን ይከተል ነበር፡፡ ሆኖም ይህ ፖሊሲ ከግምት የሚገባ ፋይዳ አላተረፈም፡፡ ፈረንሳዮች በፍሎረንስ ትገዛ የነበረችውን ፒሳ ነጻ እንድትወጣ በመርዳት የፍሎረንሶችን የማያቋርጥ ፒሳን መልሶ የመቆጣጠር ጥማት ፈጠሩ፡፡ ቡተዘዋዋሪ መልኩም የማኪያቬሊን ጠንካራ ሚሊሺያ የመቋቋም ጥማት አሰረጹ፡፡ የፍሎረንስ ሪፐብሊክ መጀመሪያ በሳቮናሮላ በኋላም በማኪያቬሊ ወዳጅ በሶደሪኒ ቁጥጥር ስር ነበር፡፡ ከዛም የሜዴቺ የቀድሞ አገዛዝ በቅዱስ ሊግ ጦር አስገዳጅነት ድጋሚ ነገሰ፡፡ በ1527 የሮም መዘረፍ ህዝቡ

በጳጳሱ በክሌመንት መንግሥት እንደራሴ ላይ በአመፅ ሲነሳና ሪፐብሊኩ በድጋሚ ግዛቲቱን ሲቆጣጠር ለአጭር ጊዜ እፎይታ ተገኝቶ ነበር። ሆኖም ከሦስት ዓመታት በኋላ ንጉሰ ነገስት ቻርልስ 5ተኛ በማያዳግም መልኩ ፍሎሬንስን በሜዴቺዎች መዳፍ ውስጥ አስገባት፡፡ ይሄም የሆነው ለሁለት ዓመታት ወደ መበስበስ ዘቅጠው ከቆዩ በኋላ ነው፡፡

ማኪያቬሊ በጊዜው ስለነበረ የፖለቲካ ህይወት በጥልቀትና በጽናት ይቆረቆር ነበር፡፡ አባቱ የፍሎሬንስ ጠበቃ ሲሆን ያደገው ፍሎሬንስ በሎሬንሶ ትመራ በነበረበት ወርቃማ ዘመን ነበር፡፡ ፈረንሳይ ያለምንም ተቃውሞ ወደ ከተማው ስትገባ ማኪያቬሊ በማንም ዘንድ የማይታወቅ ገና ወጣት ነበር። የዘመኑ ጸሐፍትም ገና ልብ አላሉትም ነበር። ርግጥ በወቅቱ እሱም የራሱ የሆነ የፃፈው መጽሐፍ አልነበረውም።

ለማንኛውም በአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የተከሰቱ ትእይንቶች በማኪያቬሊ አእምሮ ውስጥ ጥልቅና በቀላሉ የማይፋቅ ጉልህ አሻራ ትተው አልፈዋል፡፡ የሜዴቺን ውድመት አይቷል፣ በህዝባዊ ፍቃድ ላይ ያልተመሰረተ አገዛዝን ውጥረቶች ታዝቧል፣ በሳቮናሮላ የነውጥ አመራር በፍሎሬንስ አንጃዎች መካከል የነበረውን ሽኩቻ ተመልክቷል፡፡ እናም በውስጣዊ አንድነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ አስተዳደርን አስፈላጊነት ተረድቷል፡፡

ብዙም ሳይቆይ ኒኮሎ ማኪያቬሊ ፖለቲካዊ ችግሮችን በቅርብ ርቀት የመታገል እድሉን አገኘ፡፡ ፍሎሬንሶች ወረቀት ለያዙ ሰዎች የአስተዳደር ቦታን የመስጠት ልምድ ነበራቸው፡፡

ሆኖም ማኪያቬሊ እስከ ህይወቱ ፍፃሜ በገንዘብ ረገድ የነበረው የማያቋርጥ ጭንቀት እንደሚመሰክረው ክፍያቸው ጠብ የማይል እጅግ አነስተኛ እንደነበረ ነው፡፡ በ1498ዓ.ም በ30 አመቱ አካባቢ ማኪያቬሊ የሪፐብሊኩ ዋና ጸሐፊና ሁለተኛ ቻንስለር ተደርጎ ተመረጠ፡፡ የስራው ሀላፊነት የመስተዳድሩን አስፈጻሚ ኮሚቴ ማገልገል ሲሆን የሱ ሥራ በዋናነት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን የሚመለከት ነበር፡፡ በርካታ አስተዳደራዊና ወታደራዊ ተልእኮዎችም ላይ ተሳትፏል። ማኪያቬሊ በዚህ ስራው ሪፐብሊኩ እስከ ወደቀበት 1512 እ.ኤ.አ ድረስ ለ14 አመታት ቆይቷል፡፡

በተለይም በሶደሪኒ ዘንድ ተወዳጅ ነበር - ምንም እንኳን ባላንጣዎች ቢያበዛበትም - ከሶደሪኒ በርካታ ተልእኮዎች ይሰጡት ነበር፡፡ በወቅቱ ሪፐብሊኩ ከሌሎች የጣሊያን ግዛቶችና ስፔይንና ፈረንሳይን ከመሳሰሉ ታላላቅ ሀይሎች ጋር ማለቂያ የሌለው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ያካሂድ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ማኪያቬሊ በርካታ ዲፕሎማሲያዊ ተልእኮዎችን ይወጣ ነበር፡፡ ከኒኮሎ ማኪያቬሊ ተልእኮዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡ በ1499 ለፍሎረንስ የጦር ስልት ምቹ ይዞታ የነበረች ትንሽዬ ግዛት አስተዳዳሪ ከነበረችው ካቴሪና ስፎርዛ ጋር ተደራድሯል፡፡ በ1500 ፒሳ ላይ የሚካሄደውን ጦርነት ቀጣይነት እንዲኖረው ወደ ፈረንሳይ ተልኮ የንጉስ ሉዊን እርዳታ ለማስገኘት ሞክሯል፡፡ በ1502 እያደገ የመጣው የቄሳር ቦርጂያ የግዛት ማስፋፋት ምኞት በፍሎረንስ ላይ የፈጠረውን ስጋት ለማጣራት ወደ ቄሳር ቦርጂያ ተጉዟል፡፡ በ1503 የአዲሱን ጳጳስ ምርጫና ፖሊሲዎች ለመታዘብና ለመዘገብ ወደ ሮም አቅንቷል፡፡ በ1506 ጁሊየስ 2ኛ የቤተ ክርስትያኗን የቀድሞ

ግዛቶች መልሶ ለማዋሀድ በሚያደርገው ዘመቻ ላይ ፍሎረንሶች እርዳታ እንዲያደርጉ በተጠየቁበት ጉዳይ ላይ ለመወያየት ወደ ኒፔ አምርቶ ተደራድሯል፡፡ በ1507 በሮም የንጉሰ ነገስትነት ዘውድ ለመጫን ለሚያስፈልገው ወጪ የፍሎረንስን ድርሻ ለመወሰን ወደ ማክሲሚሊያን ሄዶ ተደራድሯል፡፡

ይሁን እንጂ ኒኮሎ ማኪያቬሊ ነጥሮ መውጣት የሚችል አይነት ስኬታማ ዲፕሎማት አልነበረም፡፡ የላኩትን ሰዎች ጥቅም የሚጻረር ማንኛውንም ጉዳይ በሙሉ ስልጣን የመደራደር መብትም አልተሰጠውም ነበር፡፡ ሆኖም ብዙ ጉዞዎችን አድርጓል። በአገልግሎት ዘመኑ አይኖቹን ከፍቶ በንቃት ይመለከታል፡፡ በደብዳቤዎቹ፣ በዘገባዎቹና በአስተያየቶቹ ላይ ስል በሆነ ብልጠት የተቃኘ አመለካከቱ ላይ የተመሰረቱ ሀሳቦቹ ይንጸባረቃሉ፡፡ በርግጥ እነዚህን ሀሳቦች ነበር በኋላ ላይ በመጽሐፍ መልክ ያጠናቀራቸው፡፡ በተለይም የጎበኛቸውን ግዛቶች መሰረታዊ የፖለቲካ ሁናቴ በመረዳትና ከተለያየ አቅጣጫ በጥልቀትና በጥንቃቄ የተጤኑ ጥቅል ድምዳሜዎችን በማበጀት ረገድ ከብዙሀኑ የላቀ ልእልናውን አስመስክሯል፡፡

በዚህ ወቅትም ነበር ፍሎረንስ ከቅጥረኛና ከእርዳታ ጦር ጥገኝነት ተላቃ የራሷ ጠንካራ ሚሊሺያ ትገነባ ዘንድ ጠንካራና ጽኑ ፍላጎት ያደረበት፡፡ ይሁን እንጂ በዚህም ረገድ አልታደለም፡፡ እርግጥ በ1505 ሶደሪኒ፣ የፍሎረንስን ሚሊሺያ የመገንባት ህልሙንና መርሀ ግብሩን እንዲተገብር ፈቅዶለት ነበር፡፡ ይህንንም ተከትሎ ማኪያቬሊ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በመላው የፍሎረንስ ግዛት እየተዘዋወረ ሁነኛ ወታደሮችን ለመመልመል ሞክሯል፡፡ በ1507 መጀመሪያ ላይ በተላለፈው

ድንጋጌም ማኪያቬሊ ራሱ በቻንስለርነት የሚመራው ከዘጠኝ ኮሚቴዎች የተውጣጣ ሚሊሺያ ተመስርቶ ነበር፡፡

ሆኖም የማኪያቬሊ ወታደሮች ከፒሳ ጋር በተደረገው ፍልሚያ ማንነታቸውን ሊያስመሰክሩ አልቻሉም፡፡ በ1512 ከስፔይኖች ጋር በተደረገው ውጊያም (ምንም እንኳን መጨረሻ ላይ ክህደት የተፈፀማቸው ቢሆንም) ድል አልቀናቸውም፡፡ ይህም ሆኖ ኒኮሎ ማኪያቬሊ የፍሎረንስን የቀድሞ የሲቪልና ወታደራዊ አቋም መልሶ ለማደስ ያሳየው ጽናትና ተጋድሎ ከ1529 — 1530 ዓ.ም ድረስ ሪፐብሊኩ የተደረገበትን የተራዘመ የከበባ ጦርነት በጀግንነት ለመቋቋም ባሳየው ብቃት ፍሬ ለማፍራት ችሎ ነበር፡፡

ነገር ግን የኒኮሎ ማኪያቬሊ ታማኝነት ለግዛቱ እንጂ ለሪፐብሊኩ አልነበረም፡፡ የሚዴቺ አገዛዝ ወደ ዙፋኑ ሲመለስ ከቦታው የተሰናበተው ማኪያቬሊ ለከባድ ኪሳራ ተዳርጎ ነበር፡፡ በፖለቲካ ህይወት ውስጥ የመሳተፍ እድል ተነፍጎት፣ የወቅቱን ፖለቲካዊ ክዋኔዎች ከርቀት ተስፋ በቆረጠ መንፈስ ይከታተል ነበር፡፡ ሆኖም የእርሱ ኪሳራ ለእኛ ትርፍ ነው፡፡ ቅርታውን ሁሉ በመጽሐፎቹ ውስጥ አፍስሷቸዋልና፡፡ ለፖለቲከኞች ለመለገስ አጥብቆ የቋመጠላቸውን ምክሮች በወረቀት ላይ አስፍሯቸዋል፡፡

በኖቬምበር 1512 (ለሚዴቺ ስለ መንግሥት አመራር የምክር ደብዳቤዎች ከላከላቸው በኋላ ነው ተብሎ ይገመታል) እንቅስቃሴው የተገደበ ነበር፡፡ ከተወሰኑ ወራት በኋላ በአዲሱ አገዛዝ ላይ በተቃጣ ሴራ ላይ ተካፍለሀል በሚል ለእስርና ለእንግልት ተዳረገ፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ግን ከችሎት በነጻ ተሰናብቶ ከእስር ተለቀቀ፡፡

ከዚህ በኋላ ኒኮሎ ማኪያቬሊ ሳን ካዚኖ በሚገኘው ትንሽዬ የቤተሰብ ይዞታው ተጠቃሎ ገብቶ ራሱን ከፖለቲካ አግልሎ ተቀመጠ፡፡ ከዚያው ሆኖ የፍሎሬንስን ግምቦች ከመመልከትና በከተማዋ በሚከናወኑት ነገሮች ከመደመም በቀር የሚያደርገው አንድም ነገር አልነበረም፡፡ በርግጥ ጥልቅ የሆነው የስነጽሁፍ ሥራውን የተያያዘው ይህን ጊዜ ነበር፡፡

በጡረታ ከተገለለ ከጥቂት አመታት በኋላ በኦሪቼላሪ የስነ ጽሁፍ ስብሰባዎች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ጀመረ፡፡ በወቅቱ ከስራዎቹ የተወሰኑትን ያበረክት፣ እንደጠቢብም ይቆጠር ነበር፡፡ ይሄኑ ከሜዴቺ አባወራዎች ጋር ተግባብቶ ወደ ቢሮ የመመለስ ተስፋው ለምልሞ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ በተወሰነ መልኩ በንግድ ኮሚሽኖች እየተደነመ ትናንሽ አስተዋጽኦዎችን ካበረከተ በኋላ በስተመጨረሻ ለአጭር ቆይታም ቢሆን ወደ ህዝባዊ ስራ የመመለስ እድል አገኘ፡፡ ሮምን ጎብኝቶ ለሚጽፈው የፍሎሬንስ ታሪክ ከጳጳስ ክሌመንት የገንዘብ ጉርሻ አግኝቷል፡፡ በወቅቱ ሚሊሺያ የመቋቋም እቅዱን ለጳጳሱ ማሳመን ባይሳካለትም የፍሎሬንስን ምሽግ የመገንባት ሀላፊነት ተሰጥቶት ነበር፡፡ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ሪፐብሊኩ ዳግም ፍሎሬንስን ሲቆጣጠር ማኪያቬሊ በመስተዳድሩ ላይ ለመሳተፍ የነበረው ጉጉት የሜዴቺዎች ደጋፊ ነው በሚል ተጠርጥሮ ገሸሽ ሲደረግ ከሰመ፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ በአደገኛ የጨጓራ በሽታ ጤናው ተቃውሶ በጁን 1527 (ኑዛዜው ከተደመጠ በኋላ) ህይወቱ አለፈ፡፡ እንደ ልጁ ገለጻ ከሆነ ኒኮሎ ማኪያቬሊ ቤተሰቡን ከከባድ ድህነት ጋር ጥሎ ነበር ያለፈው፡፡

ስለ ማኪያቬሊ የቤተሰብ ህይወት ብዙም የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ወደ 1502 ገደማ ማሪታ ኮርሲኒን አግብቶ ስድስት

ልጆችን ወልዳለታለች፡፡ ባለቤቱ ማሪታ ለትዳሯ እራሷን አሳልፋ የሰጠች ግን በፖለቲካ ህይወት ውስጥ በተጠመደው ማኪያቬሊ ቸል የተባለች አይነት ሴት እንደነበረች ይገመታል፡፡ የማኪያቬሊ ህይወት በብዙዎች ዘንድ እንደሚገመተው ብኩን የአኗኗር ዘዬን የተከተለ ስለመሆኑ እርግጠኛ የሆነ መረጃ ማግኘት ባይቻልም ለወዳጁ ፍራንቸስኮ ቬቶሪ ከአንዲት መልከ ጥፉ ሴተኛ አዳሪ ጋር ስለገጠመው ፍጥጫ የጻፈው ደብዳቤ ግን ከሁሉ በላቀ አስደንጋጭ ነበር፡፡

ከደንታ ቢስ የንግርት በራዥነት በራቀ ኒኮሎ ማኪያቬሊ በጥልቅና ጠንካራ ውስጣዊ ስሜቶች የተቃኘ ሰው ነበር፡፡ በመሆኑም በእድለ ቢስ እጣ ፈንታዎችና በቅጥረኛ ወታደሮች ተታሎ ሲረታ ለመጠነ ሰፌ የስሜት ስብራቶች እጅ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን ከብዙሀኑ የተገለለ፣ በተሸናፊነት ስሜት የተቀባ ፈገግታውን ታቅፎ ብቻውን የቆመ ሰው ምስል ይፈጥራል፡፡ ከልሂቃዊነት የሚመነጭ ቁጥብነትና እራስን የማምለክ አባዜው፣ እረፍት ከማይሰጥ በፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የማድረግ ንዳዱ ጋር ማስታረቅ ያልቻለም ይመስላል፡፡ የማኪያቬሊን የወጣትነት ምስል በተመለከተ በአንድ ወቅት ቪላሪ በዚህ መልኩ አስቀምጦት ነበር፡-

መካከለኛ ቁመት፣ ሸንቃጣ አቋም፣ የሚያብለጨልጬ አይኖችና ጥቁር ጸጉር፣ ትንሽዬ ጭንቅላት፣ የተቀነበበ አፍንጫ፣ ጠባብ አፍ... በጥቅሉ በትኩረት ለሚመለከተው ጥልቅ አሳቢና አስተዋይ መሆኑ ቢታወቅም፣ በሌሎች ላይ ተፅዕኖ የማሳደር ክህሎት ያለው አይመስልም፡፡ ከአፉ አካባቢና ከአይኖቹ የሚረጨውን ፌዘኛ ጨረር በቀላሉ መቆጣጠር አይችልም፡፡

ቀዝቃዛ፣ ግን ገደብ የለሽ አሰላሳይ ያስመስሉታል፡፡ ብዙውን ጊዜ ሀያል በሆኑ ምናባዊ አስተሳሰቦቹ ይዋጣል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምናባዊ ራእዩ እውነታ እስኪመስለው ይመነጠቃል፡፡

በሌላ በኩል ኒኮሎ ማኪያቬሊ ታላላቅ አስተዋጽኦዎችን ማበርከት የሚችል ሰው ነበር፡፡ ከአስርት አመታት በላይ በከባድ ጽናት ሲለፋና ሲደክምለት የኖረው ሪፐብሊክ ሲናድ የማኪያቬሊ እድሜ አርባዎቹ ውስጥ ነበር፡፡ ከሪፐብሊኩ መሽመድመድ በኋላ ከፖለቲካ ስራ በሃይል እንዲገለል በተደረገበት ጊዜ ከጣሊያን ገናና ጸሐፍት ጎራ የሚያሰልፉ በርካታ ስራዎችን አበርክቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ‹The prince› የተሰኘውን ይህን መጽሐፍ ጨምሮ እውነተኛ የፖለቲካ ሥራው የሆነው ‹The discourses on livy›፣ ‹The art of war›፣ ታላቁን ‹The history of florence›፣ አስደሳቹ ‹Dialog on language› እና ብዙ ተቀባይነት ያላገኙት ተውኔቶች ‹Mandragola› እና ‹Clizia› እንዲሁም በርካታ ግጥሞችንና ዝርው ጽሑፎችን አበርክቷል፡፡ ሁለገብነቱና እውቀቱ በርግጥ ላቅ ያለ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ “ልኡሉ” የተሰኘው ይህ መጽሐፉ ብቻውን ከተገቢው በላይ የማኪያቬሊን ምጡቅነት ያንፀባርቃል የሚለው ብዙሀኑን የሚያስማማ አስተያየት ነው፡፡ በርግጥ “ልኡሉ” የተሰኘው መጽሐፉ መሰረታዊ የፖለቲካ አመለካከቶቹን አጠቃልሎ የያዘ ድንቅ የፈጠራ ውጤቱ እንደመሆኑ የማኪያቬሊ ምንነት ቢሰፈርበት ፍርደ ገምድል አያሰኝም፡፡

በተጨማሪም “ልኡሉ” ከዚህ ሁሉ አመታት በኋላም አወዛጋቢነቱ ያልተፈታ፣ አሁንም ድረስ የብዙሀኑን ስሜት የሚገዛ መጽሐፍ ነው፡፡ የመጽሐፉ ትርጓሜ፣ አላማው፣ የተፃፈበት ጊዜ

እንኳ ሳይቀር እስካሁን ፍጻሜ ያላገኘ፣ ሁሉንም የሚያሳምን፣ ሙግቶቹን ሁሉ የሚረታ ምላሽ ያልቀረበላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

በወቅቱ ማኪያቬሊ ይህ መጽሐፍ ዝርዝር ማስተካከያ የሚፈልግ አይነት መስሎ የታየው አይመስልም፡፡ በዲሴምበር 10፣ 1513 ለፍራንቸስኮ ቬቶሪ በጻፈው ደብዳቤ ቢያንስ ጥራዝ ነጠቅ የሆኑ ንድፈ ሀሳቦችን ውድቅ ለማድረግ ስለ መጽሐፉ ጥንስስ ማብራሪያ ሰጥቶ ነበር፡፡ ደብዳቤው ከፍሎረንስ ርቆ ስላለው ህይወቱ በጸጸት ስሜት በመዘርዘር ይጀምራል፡፡ ማኪያቬሊ ጎህ ሲቀድ ከቤቱ ይወጣል፡፡ እንጨት ጠራቢዎቹ ስራውን በአግባቡ እየሰሩለት መሆኑን ይከታተላል፡፡ ከዛም የነዳንቴን፣ ፔትራርክ፣ ኦቪድ ወይም ቲቡለስን ጽሑፍ እያነበበ የራሱን የፍቅር ህይወት በተናጠል እያስታወሰ ይደሰታል፡፡ ከዛም ወደ መንደሩ ሆቴል ዘልቆ ከአልፎ ሂያጅ መንገደኞች ጋር ሲጨዋወት ይቆያል፡፡ ከቤተሰቡ ጋር መናኛ እራት ከበላ በኋላ ወደ ሆቴሉ ተመልሶ ከመንደሩ ነጋዴዎች ጋር ካርታ ወይም ዳይስ በመጫወት ጊዜውን ያሳልፋሉ፡፡ ከዛም ምሽት ይነግሳል፡፡ ይህን ጊዜ ኒኮሎ ማኪያቬሊ ወደ ቤቱ ይመለስና ከጥናት ክፍሉ ይመሽጋል፡፡ የመነቸኩ ልብሶቹን አውልቆ የችሎት ልብሱን ያጠልቃል፡፡ በምናቡ ክንፍ ያወጣና ወደ ጥንታዊው ቤተ መንግሥት በመብረር ከቀድሞ ዘመን ታላላቆች ጋር በወዳጅነት መንፈስ ይነጋገራል፤ ስለ ፖለቲካ፣ ስለተፈጠረለት ነገር ይወያያል፡፡ እነዛን ሰዎች የፖሊሲዎቻቸውን መንስኤ ይጠይቃቸዋል፤ እነሱም ይነግሩታል፡፡

እናም ከዚህ ውይይት ‹‹ግዛቶችን በተመለከተ ትንሽዬ ስራ ፅፌ አጠናቅሬያለሁ፡፡ ግዛት ምን ማለት እንደሆነ፣ በስንት

አይሸሬ፣ ዘመን ተሻጋሪ ስራ ለመሆን በቅቷል፡፡ መጽሐፉ ለሚፈጥረው ንዝረትና ተደምሞ በማኪያቬሊ ውስጥ ያለው ጥበበኝነት ነገራትን ከመተንተን ብቃቱ ያልተናነሰ ሚና አለው፡፡ ተቃርኖና ጥቅል ድምዳሜዎችን ይወዳል፡፡ ከአመክንዮ ይልቅ ደመነፍስን ይንተራሳል፡፡ ከአንባቢያን ልቦና በቀላሉ የማይፋቅ ተጽእኖ ለማስረጽ ነጥቦቹን ተውኔታዊ አድርጎ፣ ጥቅል ድምዳሜዎቹን አጋንኖ ያስቀምጣቸዋል፡፡ ግልጽነቱና የድፍረቱ አስገራሚነት፣ ቀልብን የሚያሸፍቱ አረፍተ ነገሮቹ፣ በማንኛውም መስዋዕትነት ለሚመጣ ውጤታማነት የሚሰጠው አድናቆት፣ የውጭ ወራሪዎችን አረመኔነት ከነሱ ባልተናነሰ መራራነት ይመክቱ ዘንድ በጣሊያን ልኡላን ላይ የሚያወርደው ተግሳፅ… መጽሐፉ ለበርካታ ክፍለ ዘመን ከሚጠቀስባቸው ከራሱ ምንጭ የተቀዱ ልዩ ዘውጎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ከሁሉ ነገር በላቀ ግን ሁሉም በይሁንታ ቢታለፍ እንኳ የመጽሐፉ ትርጓሜ በተግባር ሳይተገበር በሀሳብ ደረጃ ብቻ ብዙዎቹን መቅፈፉ በእንጥልጥል እንደተተወ የሚቀር ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡

ሳተን ሱሬ (ጂ.ቢ)

# ልኡሉ

"በዚህ መጽሐፍ ሥራውንና ሰብዕናውን ትቃኙ ዘንድ ካቀረብንላችሁ ሰው የላቀ በሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ አወዛጋቢ ጸሐፊ መኖሩን እንጠራጠራለን።"

ማኮሌይ

# ከኒኮሎ' ማካቬሊ

## ለግርማዊ ሎሬንሶ ደ' ሜዴቺ የተጻፈ ደብዳቤ

ከአንድ ልኡል ዘንድ ግርማ መጎናጸፍ የሚሹ ሰዎች እራሳቸውን ላቅ ያለ ዋጋ ከሚሰጡት ገጸ በረከት ወይንም ልኡሉን በተለየ ያስደስተዋል ከሚሉት ስጦታ ጋር የማቅረብ ልምድ ይከተላሉ። በመሆኑም ብዙውን ጊዜ ልኡላን ፈረስ፣ መሳሪያ፣ በወርቅ የተንቆጠቆጡ አልባሳት፣ የከበሩ ድንጋዮችና ለታላቅነታቸው የሚመጥኑ ሌሎች ጌጣ ጌጦች ሲበረከትላቸው እናያለን። አሁን፣ እኔም እራሴን ከልባዊ የፍቅር ማስታወሻዬ ጋር ስለግርማዊነትዎ ማበርከት ወደድኩ። ሆኖም በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ በነበረኝ ተሳትፎ ካካበትኩት ሰፊ ተሞክሮና በጥንታዊው አለም ላይ ባደረግኩት ጥልቅ ጥናት ከቀሰምኩት የታላላቅ ሰዎች አድራጎት በቀር ስለግርማዊነትዎ ክብር ይመጥናል ብዬ የማስበው አንዳችም ሀብት የለኝም። በከፍተኛ ልፋት መርምሬ፣ ለረዥም ጊዜ አውጥቼ አውርጄ ያገኘሁትን በትንሽዬ መጽሐፍ አጠቃልዬ ለግርማዊነትዎ ማስታወሻ ከምለው የላቀ የረባ ዋጋ ያለው ገጸ በረከት አይኖረኝም።

ምንም እንኳ ይህ ስራ ከእርስዎ ፊት ለመቅረብ የሚመጥን ፋይዳ እንደሌለው ቢገባኝም፣ ለበርካታ አመታት በከፍተኛ ጭንቅና ማጥ ተፈትኜ የቀሰምኩትን ሁሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠቅልዬ ከማቅረብ የላቀ ጠቃሚ ነገር ማበርከት እንደማልችል በመረዳት ገጸ በረከቴን በቅን ልቦና እንደሚቀበሉኝ ፍጹም እርግጠኛ ነኝ።

ይህን መጽሐፍ ዙሪያ ጥምጥም በሆኑ ጥራዝ ነጠቅ አረፍተ ነገሮች ወይም ከባድ በሚመስሉ ምትሀታዊ ቃላት ለመቀባባት ወይም ለማስጌጥ አልሞከርኩም፡፡ ወይም ግኝታቸውን ለመግለጽ ከንቱ ውዳሴና የተጋነኑ ሽንገላዎችን እንደሚያኸጎደጉዱት አልተመጻደቅኩም፡፡ በርግጥ የእኔን መጽሐፍ ከሌሎች ልዩ የሚያደርገው ነገር የለም፡፡ አድናቆትም ከተገባው ምናልባት ለየት ካለ ይዘቱ ወይም ከሚያነሳቸው ጉዳዮች አሳሳቢነት የሚመነጭ ይሆናል፡፡

እንዲሁም የግዛት አስተዳደርን በተመለከተ ለመደራደርና ህጋጋቱን ለማርቀቅ መነሳቴ ህግ አክባሪና መሰረተ ጨዋ በሆነ ልኡል ዘንድ በማይመለከተው ጣልቃ የገባ ደፋር እንደማያሰኘኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምክንያቱም የአካባቢውን ገጸ ምድር የሚስል አንድ የመልክአ ምድር ተመራማሪ የተራሮችንና ጉብታዎችን አቀማመጥ ለማጤን ወደ ሜዳ ይወርዳል፤ ዝቅተኛ ቦታዎችን ለማጤን ደግሞ ከተራራ ጫፍ ይወጣል፡፡ በመሆኑም የሰዎችን ተፈጥሮ ሙሉ ለሙሉ ለመገንዘብ ልኡል መሆን ግድ ይላል፤ የልኡላንን ተፈጥሮ ሙሉ ለሙሉ ለመገንዘብ ደግሞ ተራ ግለሰብ መሆን ያስፈልጋል፡፡

ይህችን ትንሽዬ ገጸ በረከትም ከእኔ በተላከችበት መንፈስ ይቀበሉኝ ዘንድ ግርማዊነትዎን እጠይቃለሁ፡፡ በርግጥ ካነበቡትና በጥልቀት ካጤኑት፤ ቀናኢ ዕጣ ፈንታዎ ከሌሎች ምግባርዎ ተዳምሮ የታላቅነትን መንበር ይጨብጡ ዘንድ ያለኝን ጥልቅ ምኞት ይረዱታል፡፡ ምናልባትም ግርማዊነትዎ ከተቀመጡበት የታላቅነት አጥናፍ ሆነው አንዳንድ ጊዜ ዝቅተኛዎቹን ስፍራዎች ከቃኙ፤ ምን ያህል ባልተገባ ሁኔታ ማለቂያ የሌለውን የከፋ ውርደት የበዛበት ጭንቀት ተሸክሜ እንደምኖርና በዕድለ-ቢስ ዕጣ ፈንታዬ እንደማቀቅኩ ይረዳሉ፡፡

# የግዛቶች ዓይነትና አመሠራረታቸው

## 1. የግዛቶች ዓይነትና አመሠራረታቸው

የሰው ልጅ በቀደምት ዘመኑም ሆነ አሁን ባለንበት ጊዜ ይተዳደርባቸው የነበሩ፣ እየተዳደረባቸው ያሉ ግዛቶችና ክልሎች አንድም በህዝባዊ መንግስት አሊያም በልኡላዊ አስተዳደር የሚመሩ ናቸው። በልኡላዊ አስተዳደር የሚተዳደሩ ግዛቶች በውርስ የሚተላለፉ ሲሆን፣ የመሳፍንቱ ቤተሰቦች ለረዥም ጊዜ እየተቀባበሉ ያቆዩዋቸው ወይም እንደ አዲስ የመሰረቷቸው ሊሆኑ ይችላሉ። እንደ አዲስ የሚመሰረቱ ልኡላዊ ግዛቶች በአንድ በኩል ፍራንሲስኮ ስፎርዛ ሚላን ውስጥ የፈጠረውን አይነት አዲስ ግዛት ሊሆኑ ሲችሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኔፕልስ ግዛት ወደ ስፔይኑ ንጉስ እንደተቀላቀለችው የአንድ ንጉሳዊ ግዛት ክንፍ ሆነው ሊመሰረቱ ይችላሉ። በዚህ መልኩ የሚመሰረቱ ግዛቶች በአንድ ልኡል ቁጥጥር ስር የኖሩ ወይም ከነጻ አስተዳደር የተዋቀሩ ሊሆኑ ይችላሉ። መስራቹ ልኡል ግዛቶቹን በራሱ ሰራዊት አሊያም በሌሎች ልዕለ ሀያላን ድጋፍ፣ በቀናኢ እድል ወይም በራሱ ጦር ጀግንነትን በተላበሰ ተጋድሎ ሊመሰርት ይችላል።

## 2. የውርስ ግዛቶች

ከዚህ ቀደም በህዝባዊ አስተዳደር የሚመሩ ግዛቶችን በተመለከተ መጠነ ሰፊ ዳሰሳ ስላቀረብኩ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን ርእስ ደግሜ አላነሳም፡፡ በዚህ መጽሐፌ በጥልቀት የማተኩረው በልኡላዊ ግዛቶች ላይ ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውን አካሄድ ተመርኩዤ በልኡላን አገዛዝ የሚተዳደሩ ግዛቶች በምን አይነት አግባብ መመራትና ለዘለቄታው ተጠብቀው መቆየት እንዳለባቸው ሀሳቤን አቀርባለሁ፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በውርስ የተገኙ ግዛቶች ከአስተዳዳሪው ልኡል ቤተሰብ ጋር የተላመዱ እንደመሆናቸው እነዚህን ለማስተዳደር በጣም ጥቂት የሚባል ችግር ቢገጥማቸው ነው፡፡ ምክንያቱም በውርስ የተገኙ ግዛቶችን ለማስተዳደር በቀደምት አያቶች የተቋቋሙትን ተቋማትና ህግጋት (ደንቦች) መንከባከቡ፣ ለወቅቱ የሚስማማውን ህግ ማውጣቱ ብቻውን በቂ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ልኡሉ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ አሳማኝ ትጋትን ማሳየት ከቻለ ሁሌም ትእዛዙን አስከብሮ፣ ህልውናውን አስጠብቆ ለረዥም ዘመን መግዛት ይችላል፡፡ ያልተጠበቁ አደጋዎች ወይም ተቀናቃኝ ሀይሎች ዘውዱን ካልነጠቁት በቀር ህልውናውን የሚፈታተን መጠነ ሰፊ ችግር አይገጥመውም፡፡ በዚህ መልኩ የገዢነት ክብሩን ቢገፈፍ እንኳን ዘውድ ነጣቂው አንድ አስተዳደራዊ ችግር በተጋረጠበት ቅጽበት ልኡሉ አንሰራርቶ እንደገና ሊያሸንፈው ይችላል፡፡

እዚህ ጋር ጣሊያናዊውን የፌራራ ሀገረ ገዥ እንደምሳሌ እናውሳ፡፡ ከሌሎች ምክንያቶች በኋላ ሀገረ ገዢው ለረዥም ዘመን

በግዛቱ ተደላድሎ የተቀመጠ ባይሆን ኖሮ በ1484 በቬኔሻውያን የተቃጣበትን ወረራና 1510 በጳጳስ ጁሊየስ ከደረሰበት ጥቃት አንሰራርቶ መነሳት በተሳነው ነበር፡፡

ብዙውን ጊዜ በውርስ ባገኘው ግዛት ውስጥ ለረዥም ዘመን ተደላድሎ የተቀመጠ ልኡል፣ በዜጎቹ ላይ አስከፊ ጥቃት የመቃጣት ምክንያትና ፍላጎት አይኖረውም፡፡ ይህ ደግሞ በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅነት ያተርፍለታል፡፡ እንዲህ አይነቱ ልኡል ከተለምዶ ባፈነገጡ ኢ-ሰብአዊ አድራጎቶች የዜጎችን ጥላቻ እስካልቀሰቀሰ ድረስ የሎሌዎቹ ይሁንታ ሁሌም ከርሱ ጋር ነው፡፡ እናም ቀዳማዊውን ልማድ በማጽናትና ህግጋቱን ጠብቆ በማቆየት የህዝቡ የለውጥ ተሃድሶም ሆነ መነሳሳት ይጠፋል - ምክንያቱም ትንሽዬ ለውጥ ተከታታይ ለውጦችን ታቀጣጥላለች፡፡

## 3. ቅይጥ የመሳፍንት ግዛቶች

አዳዲስ ግዛቶችን ማስተዳደር በውርስ የተገኙትን እንደማስተዳደር አይቀልም፡፡ አንድ ልኡል ሌላ አዲስ ግዛት ለመቆጣጠር በሚያደርገው ሂደት ውስጥ የሚገጥመው አንድ የተለመደ መሰናክል አለ፡፡

ብዙውን ጊዜ ሰዎች የተሻለ አስተዳደር ለማግኘት በመሻት መሪዎቻቸውን የማስወገድ ፍላጎት ያድርባቸዋል፡፡ ይህ ተስፋቸው በመሪያቸው ላይ እንዲነሱ ይገፋፋቸዋል፡፡ ሆኖም ተተኪው ሀገረ ገዥ ነግሶ ሁኔታዎች ከመሻሻል ይልቅ ተባብሰው ሲገኙ ህዝቡ በቀቢጸ ተስፋ እንደተማለለ ይረዳል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚከሰተው

አዲስ ግዛትን በመቆጣጠር ሂደት ውስጥ የግድ መወሰድ ያለባቸው አንዳንድ እርምጃዎች በመኖራቸው ነው፡፡ ግዛቱን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል ልኡሉ ወታደሮቹን በማሰማራትና ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን በመፍጠር ህዝቡ ላይ ጉዳት ለማድረስ ይገደዳል፡፡ በመሆኑም ግዛት በማስፋፋቱ ሂደት ውስጥ ጉዳት የደረሰባቸውን አካላት መራር ጥላቻ ያተርፋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አዲሱን ግዛት እንዲቆጣጠር ድጋፍ ያደረጉ ሀይሎችንም ወዳጅነት ማትረፍ አዳጋች ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ደጋፊዎቹ የሚጠብቁትን ያህል መስጠት ወይም የደጋፊዎቹን ተስፋ እውን ለማድረግና የሁሉንም ፍላጎት ማሟላት በእጅጉ ከባድ ነው፡፡ ሀይልን በደጋፊዎቹ ላይ እንዳይጠቀም ደግሞ በውለታቸው ሰንሰለት ይታሰራል፡፡

አንድ ልኡል ያሻውን ያህል ሠራዊት፣ የጦር መሳሪያና የሀይል ሚዛን ቢኖረውም ወደሌላ ግዛት ሰርጎ ለመዝለቅ በህዝቡ መልካም ፈቃድና ይሁንታ ሊታገዝ ይገባል፡፡ በዚህ የተነሳ ነው የፈረንሳዩ ንጉስ ሉዊ 12ተኛ ሚላንን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቆጣጥሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያጣት፡፡ በመጀመሪያው ፍጥጫ ላይ የሉዶቪኮ ሰራዊት ብቻውን ሚላንን ከፈረንሳይ ለመንጠቅ በቂ ነበር፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያ ላይ በራቸውን በፈቃደኝነት የከፈቱለት ጣሊያናውያን በንጉሱ ላይ የጣሉት ተስፋና ከንግሱ የሚጠብቁት ጥቅም እውን እንደማይሆን ሲረዱ በአዲሱም አስተዳደር እናገኛለን ብለው የጠበቁትን ስላላገኙ የወደቀባቸውን ውርደትና ሀፍረት መቋቋም አልቻሉም ነበር፡፡ ያመፁ አገሮች እንደገና ድል ሲሆኑ በቀላሉ የማይጠፉ መሆናቸው የተረጋገጠ እውነት ነው፡፡ ስለሆነም ፈረንሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ባደረገችው

ሙከራ ላይ በርካታ ተቀናቃኞች አፍርታ፣ ሰራዊቷ ከጣሊያን ግዛት ተደምስሶ ለመውጣት ተገድዳለች፡፡

ከዚህ በመቀጠል ለፈረንሳይ ዳግማዊ ሽንፈት መንስኤውን፣ ንጉሱ የገጠመውን ተግዳሮት በምን መልኩ መፍታት ይችል እንደነበርና በሱ ቦታ ያለ ሌላ አካል በምን አይነት መንገድ የግዛት ማስፋፋቱን ሂደት አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ሊቀጥልበት እንደሚችል እናያለን፡፡

ግዛት በማስፋፋት ሂደት ውስጥ የሚመሰረቱ አዳዲስ ግዛቶች አንዳንድ ጊዜ ግዛቱን ከሚያስፋፈው ሀይል ጋር ተመሳሳይ ቋንቋና ባህል የሚጋሩ ሲሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከወራሪው ግዛት ፍጹም የተለየ ባህልና ልምድ ይኖራቸዋል፡፡ አዲሱ ግዛት ከቀድሞው ተመሳሳይ ቋንቋና ባህል ካለው ግዛቱን የመቆጣጠርና የማስተዳደር ሂደቱ የተለሳለሰ ይሆናል፡፡ ከልኡሉ የሚጠበቀው የቀድሞውን ገገር መደብ የዘር ግንድ ጨርሶ ማጥፋት ብቻ ነው፡፡ የተቀረው ዜጋ የወትሮው የአኗኗር ሁኔታ ካልታወከ፣ የባህል መፋረስ ካልተፈጠረና የቀረጥ ጭማሪ ካልተደረገ ኑሮውን በጸጥታ ይመራል፡፡

በፈረንሳይ ስር የነበሩትን ቡርጋንዲን፣ ብሪታኒ፣ ጋስኮኒና ኖርማንዲን እንደምሳሌ ማንሳት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳ ከፈረንሳያውያኑ ጋር የቋንቋ ልዩነት ቢኖራቸውም ባህላቸው ተመሳሳይ በመሆኑ ከአገዛዙ ጋር በቀላሉ ተስማምተው መኖር ችለዋል፡፡ በዚህ መልኩ አዳዲስ ግዛቶችን በአግባቡ ለመቆጣጠር ልኡሉ ሁለት ነገሮችን ማጤን ይኖርበታል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የግዛቱ የቀድሞው ንጉስ ቤተሰቦች የግድ መጥፋት አለባቸው፡፡

ከዛም የቀድሞውን ስርአት ህግጋትና የቀረጥ ደንብ በመለወጥ ባጭር ጊዜ ውስጥ አዳዲሶቹ ግዛቶች ከነባሩ ጋር እንዲዋሀዱ ማድረግ ይቻላል፡፡

ነገር ግን አዲስ የሚመሰረቱት ግዛቶች ግዛቱን በማስፋፋት ሂደት ላይ ካለው ግዛት በቋንቋ፣ በባህልና በተቋማት የሚለያዩ ከሆነ በቀላሉ የማይፈቱ አዳጋች መሰናክሎች ይነሳሉ፡፡ እነዚህን መሰናክሎች በቁጥጥር ስር ለማዋል እድለኝነትንና ከፍተኛ ጥንካሬን ይጠይቃል፡፡ እንደዚህ አይነት ግዛቶችን ለማስተዳደር ምቹ ከሆኑት መንገዶች አንዱ በግዛቶቹ ውስጥ በአካል ተገኝቶ ማስተዳደር ነው፡፡

ይህ መንገድ አዲሱን ግዛት የተረጋጋና ዘላቂነት ያለው ያደርገዋል፡፡ ቱርኮች በግሪክ ለነበራቸው ስኬት መሰረቱ ይህ ነው፡፡ ከወሰዷቸው በርካታ እርምጃዎች በላቀ፣ ግዛቱን በአካል ተገኝተው ባያስተዳድሩ በአግባቡ መቆጣጠር በተሳናቸው ነበር፡፡ በቦታው ተገኝቶ ማስተዳደር ግዛቱ ውስጥ ችግሮች ሲከሰቱ በወቅቱ ለመመልከትና አፋጣኝ እርምጃዎችን ለመውሰድ ይጠቅማል፡፡ አስተዳዳሪው በቦታው ላይ ካልተገኘ ችግሮች መከሰታቸውን የሚረዳው ከተባባሱ በኋላ ነው፡፡ ለችግሮቹ መፍትሄ ለማበጀት ቢሞክር እንኳን የሚወስዳቸው እርምጃዎች የረፈደባቸው ይሆናሉ፡፡

ከዚህም ባሻገር የያዙትን ግዛት በአካል ተገኝቶ ማስተዳደር አዲሱን ግዛት በእንደራሴዎችና በባለስልጣናት ከመመዝበር ይታደገዋል፡፡ ዜጎችም ከገዢው መደብ ቀጥተኛ እርዳታ ስለሚያገኙ ፍላጎታቸው ይሟላል፡፡ ገዢያቸውን ለመውደድ፣ ለማክበርና ለመገዛት ምክንያት ይሆናቸዋል፡፡

ሌላኛው ወሳኝና ጠቃሚ ነገር ደግሞ በጥቂት ቦታዎች ላይ የሰፈራ መንደሮችን ማዘጋጀት ነው፡፡ የሰፈራ ካምፖችን ማዘጋጀት አዲሱ ግዛት ከነባሩ ጋር ጥብቅ ትስስርና ቁርኝት እንዲፈጥር ያደርገዋል፡፡ የሰፈራ መንደር የማይመሰርት ገዢ በርካታ ታጣቂ ሰራዊትና እግረኛ ወታደሮችን በየጊዜው ከቦታ ቦታ ማንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ ይህ ደግሞ ለከባድ ወጪ ይዳርጋል፡፡ የሰፈራ መንደሮችን መቋቋም ወጪ ቆጣቢ ስልት ነው፡፡ አንድ ልኡል በትንሽዬ ወጪ ወይም ምንም ሳያወጣ የሰፈራ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይችላል፡፡ ጉዳት ሊያደርስ የሚችለው ለሰፋሪዎቹ መኖሪያ መሬትና ቤት በሚነጥቃቸው ሰዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ተጎጂዎች በቁጥር አናሳ ስለሚሆኑ የተበታተኑ፣ አቅመ ደካሞች ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም በልኡሉ ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሊያደርሱ አይችሉም፡፡ የተቀረው ሰፊው ህዝብ ምኑም ስለማይነካበት አርፎ ይቀመጣል፡፡ በሌላው የደረሰው መፈናቀል ይደርስብኛል ብሎ ስለሚሰጋ በጸጥታ ኑሮውን ይቀጥላል፡፡

ለማጠቃለል የሰፈራ መንደሮችን ማቋቋም ወጪ ቆጣቢና እምነት የሚጣልበት አካሄድ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚያደርሰው ጉዳት ውሱን ነው፡፡ ተጎጂዎቹም አስቀድሜ እንደገለጽኩት አቅመ ደካማና የተበታተኑ በመሆናቸው የመልሶ ማጥቃት እርምጃ የመውሰድ አቅም አይኖራቸውም፡፡

እዚህ ጋር ሊተኮርበት የሚገባው እውነት፣ ሰዎች ከተቻለ በእንክብካቤ መያዝ፣ ካልሆነ ደግሞ በማያዳግም መልኩ መደምሰስ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ለጥቃቅን ጉዳቶች በቀልን ያረግዛሉ፤ በታላላቅ ጉዳቶች ግን ይሰበራሉ፡፡ ስለዚህ

አንድ ልኡል በስዉ ላይ ከሚያደርሰው ማንኛውም ጉዳት አስቀድሞ እርምጃው ከበቀል ስጋት ነጻ መሆኑን ሊያጤን ይገባል፡፡

የሰፈራ መንደሮችን ከመገንባት በተቃራኒ ሰራዊቶችን መላክ ወታደራዊ ወጪን ስለሚያንር የገገርው ገቢ በጠቅላላ ለመከላከያ ሰራዊት መዋል ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ግዛት የማስፋፋት ትርፉ ኪሳራ ብቻ ይሆናል፡፡ ከዚህም ባሻገር ልኡሉ ታጣቂ ወታደሮችን በግዛቱ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች እያዞረ ሲያሳድር ከዚህ የከፋ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ የግዛቷ ነዋሪ ባጠቃላይ በዚህ ቁጣን በሚያነሳሳ ድርጊት ይማረራል፣ እያንዳንዱ ዜጋ ወደ ጠላትነት ይቀየራል፡፡ ይሄ አይነቱ ጠላትነት ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ዜጎች በገዛ ቤታቸው የበታች ተደርገዋል፣ ተሸናፊ ሆነዋል፡፡ በማንኛውም መልኩ ቢሆን ይህ አይነቱ ግዛትን የማስጠበቅ መንገድ ቅኝ ገዢነት ጠቃሚ የሆነውን ያህል ጎጂ የሚባል ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከወራሪው የተለየ ብሂል ያላቸውን አዳዲስ ግዛቶች በአግባቡ ለመቆጣጠር ልኡሉ በዙሪያው የሚገኙ ትናንሽ አጎራባች ሀገራት ጠባቂና መሪ መሆን እንዲሁም ጠንካራና ሀያል የሆኑትን ማዳከም ይኖርበታል፡፡ ከዚህም ባለፈ ከግዛቶቹ አንዱ ሀያል በሆነ ሌላ የውጭ ተቀናቃኝ እንዳይወረር መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

ብዙውን ጊዜ የውጭ ሰርጎ ገቦች ግዛቱን የሚቀላቀሉት በጽንፍ ቀቢጸ ተስፋ ወይም ስጋት በተመረዙ የውስጥ ሀይሎች ጥሪ ነው፡፡ ሮማውያን ወደ ግሪክ ምድር ሰርገው የገቡት አንድ

ጊዜ ከኢቶሊናውያን በተደረገላቸው ጥሪ ነበር፡፡ ከዚህም በኋላ ሮማውያውን የወረሯቸውን ግዛቶች በሙሉ የተቆጣጠሩት በነዋሪዎች ጥሪና ትብብር ነው፡፡

በርግጥ ይህ ሁሌም የሚከሰት እውነት ነው፡፡ አንድ ሀያል ሀገር አንድን ግዛት ሲወር አቅም ያጡ ሀይሎች በመሪያቸው ቀናተኝነት ተገፋፍተው ድጋፋቸውን ይሰጡታል፡፡ እነዚህን ደካማ ሀይሎች በተመለከተ የሚከሰት ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ችግር አይኖርም፡፡ ምክንያቱም በራሳቸው ጊዜ የግዛት መስፋፋቱ አካል ይሆናሉ፡፡

በዚህ ደረጃ ልኡሉ መጠንቀቅ ያለበት እነዚህ ደካማ ግዛቶች በቂ ሀይልና ስልጣን እንዳይገነቡ በማድረጉ ረገድ ብቻ ነው፡፡ ደግሞም በራሱ ጥንካሬና በሌሎቹ ድጋፍ ሀያል የሆኑቱን በማፈንና በመቆጣጠር በማንኛውም ረገድ የአካባቢው ሀያል መሆን ይችላል፡፡ እነዚህን እውነታዎች ልብ ያላለ ማንኛውም ሀያል ሀይል የያዘውን ሁሉ ከመቅጽበት ያጣል፡፡ በከፍተኛ ትግል ይዞታውን ለማጽናት ቢችል እንኳ ስፍር ቁጥር የሌላቸው እክሎች ይጋረጡበታል፡፡

ሮማውያን እነዚህን እውነታዎች በሚገባ የተረዱ ይመስላሉ፡፡ በወረራ በተቆጣጠሯቸው ግዛቶች ውስጥ የሰፈራ መንደሮች ይገነባሉ፡፡ ጥንካሬያቸውን እያመዛዘኑ ደካሞችን ይረዳሉ፡፡ ሃያል የሆኑ ሀይሎችን ደግሞ ከመቅጽበት ይደመስሳሉ፡፡ ከውጭ የሚመጡ ወራሪዎች ሀይል እንዳያገኙ ይከላከላሉ፡፡

በዚህ ረገድ ሮማውያን ሲያደርጉ የቆዩት ከብልህ መሪ የሚጠበቀውን ነው፡፡ አሁን ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ

ከማበጀት ባሻገር ወደፊት ይከሰታሉ ብለው የሚያስቧቸውን
አስቀድመው ለመቅረፍ ይጥራሉ፡፡ በርግጥ ማንኛውም ችግ
ከመከሰቱ ቀድሞ ከታወቀ በቀላሉ መድሀኒት ሊበጅለት
ይችላል፡፡ ችግሩ እስኪከሰት ከጠበቅክ ግን የቱንም መድሀኒት
ችግሩን ሊፈውሰው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ችግሩ አንደ
ሊያገግም ከማይችልበት ደረጃ ደርሷል፡፡ እነዛ የህክምና
ባለሞያዎች እንደሚሉት ማንኛውም በሽታ ሲጀማምር ከታወቀ
በሽታውን ለመፈወስ በጣም ቀላል ነው፡፡ ሆኖም በሽታው
ሲጀምር ማወቅ በእጅጉ አዳጋች ነው፡፡ ከጊዜ በኋላ በሽታው
ካልታወቀና በእንጭጩ ካልተቀጨ በስተመጨረሻ በሽታው በመላ
አካላት ዙሪያ በስፋት ተንሰራፍቶ በቀላሉ የሚታይ ግን በቀላሉ
የማይፈወስ ከመሆን ደረጃ ይደርሳል፡፡

ፖለቲካም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ማንኛውም አይነት ፖለቲካዊ ቀውስ አስቀድሞ ከታወቀ በቀላሉ ሊፈታ ይችላል፡፡ (በርግጥ ችግሮችን አስቀድሞ የመተንበይ ብቃት ያላቸው አርቆ አሳቢ መሪዎች ብቻ ናቸው)። ችግሮቹ ቀድመው ካልታወቁ ግን በጊዜ ሂደት ለሁሉም ሰው ይፋ የሆኑ የአደባባይ ሚስጥሮችና መፍትሄ ለመስጠት የረፈደባቸው ጋሬጣዎች ይሆናሉ፡፡

እናም ሮማውያን ችግሮች ሲመጡ አስቀድመው በመመልከት አግባብነት ያለው ግብረ መልስና የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ችግሮቹን ለመፍታት ጦር መማዘዝ ቢኖርባቸው እንኳ ጦርነት ውስጥ ላለመግባት ብለው ችግሮቻቸውን ከመፍታት አይታቀቡም፡፡ ምክንያቱም ጦርነትን ማስተላለፍ እንጂ ማስወገድ እንደማይቻል ያውቃሉ፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ጠላት አቅሙን የሚገነባበት ፋታ ያገኛል፡፡ ከዚህም ባለፈ

ሮማውያን የዘመናችን ጠቢባን ሁሌም እንደሚሰብኩት በአሁን ላይ ማድረግ የሚችሉትን ያህል ለማድረግ ሳይሆን አስተውሏቸውና ጀግንነታቸው የፈቀደላቸውን ያህል ለመስራት ይሞክራሉ፡፡ ጊዜ ሁሉን ነገር ይዞ ይነጉዳልና፡፡ በርግጥ የጊዜ ሂደት በጎን ወይም ክፉን፣ ክፉን ወይም በጎን ይዞ ሊመጣ ይችላል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ በእንጥልጥል ወደተውናት ፈረንሳይ ተመልሰን ግዛት በማስፋፋቱ ሂደት ውስጥ ፈረንሳይ ከላይ የዘረዘርኳቸውን መርሆዎች ተከትላ እንደሆን እንይ፡፡ የፈረንሳዩ ንጉስ ሉዊ በጣሊያን የነበረውን ቆይታ በጥልቀት ከመረመርን ንጉሱ በእንግዳ አገር ውስጥ ግዛትን ጠብቆ ለማቆየት መደረግ ካለባቸው ነገሮች በተቃራኒ ሲያደርግ እንደቆየ እንመለከታለን፡፡

ንጉስ ሉዊ ወደ ጣሊያን ምድር ሰርጎ የገባው የሎምበርዲን ክፊል ግዛት የራሳቸው ለማድረግ በቋመጡት ቬኔዣውያን ጥሪ አማካኝነት ነበር፡፡ በበኩሌ ይህንን የንጉሱን እርምጃ አልኮንንም፡፡ ምክንያቱም ንጉሱ ወደ ጣሊያን ግዛቶች እግሩን ማስገባት ይፈልግ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በግዛቲቱ ውስጥ ምንም አይነት አጋር አልነበረውም፡፡ በተቃራኒው በቀዳሚው የፈረንሳይ ንጉስ ቻርልስ አፍራሽ ድርጊት የተነሳ የግዛቲቱ በሮች ሁሉ ለሉዊ ዝግ ነበሩ፡፡ ስለዚህ በግዛቲቱ ውስጥ ካለ ማንኛውም ሀይል ጋር ለመደራደር ዝግጁ መሆን ነበረበት፡፡ ከዚህም ባለፈ ይህ የሉዊ የመጀመሪያ እርምጃ ሌላ ስህተት ባያስከትል ኖሮ ትክክለኛና ስኬታማ ሊባል የሚችል ነበር፡፡ በርግጥ ሎምበርዲ በንጉሱ ቁጥጥር ስር ስትወድቅ ንጉስ ቻርልስ አጥቶት የነበረው የእድል በር ተከፈተለት፡፡ ጄኖዋ በቀላሉ ለንጉሱ እጅ ሰጠች፣

ፍሎረንሶች የንጉሱ አጋር ሆኑ፣ የማንቱዋው መኳንንት፣ የፌራራው መስፍን፣ ቤንቲቮግሊ፣ የፎርሊዋ መኳንንት፣ የፌንዛ፣ የፒሳሮ፣ የሪሚኒ፣ የካሜሪኖ፣ የፒዮምቢኖ ሀገረ ገዥዎች፣ የሉካ፣ ፒሳና የሲየና ነዋሪዎች ባጠቃላይ የንጉሱን ወዳጅነት አጥብቀው በመሻት ወደ እሱ መምጣት ጀመሩ፡፡ ይህን ጊዜ ንጉሱን ወደ ጣሊያን ግዛት የጎተቱት ቬኒሻውያን ምን ያህል ችኩል፣ ቀንድ ነካሽ እንደነበሩ ተረዱ፡፡ የሎምበርዲን ሁለት ከተሞች ለመያዝ ሲሉ ንጉሱን የጣሊያንን ሲሶ ባለቤት አድርገውት ነበር፡፡

አሁን ንጉሱ ከላይ የገለፅኳቸውን የአመራር መርሆች ተከትሎ አጋሮቹን በአስተማማኝ ሁኔታ ጠብቆ ማቆየት ቢችል ኖሮ በጥቂት ተግዳሮት ብቻ በመላዋ የጣሊያን ግዛት ላይ ሀያል ሆኖ መቆየት በቻለ ነበር፡፡ በዙሪያው በቤተክርስቲያኑና በቬኒሻውያን ሀያልነት የተዳከሙና የተጎሳቆሉ፣ በስሩ ለመሆን የሚፈቅዱ በርካታ አቅም አልባ ግዛቶች ነበሩ፡፡ እነዚህን ግዛቶች በመጠቀም ንጉሱ በዙሪያው ካሉ ሀያላን እራሱን በቀላሉ መከላከል ይችል ነበር፡፡

ንጉስ ሉዊ ግን ያደረገው ተቃራኒውን ነው፡፡ በቅድሚያ የሮማው ጳጳስ አሌክሳንደር የሮማኛን ግዛት በቁጥጥሩ ስር እንዲያውል ረዳ፡፡ እንደዚህ አይነቱን የተሳሳተ ውሳኔ ሲወስን ንጉሱ ሌላውን ሀያል በማድረግ እራሱን እያዳከመ፣ እራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ አጋሮቹን እያሸሸ እንደሆነ ልብ አላለም፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ ቀድሞውኑ ከተጎናጸፈችው መንፈሳዊ ሀይል በተጨማሪ ገደብ የለሽ ጥንካሬና ስልጣን እየሰጣት እንደነበር አልተረዳም፡፡

ንጉሱ የመጀመሪያውን ስህተት በመፈጸሙ ሁለተኛውን ስህተት ለመድገም ተገደደ፡፡ የአሌክሳንደርን ስልጣን ለመገደብና ቱስካኒን ለመጠቅለል የሚያደርገውን ጉዞ ለማጨናገፍ ንጉሱ ራሱ በጣሊያን ግዛቶች ውስጥ ወረደ፡፡ ቤተክርስቲያኒቱን ሀያል ማድረጉና አጋሮቹን ማሸሹ ሳያንስ የኔፕልስን ግዛት የግሉ ለማድረግ በማሰብ ከስፔይን ጋር ተቀራመታት፡፡ መጀመሪያ ንጉሱ በጣሊያን ግዛት ውስጥ ያለ ብቸኛ ሀያል ነበር፡፡ ስፔይንን ወደ ግዛቲቱ ሲጋብዝ ግን የተከፉትና በቀቢጸ ተስፋ የሚዋልሉትን ቀልብ የሚስብ ሌላ ተቀናቃኝ ሀይል በጣሊያን ግዛት ውስጥ ፈጠረ፡፡ ኔፕልስ ውስጥ ስፔይንን መጋበዝ ሳያስፈልግ ለርሱ አዳሪ የሆነ ሎሌ በመሾም ግዛቲቱን መቆጣጠር ሲችል ሎሌውን አፈናቅሎ ጊዜ ጠብቆ የሚያፈናቅለው ሀይል ከጉያው ተከለ፡፡

ተጨማሪን የመሻት ጉጉት የሰው ልጅ የተለመደና ፍጹም ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው፡፡ ይህን ፍላጎታቸውን ማሟላት የቻሉቱ ከመወገዝ ይልቅ መወደስ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት አቅም ሲያጡና በማንኛውም አይነት መስዋዕትነት ተጨማሪን የመሻት ጉጉታቸውን ለማሟላት ሲጥሩ ለስህተታቸው ውግዘት ይገባቸዋል፡፡

ፈረንሳይ ኔፕልስን በራሷ ሀይል ብታጠቃ ባይወገዝ እንኳ ከሌላ ሀይል ጋር መቀራመቷ አግባብነት አልነበረውም፡፡ ሎምባርዲን ከቬኒሻውያን ጋር መቀራመቷ ወደ ጣሊያን ግዛት እግሯን ለማስገባት የሚረዳ መሰረተ ድንጋይ በመሆኑ በይቅርታ ሊታለፍ ቢችልም በኔፕልስ የወሰደችው እርምጃ ግን ሊወገዝ ይገባል፡፡ ምክንያቱም አስፈላጊ አልነበረም፡፡

በመሆኑም ጠቅለል ባለ መልኩ የፈረንሳዩ ንጉስ ሉዊ አምስቱን መሰረታዊ ስህተቶች ሰርቷል ለማለት እንችላለን፡፡ አቅም አልባ የሆኑ ግዛቶችን አጥፍቷል፣ በጣሊያን ውስጥ ቀድሞውን ሀያል የነበረን ግዛት ሀያልነት አጠናክሯል፣ በግዛቱ ውስጥ ሀያል የሆነ የውጪ ሰርጎ ገብ ፈጥሯል፣ ከጣሊያን ግዛቶች ወጥቷል፣ የሰፈራ መንደሮችን መገንባት ተስኖታል፡፡

እነዚህ ሁሉ ስህተቶች እንደተጠበቁ ሆነው እንኳን ንጉሱ ሌላ ስድስተኛ ጥፋት ባያክልባቸው ኖሮ ለከፋ ጉዳት የሚዳርጉ ባልሆኑ ነበር፡፡ ሆኖም ንጉሱ ቬኒሻውያንን ከግዛታቸው በመመንገል በስህተቶቹ ላይ ሌላ ድርብ ስህተት ፈፀመ፡፡ ቤተክርስትያኗን ሀያል ባያደርግ ወይም የስፔይንን ሀይል ወደ ጣሊያን ባያመጣ ኖሮ ቬኒሻውያንን መደምሰስ ትክክለኛና አስፈላጊ እርምጃ ሆኖ ሊገኝ ይችል ነበር፡፡ ሆኖም የቤተ ክርስትያኑና የስፔይናውያን ሀያል ተቀናቃኝነት በነገሰበት ቬኒሻውያንን ማውደም ተገቢ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የቬኒሻውያን ጥንካሬ ሁለቱ ሀይሎች ወደ ሎምበርዲ እንዳይዘልቁ ለማገድ ይረዳ ነበር፡፡ ፈረንሳይንና ቬኒሻን ተላልፎ ሎምበርዲን የመቆጣጠር ድፍረት አይኖራቸውም ነበር፡፡

ንጉስ ሉዊ ሮማኛን ለአሌክሳንደር፣ ኔፕልስን ለስፔይን አሳልፎ የሰጠው ጦርነት ውስጥ ላለመግባት ብሎ ነው የሚል አስተሳሰብ ያለው ሰው ካለ የእኔ ምላሽ አስቀድሜ እንደገለጽኩት ጦርነትን ለመሸሽ ብሎ ይዞታን ማቃወስ በምንም መመዘኛ አግባብነት አይኖረውም የሚል ይሆናል፡፡ ደግሞም ጦርነትን ማስወገድ አይቻልም - በራስ ጉዳት ቁርጦ በይደር ማስተላለፍ እንጂ፡፡ ንጉሱ ግዛቱን ለጳጳሱ የሰጠው ለእምነቱ የሚኖር በመሆኑ

ቃሉን ለመጠበቅና ውለታውን ለመመለስ ብሎ ነው በሚል እርምጃውን የሚደግፍ ካለም የእኔ ምላሽ የሚሆነው በኋላ ላይ በልኡላን እምነትና ቃላቸውን በመጠበቅ አግባብ ዙሪያ የማስቀምጠው መጠነ ሰፊ ዳሰሳ ይሆናል፡፡

በመሆኑም ንጉስ ሉዊ ሎምበርዲን ያጣው ግዛቶችን በመቆጣጠርና በቁርጠኝነት በማቆየት ጨዋታ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሀይሎች ከሚከተሏቸው ህግጋት ውስጥ አንዱንም መከተል ባለመቻሉ ነው፡፡ ይህ የተጋነነ ሀቅ አይደለም፤ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ምክንያታዊ እውነት ነው፡፡ ቄሳር ቦርጂያ ሮማኛን ሲቆጣጠር በዚህ ጉዳይ ላይ ከሮዌን ጋር ተነጋግሬ ነበር፡፡ ሊቀ ጳጳሱ “ጣሊያናውያን ጦርነትን አያውቁም” ሲሉኝ፣ እኔ ደግሞ “ፈረንሳውያን የአገዛዝ ጥበብን አያውቁም” ስል ተግሳጼን አሰምቻቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም እውቀቱ ቢኖራቸው ኖሮ ቤተ ክርስቲያኗ ይህን ያህል ሀያል እንድትሆን ባላደረጉ ነበር፡፡ በጣሊያን ውስጥ የተከናወኑ ክስተቶች እንዴት የቤተ ክርስትያኗና የስፔይን ታላቅነት በፈረንሳይ አማካኝነት እንደተከሰተና እንዴት የፈረንሳይም ውድቀት በነዚህ ሁለት ሀይሎች እንደተፋጠነ በሚገባ ያመላክታሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት አንድ መቼም ሊፋለስ የማይችል ህግ ማርቀቅ እንችላለን፡- ለሌሎች ሀያልነት መንስኤ የሚሆን ማንኛውም ሀይል የራሱን ውድቀት ያፋጥናል፡፡ ምክንያቱም ይህ ሀያልነት እውን ሊሆን የሚችለው አንድም በብልሃት አሊያም በሀይል ነው፡፡ ሁለቱም ነገሮች በሀያልነት ጎዳና ላይ ላለ ጋሬጣዎች ናቸው፡፡

## 4. በአሌክሳንደር ቁጥጥር ስር የነበረው የዳሪስ ግዛት ስለምን በአሌክሳንደር ተተኪዎች ላይ አላመጸም?

የግዛት ማስፋፋትና ስልጣንን ጠብቆ የማቆየት ሂደት ምን ያህል አዳጋች እንደሆነ ለተመለከተ ታላቁ አሌክሳንደር እንዴት በጥቂት አመታት ውስጥ የመላዋ ኤስያ ገዢ መሆን እንደቻለ፣ ግዛት የማስፋፋት ተልዕኮውን በድል ከመወጣት አፋፍ ደርሰ ሲሞት፣ በሁሉም ሰው ዘንድ እንደሚጠበቀው አሌክሳንደር በመሰረተው ታላቅና ሰፊ ግዛት ውስጥ ሁለገብ አመጽ አለመቀጣጠሉ በእጅጉ ሊያስገርም ይችላል፡፡ በተቃራኒው የአሌክሳንደር ተተኪዎች የወረሱትን ግዛት አስተማማኝ በሆነ መንገድ ማቆየት ችለው ነበር፡፡ የአሌክሳንደር ተተኪዎች በፈጠሩት አመራር ውስጥ የነበረው ብቸኛ እንቅፋት በመካከላቸው የፈጠሩት የእርስ በርስ የስልጣን ሽኩቻ ነበር፡፡

በታሪክ ውስጥ የሚወሱ ግዛቶች ባጠቃላይ የሚተዳደሩት ከሁለት መንገዶች በአንዱ ነው፡፡ አንድም በሁሉም ሰው ዘንድ የበላይ በሆነ፣ በራሱ ግላዊ ይሁንታና ፈቃድ የሚመራ ካቢኔ ባለው ፈላጭ ቆራጭ ልኡል አሊያም ስልጣናቸው በልኡሉ ቁጥጥር በማይገደብ ሲወርድ ሲዋረስ በመጣ የዘር ሀረግ የሚወሰን መሳፍንትና ልኡል የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ መሳፍንት የየራሳቸው የሆነ ግዛትና እነሱን ብቻ የሚገዛ ታማኝ ሎሌ ያካበቱ ናቸው፡፡

በአንድ ልኡልና በልኡሉ ተገዢ ሎሌዎች በሚተዳደር ግዛት ውስጥ የግዛቱ ሀያል ስልጣን የልኡሉ ብቻ ይሆናል፡፡

በመላ ግዛቱ ውስጥ ከልኡሉ ያለፈ ተቀባይነት ያለው አካል አይኖርም።

ሁለቱን የተለያዩ የአስተዳደር አካሄዶች የሚያሳዩን አይነተኛ ምሳሌዎች ከቱርክና ፈረንሳይ መንግስታት መረዳት ይቻላል። የቱርክ ግዛት የሚመራው በአንድ ሰው ነው። የተቀሩት ባለስልጣናት ባጠቃላይ የርሱ ታዛዥ፣ ተገዥ ሎሌዎች ናቸው። ብቸኛው መሪያቸው ግዛቲቱን ወደ ተለያዩ ክፍለ ግዛቶች በመከፋፈል ያሻውን አስተዳዳሪ ይሾማል፣ በፈለገው ጊዜ የሾመውን ይሽራል።

ከዚህ በተቃራኒ የፈረንሳይ ንጉስ በተለያዩ ግዛቶች ውስጥ ለረዥም ዘመን ራሳቸውን አደላድለው፣ የራሳቸውን ታማኝ ሎሌና ተከታይ አፍርተው በሚኖሩ መሳፍንት የተከበበ ነው። ሁሉም የየራሳቸው የሆነ የስልጣን ኬላ አላቸው። ንጉሱ በራሱ ላይ ካልቆረጠ በስተቀር ኬላቸውን መንጠቅ አይችልም።

በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ስናነጻጽር የቱርክን አይነት ግዛት በቀላሉ ረትቶ መቆጣጠር በእጅጉ አዳጋች ሲሆን አንድ ጊዜ ግዛቱን መርታት ከተቻለ ግን ስልጣንን በቀላሉ ጠብቆ ማቆየት ይቻላል። የፈረንሳይ ግዛት በአንጻሩ በቀላሉ ሊወረርና በቁጥጥር ስር ሊውል ቢችልም ግዛቱን ጠብቆ ማቆየት በእጅጉ አዳጋች ነው።

የቱርክን ግዛት መቆጣጠር አዳጋች የሚሆነው በግዛቱ ውስጥ ከውጫዊ ሀይሎች ጋር ለማሴርና ለመተባበር የሚፈቅዱ ውስጣዊ ተቀናቃኞችን ማግኘት ከባድ ስለሚሆን ነው። የልኡሉ

ሎሌዎች በታማኝነት የተሳሰሩ ባሪያዎች በመሆናቸው ለውጫዊ ሀይል ማደር ይሳናቸዋል፡፡ በልኡሉ ላይ ለማሴርና ከውጫዊ ሀይሎች ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ ቢሆኑ እንኳን በልኡሉ ላይ የሚነሳ የራሳቸው ተከታይ ስለሌላቸው የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ጉልህ የሚባል አይሆንም፡፡ በመሆኑም ቱርክን ለማጥቃት የሚነሳ ማንኛውም ሀይል የግዛቲቱን ህብርና አንድነት ከቅድመ ግንዛቤ ከቶና ውስጣዊ ክፍፍልን ከመተማመን ይልቅ ድል የመንሳት ተስፋውን በራሱ ጥንካሬ ላይ ጥሎ መሆን ይኖርበታል፡፡ አንድ ጊዜ የልኡሉን ሀይል መደምሰስ ከቻለ ግን ሌላ አሳሳቢ ሀይል አይነሳበትም፡፡ ከገዢው ቤተሰቦች በቀር ሌላ የሚፈራው ሀይል ሊኖር አይገባም፡፡ እነሱንም አንዴ ይህን መመንገል ከቻለ ሌላ የሚያስፈራው ነገር አይኖርም፡፡ ምክንያቱም የተቀሩት ሀይሎች የህዝቡ ተቀባይነትና አመኔታ የላቸውም፡፡ አሸናፊው ድል ከማድረጉ በፊት በውስጣዊ ሀይሎች መተማመን እንደሌለበት ሁሉ ድል ካደረገም በኋላ ውስጣዊ ሀይሎችን መፍራት አይኖርበትም፡፡

በፈረንሳይ አይነት አስተዳደሮች ውስጥ የሚከሰተው ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ፈረንሳይን ለመውረር አንዱን የመኳንንት ዘር መያዝ በቂ ነው፡፡ ደግሞም ሁሌም የተማረሩ ወይም የለውጥ ጥማት ያደረባቸው መኳንንትን ማግኘት አይከብድም፡፡ በዚህ የተነሳ ለውጥ ፈላጊዎቹ መሳፍንት በራቸውን በመክፈት ድልህን ሊያቀጣጥሉት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ግዛቲቱን በቁጥጥርህ ስር ካዋልክ በኋላ ስልጣንህን ጠብቀህ ለማቆየት በምታደርገው ትግል ከተባባሪዎችህም ሆነ ከተደምሳሾቹ በኩል ለቁጥር የሚያታክቱ መሰናክሎች ያጋጥሙሀል፡፡ በንደዚህ አይነቱ ግዛት

ውስጥ ስልጣንህን ለማደላደል የገገርውን ቤተሰቦች ማጥፋት ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አሁንም አመጽ ሊያቀጣጥሉ የሚችሉ በርካታ መሳፍንት አሉ፡፡ ፍላጎታቸውን ለማርካትም ሆነ ከነአካቴው ድምጥማጣቸውን ለማጥፋት ብትሞክር ምቹ አጋጣሚ ባገኙ ቅጽበት ግዛቱን መነጠቅህ አይቀርም፡፡

ከዚህ በመነሳት ዳሪዮስ ይከተለው የነበረውን የአስተዳደር ስርአት ስንመለከት ከቱርክ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም አሌክሳንደር የዳሪዮስን ግዛት ለመቆጣጠር ዳሪዮስን ከጦር ሜዳ ማባረርና ከመንበሩ መመንገል ነበረበት፡፡ በዳሪዮስ ላይ ድልን ከተቀናጀ፣ ዳሪዮስ ከሞተ በኋላ መላ ግዛቱ በአስተማማኝ ሁኔታ በአሌክሳንደር መዳፍ ውስጥ ወደቀ፡፡ የአሌክሳንደር ተተኪዎች ህብረት ቢኖራቸው ኖሮ ያለምንም ረብሻና ስጋት በዳሪዮስ ግዛት ውስጥ ለረዥም ዘመን ተደስተው መኖሩ በቻሉ ነበር፡፡ የአሌክስንደር ተተኪዎች በራሳቸው የስልጣን ሽኩቻ ከሚቀሰቅሱት ሁከት በስተቀር ምንም አይነት ረብሻ አይፈጠርም ነበር፡፡

ነገር ግን በፈረንሳይ መልኩ የተዋቀሩ ግዛቶችን በቀላሉ ማስተዳደር በእጅጉ አዳጋች ነው፡፡ ይህ እውነት ሮማውያን ስፔይንን፣ ፈረንሳይንና ግሪክን በሚገዙበት ወቅት በየጊዜው ለሚከሰቱባቸው በርካታ አመፆች መሰረት ነበር፡፡ ሮማውያን ሁል ጊዜ በይዞታቸው ስለማይተማመኑ ይዞታቸውን ለማስጠበቅ ይቸገሩ ነበር፡፡ ሆኖም የሮማውያን አገዛዝ ጥብቅና ስር የሰደደ ሃያል ሲሆንና ግዛቶቹ ሙሉ ለሙሉ ፈፅመው ሲረሱ ሮማውያኑ አቋማቸውን ማጠናከርና አገዛዛቸውን ማረጋገጥ ችለው ነበር፡፡

ይህም ሆኖ በኋላ ላይ ሮማውያን እርስ በርሳቸው መሻኮት ሲጀምሩ ሁሉም በየፊናቸው ከተገገርዎቹ ግዛቶች በስልጣናቸው ልክ የየራሳቸው ደጋፊ ያገኙ ነበር።

ይህ እውነታ ከግንዘቤ ሲገባ አሌክሳንደር ኤስያን በቀላሉ ተቆጣጥሮ ማቆየቱ ወይም ፓይራስንና የመሳሰሉት ሌሎች ገዢዎች ግዛቶቻቸውን ጠብቀው ለማቆየት በእጅጉ መቸገራቸው አያስገርምም። ይህ አይነቱ ልዩነት የሚከሰተው ገዢዎች ጠንካራ በመሆናቸውና ባለመሆናቸው ብቻ አይደለም። ልዩነቱ የሚከሰተው በሚመሩት ግዛት የአገዛዝ ልማድ መለያየት አማካኝነትም ጭምር ነው።

## 5. በራሳቸው ህግጋት የሚመሩ ግዛቶች

አንዳንድ አዳዲስ ግዛቶች በራሳቸው ህግጋት የሚተዳደሩ ወይም በነጻነት ከመኖር ብሂል ጋር የተላመዱ ሆነው ሲገኙ እንዲህ አይነቶቹን ግዛቶች በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚረዱ ሶስት መንገዶች አሉ። አንድም ግዛቶቹን ሙሉ ለሙሉ በመደምሰስ ወይም በአካል ተገኝቶ በማስተዳደር ካልሆነም ግዛቲቱን የሚያመቻች አምባገነን መንግስት በመሾም በራሳቸው ህግ እንዲመሩና፣ ግብር እንዲገብሩ በማድረግ ግዛቶቹን ማስተዳደር ይቻላል።

በሶስተኛው መንገድ ውስጥ የሚሾመው አምባገነን መንግስት ከመስራቹ ልኡል ሀይልና አጋርነት (እርዳታ) ተነጥሎ መኖር እንደማይችል ስለሚገነዘብ ህልውናውን ጠብቆ ለማቆየት

አገልጋይነቱን ለማረጋገጥ ይገደዳል፡፡ ነጻነትን የለመዱ ግዛቶች ግን በራሳቸው ዜጋ ቢመሩ የቀለለ ይሆናል - ልኡሉ ግዛቱን የመደምሰስ ሀሳብ ከሌለው በስተቀር፡፡

የስፓርታና የሮማውያን አገዛዝ ከላይ የተጠቀሱትን የአስተዳደር አይነቶች ለማሳየት ሁነኛ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ስፓርታውያን የራሳቸውን አምባገነን በአቴንስ እና ቴቤስ ውስጥ በመሾም ግዛቶቹን ለመግዛት ጥረት አድርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ በስተመጨረሻ ሁለቱንም ግዛቶች ከማጣት አልዳኑም፡፡ ሮማውያን በአንጻሩ ካፑዋን፣ ካርቴጅንና ኑሜንሻን ሲያስተዳድሩ በቅድሚያ ግዛቶቹን አውድመዋቸዋል፡፡ በመሆኑም ለረዥም ዘመን ከመዳፋቸው አላመለጡም፡፡ በርግጥ መጀመሪያ ላይ ሮማውያን የግሪክ ግዛቶችን ለማስተዳደር ስፓርታውያን እንዳደረጉት በነጻነትና በራሳቸው ህግጋት ሊያስተዳድሯቸው ሞክረው ነበር፤ ግን አልተሳካላቸውም፡፡ ስለሆነም ስልጣናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ በግሪክ ውስጥ የነበሩ በርካታ ከተሞችን ለማጥፋት ተገደዋል፡፡

በርግጥ አንድን ግዛት በሚገባ ለመቆጣጠር ግዛቱን መደምሰስን የመሰለ አስተማማኝ መፍትሄ የለም፡፡ ነጻነትን የተላመዱ ግዛቶችን ሲቆጣጠር ነባር ተቋማቱን የማይደመስስ ገዢ፣ የሆነ ቀን እሱ ራሱ መጥፋቱ እንደማይቀር ልብ ሊል ይገባል፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ አይነት ግዛቶች አመጽ ባነሱ ቁጥር የጥንት ተቋማትንና የነጻነትን ስም በመፈክርነት እንግበው ነው፡፡ የፈለገውን ያህል ጊዜ ቢያልፍ፣ የፈለገውን ያህል ጥቅማ ጥቅም ቢሰፈር ዜጎች የቀድሞ ነጻነታቸውንና ጥንታዊ ተቋማትን አይረሱም፡፡ ገዢው ያሻውን ያህል አርቆ አሳቢና ብርቱ ቢሆን

ኗሪዎቹ እስካልተዳከሙና እስካልተበታተኑ ድረስ እድል በሯን በከፈተችላቸው ቅጽበት 'ሆ' ብለው መነሳታቸው አይቀሬ ነው . ልክ ፒሳ ለአንድ መቶ አመታት በፍሎረንስ ስትገዛ ቆይታ እንዳፈነገጠችው።

ሆኖም በአንድ ልኡል ሲገዙ የቆዩ ግዛቶች ልኡሉና መላ ቤተሰቡ ሲደመሰስ፣ በአንድ በኩል በልኡል መገዛትን ስለለመዱና በሌላ በኩል ደግሞ የቀድሞ ልኡላቸውን በማጣታቸው ከመካከላቸው አዲስ ልኡል ለመምረጥ ከስምምነት መድረስ ስለሚሳናቸው ያለመሪ በነጻነት መኖር ይቸግራቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳ ነፍጥ ለማንገብ ጊዜ ይፈጅባቸዋል፡፡ ይህ ሲሆን አንድ መስፍን (ገዢ) በቀላሉ ሊረታቸውና ያለ ብዙ ውጣ ውረድ ሊገዛቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ክስተት በህዝባዊ መንግስታት ውስጥ ሲሆን ይበልጥ መነቃቃት ይኖራል፡፡ ላቅ ያለ የጥላቻና የበቀል ጥም ይፈጠራል፡፡ ምክንያቱም የድሮው ነጻነታቸው ትዝታ ዝም እንዲሉ አያስችላቸውም። በተለይ ስቅታው እረፍት አይሰጣቸውም፡፡ ይህን ጊዜ አስተማማኝ የሚሆነው መንገድ እነሱን ከስረ መሰረታቸው መመንገል ወይም እዛው እመሃከላቸው በቅርበት በአካል ተገኝቶ መግዛት ነው፡፡

## 6. በገዛ ራስ ጦርና

## በገዛ ራስ ጀግንነት የሚመሰረቱ ግዛቶች

አዳዲስ ግዛቶችን የሚመሰርቱ አዳዲስ ልኡላንን በተመለከተ የማቀርባቸው አስረጂዎች የምድራችን ታላላቅ ባለታሪኮች በመሆናቸው የተጋነነ አግራሞት ባያጭሩ እመኛለሁ፡፡

ሰዎች ሁሌም የሌሎችን ፈለግ እየተከተሉ አርአያዎቻቸውን ለመምሰል በመሞከር ህይወታቸውን ይመራሉ፡፡ ይሁን እንጂ የአርአያዎቻቸውን ፈለግ ሙሉ ለሙሉ መከተልም ሆነ ጀግንነታቸውን እውን ማድረግ አይችሉም፡፡ ይህም ሆኖ ግን ማንም አስተዋይ የሆነ ሰው የታላላቅ ሰዎችን ዱካ መከተል ይኖርበታል፡፡ የራሱ ጀግንነት ከአርአያዎቹ ሃይል ጋር ተመጣጣኝ ባይሆን እንኳ ታላቅ የመሆን ፍላጎት በራሱ የታላቅነት መንፈስ አለው፡፡ የታላላቅ ሰዎችን ፈለግ ለመከተል የሚሞክር ሰው እንደ ብርቱ ቀስተኛ ነው፡፡ ኢላማው በጣም ሩቅ መሆኑ ሲታወቅ የተካነ ቀስተኛ የቀስቱን አቅም በማመዛዘን፣ አካባቢውን በትክክል በማለም ሳይሆን ከአካባቢው ከፍ አድርጎ በማነጣጠርና ቀስቱን አርቆ በመወርወር ኢላማው ጋር ለማድረስ ይሞክራል፡፡

ሙሉ ለሙሉ አዲስ ግዛት የሚመሰርት አዲስ ልኡልም በትረ ስልጣኑን ጠብቆ ለማቆየት በሚያደርገው ተጋድሎ ውስጥ የሚያጋጥሙትን እንቅፋቶች የመወጣት እድሉ በልኡሉ ብቃት ልክ የሚወሰን ይሆናል፡፡ በርግጥ ከተራ ግለሰብነት ወደ ልኡልነት መድረስ በራሱ አንድም የልኡሉን እድለኝነት አሊያም ጀግንነት (ብቃት) የሚያመለክት እውነት ነው፡፡ ከሁለቱ አንዱ ደግሞ የልኡሉን እንቅፋቶች የማቅለል ሚና ይጫወታል፡፡ ሆኖም አንድ ሰው በእድል መመካቱ በቀነሰ ቁጥር የራሱን አቋም እያጠናከረ ይሄዳል፡፡

በእድል ወይም በሌሎች ችሮታ ሳይሆን በራሳቸው ብቃት ሀይልን መጨበጥ ከቻሉ ሀያላን ጥቂት ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ሙሴ፣ ሲይራስ፣ ሮሙለስ፣ ቴሲየስና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በርግጥ ሙሴ እግዚአብሄር ያዘዘውን የሚተገብር ብቻ በመሆኑ ጥያቄን ሊያጭር ቢችልም ከእግዚአብሄር ጋር ለመነጋገር የሚያበቃ ግርማ ሞገስ መላበስ መቻሉ በራሱ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስጠው ይገባል፡፡ ሲይራስንና የመሳሰሉ በራሳቸው ተጋድሎ ግዛታቸው ያስፋፉና ያስፋፉትን ግዛት ጠብቀው ለማቆየት የቻሉ ነገስታት ግን ሙሉ ውዳሴና ታላቅነት ይገባቸዋል፡፡ በርግጥ እርምጃቸውንና የገነቧቸውን ተቋማት ስናጤን ልእለ ሀያል በሆነ አምላክ ከሚመራው ሙሴ የማይተናነሱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ድርጊትና ህይወታቸውን ጠለቅ ብለን ስንመረምር ደግሞ የተፈጠረላቸውን ምቹ አጋጣሚ በአግባቡ ከመጠቀም ባለፈ ታላቅነታቸው በእድል ያልተገኘ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በርግጥ ምቹ አጋጣሚዎች ባይፈጠሩላቸው ኖሮ ጀግንነታቸው ብቻውን ዋጋ ባጣ ነበር፤ ጀግንነት የተላበሱ ባይሆኑ ኖሮም የተፈጠሩላቸው አጋጣሚዎች ባክነው በቀሩ ነበር፡፡

እስራኤላውያን ከባርነት ለማምለጥና፣ ሙሴን ለመከተል ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ፣ ሙሴ በግብጽ ውስጥ በግብጻውያን በባርነትና በጭቆና ተይዘው ሊያገኛቸው ግድ ነበር፡፡ ሮሙለስ የሮም መስራችና ንጉስ ለመሆን ልክ እንደተወለደ ለሞት አደጋ መጋለጥ፣ በኋላም አልባን ለቆ መሰደድ ነበረበት፡፡ ሲይራስ ታላቁን የፔርሺያ ግዛት ለመመስረት ፔርሻውያን በሜዲያውያን መንግሥት ላይ ማመጽ፣ ሜዲያውያንም በረዥም ዘመን ሰላም የተዳከሙ ለስላሳና ሴታ ሴት ሆነው መገኘት ነበረባቸው፡፡ ቴሲየስ አቴናውያንን ተዳክመውና ተበታትነው ባያገኛቸው ሃይሉን ማሳየት ባልቻለ ነበር፡፡

እነዚህ ሰዎች የተፈጠሩላቸው አጋጣሚዎች ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ ረድተዋቸዋል፡፡ ልዩ የሆነ የገዛ ራሳቸው ጀግንነት ደግሞ

የተፈጠሩላቸውን እጋጣሚዎች በአግባቡ ለመጠቀም እስችሏቸዋል:: በውጤቱም ግዛቶቻቸው ሊከበሩና ሊበለፅጉ ችለዋል::

በከፍተኛ ተጋድሎና መስዋዕትነት ስልጣንን የሚቀናጁ ገገርዎች ግዛቶቻቸውን በከባድ ፈተና ቢመሰርቱም፣ እንዴ የመሰረቱትን ግዛት ጠብቀው ለማቆየት ብዙም አይቸገሩም:: አዲስ ግዛት በመመስረት ሂደት ውስጥ ለሚያጋጥሟቸው ፈታኝ ችግሮች (እንቅፋቶች) መንስኤው ግዛትን ለመመስረትና ዙፋናቸውን ለማስጠበቅ አዳዲስ ህጎች ለማፅደቅና አዳዲስ ተቋማት ለመመስረት ግድ ሲሆንባቸው ነው:: በርግጥ የአንድን ሀገር ህገ-መንግስት እንደመለወጥ አዳጋች፣ በቀላሉ እውን የማይሆንና በአደጋ የተሞላ ሂደት የለም:: ህገ መንግስቱን ለመለወጥ የሚነሳው አካል በቀድሞው ስርአት ውስጥ ከበለጸጉ መደቦች ሁለንተናዊ ተቃርኖ ሲገጥመው፣ በአዲሱ ስርአት እንበለጽጋለን ብለው ከሚያስቡት ደግሞ ስስ ድጋፍ ይቸረው ይሆናል:: ደጋፊዎቹ በአንድ በኩል በቀድሞ ህግጋት የሚታገዙትን ተቀናቃኞቻቸውን ስለሚፈሩ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች በተሞክሮ ያላረጋገጡትን አዲስ ነገር በቀላሉ የማይቀበሉ ጠርጣራዎች በመሆናቸው ድጋፋቸው አስተማማኝ ሊባል የሚችል አይደለም:: በመሆኑም ለውጡን የሚጻረረው መደብ የሞት ሽረት ትንቅንቅ ሲገጥም፣ በተቃራኒው በኩል የሚኖረው ግብረ መልስ የተገደበ ይሆናል:: በዚህ የተነሳ ህገ መንግስቱን ለመለወጥ የተነሳሳው አካልና ወዳጆቹ ለውድቀት ሊዳረጉ ይችላሉ::

ይህን ጉዳይ በጥልቀት ለመዳሰስ ለውጥ አራማጆቹን በሁለት ክፍሎ መመልከት ያስፈልጋል:: አንዳንዶች በራሳቸው

ሀይል ለውጥ ለመፍጠር ሲንቀሳቀሱ አንዳንዶች በሌሎች ሀይል ላይ በመመርኮዝ ለውጥ ለመፍጠር ይንቀሳቀሳሉ። የመጀመሪያዎቹ አላማቸውን ከጫፍ ለማድረስ በራሳቸው አቅም የማስፈጸም ሀይል ሲኖራቸው፣ አንዳንዶቹ አላማቸውን የሚያሳኩት ሌሎችን በማሳመን ነው። በሌሎች ላይ ጥገኛ በመሆን አላማቸውን ለማሳካት የሚሞክሩቱ ምንንም ሳያሳኩ ለውድቀት ይዳረጋሉ። የራሳቸውን ሀይል ተጠቅመው አላማቸውን ማስፈጸም የሚችሉቱ ግን የመውደቅ እድላቸው ዝቅተኛ ነው። በዚህ የተነሳ ነው የታጠቁ ነብያት ድል ሲያደርጉ ያልታጠቁቱ ተቃራኒው የሚገጥማቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ህዝብ በተፈጥሮው ተለዋዋጭ ነው። ህዝብን ማሳመን ቀላል ቢሆንም በእምነቱ ማግኘት ግን በእጅጉ አዳጋች ነው። በመሆኑም ህዝብ በማያምንበት ወቅት በሀይል ማሳመን ይቻል ዘንድ ነገሮችን አስቀድሞ ማሰናዳት አስፈላጊ ነው። ሙሴ፣ ሲይራስ፣ ቴስዩስ እና ሮሙለስ የታጠቀ ሀይል ባይኖራቸው ኖሮ የገነቧቸውን ተቋማት ለረዥም ጊዜ አስከብረው መዝለቅ በተሳናቸው ነበር።

አላማቸውን ለማሳካት በርካታ መሰናክሎች የሚጋፈጡ ልኡላን በአደጋ የተከበበ አስቸጋሪ ፈተና የሚገጥማቸው አላማቸውን እውን በማድረጉ ሂደት ውስጥ ነው። ተቀናቃኞቻቸውን አጥፍተው፣ አላማቸውን አሳክተው ከበሬታን መጎናጸፍ የቻሉ ጊዜ ግን ያለምንም ስጋት በደስታና በሀያልነት ለረዥም ዘመን መንገስ ይችላሉ።

እዚህ ጋር ከላይ ካወሳኋቸው ታላላቅ መሪዎች ተጨማሪ ቀለል ያለ፣ ግን በጣም የላቀ ክብር ላላቸው ምሳሌ የሚሆን

ምሳሌ ማቅረብ እወዳለሁ፡፡ የሳይራኩዙ ሂየሮ ከተራ ግለሰብነት ተነስቶ የሳይራኩዝ ገገር መሆን የቻለ ሰው ነበር፡፡ ከላይ እንዳነሳኋቸው ታላላቅ መሪዎች ሁሉ ሂየሮም ስልጣኑን እውን ያደረገው በእድል ሳይሆን የተፈጠረለትን አጋጣሚ በአግባቡ በመጠቀም ነበር፡፡ የሳይራኩዝ ህዝቦች በከፍተኛ ጫና ውስጥ ወድቀው በሃይል ወደኋላ በተነዱ ጊዜ ጦራቸውን ይመራላቸው ዘንድ ሾሙት፡፡ ይህን መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ የልኡልነት ክብርን ተጎናጸፈ፡፡ ጀግንነቱ ወደር የለሽ ከመሆኑ የተነሳ የሂየሮን ግለ ታሪክ የዘገበ ጸሐፊ እንዳስቀመጠው «ሂየሮ ተራ ሰው እያለ እንኳን ሙሉ ለሙሉ የገገርነት ባህሪ የተላበሰ ነበር፡፡»

ሂየሮ ግዛቱንና ሀይሉን አስተማማኝ ለማድረግ የቀድሞውን ሚሊሺያ በትኖ አዲስ አዋቅሯል፣ የቀድሞ የጦር ጓዶቹን አስወግዶ አዳዲስ የጦር ጓደኞችን መስርቷል፡፡ ሂየሮ የራሱን ሰራዊት በማቋቋምና አዳዲስ አጋሮችን በማፍራት ፍላጎቱን ሁሉ እውን የሚያደርግበት ጠንካራ መሰረት መፍጠር ችሏል፡፡ በመሆኑም ዙፋኑን ለማግኘት በከፍተኛ ሁኔታ ጠንክሮ ታግሏል፣ ዙፋኑን ጠብቆ ለማቆየት ግን ትንሽዬ ጥረት በቂ ነበር፡፡

## 7. በዕድልና በውጭ ኃይሎች/በሌሎች እርዳታ የሚመሰረቱ ግዛቶች

በቀናኢ እጣ ፈንታ ወይም በንፁህ ዕድል ብቻ ወደ ስልጣን የሚወጡ ሰዎች በትረ ስልጣናቸውን የሚጨብጡት ከራሳቸው ብርቱ ትጋት በተቃራኒ በሁኔቶች ወይም በሌሎች ሀይላት በጎ

ፍቃድ አማካኝነት ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ወደ ስልጣን ለመወጣጣት የሚያደርጉትን በረራ ክንፍ እንዳለው ፍጥረት ቢጀምሩም ችግራቸው የሚከሰተው ለማረፍ ሲያኮበኩቡ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በገንዘብ ሀይል ወይም በሌሎች እርዳታ ስልጣን ለመጨበጥ በሚጥሩ ሰዎች ላይ በተደጋጋሚ ሲከሰት ተስተውሏል፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ ወታደሮችን በመደለል ከተራ ግለሰብነት ወደ ንጉስ ነገስትነት በተመነደጉ ሰዎችም ላይ ታይቷል፡፡

በእድል ወይም በሌሎች እርዳታ ግዛት የሚመሰርቱ መሪዎች ወደ ስልጣን ባወጧቸው ሀይሎች በጎ ፈቃድና እገዛ ላይ ጥገኛ ለመሆን ይገደዳሉ፡፡ ስለዚህም አካሄዳቸው ሁሉ በውዥንብርና ባለመረጋጋት የተሞላ ይሆናል፡፡ በዚህ መልኩ ወደ ዙፋን የሚወጡ ገዢዎች የተቆናጠጡትን ድንገተኛ መንበር በምን መልኩ ጠብቀው ማቆየት እንዳለባቸው አያውቁም፡፡ ቢያውቁም ጠብቀው ማቆየት አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ተገቢውን ክህሎትና ወኔ ካላካበቱ በቀር ተራ ግለሰቦች ህዝብን የመግዛት ችሎታ አይኖራቸውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ራሱን ለእነሱ አሳልፎ የሰጠ ታማኝና ጽኑ የሆነ የገዛ ራሳቸው ሰራዊት የላቸውም፡፡

በአንድ ጀምበር የሚመሰረት አስተዳደር፣ ያለተፈጥሮው በግድ ዕድገቱ እንዲፋጠን እንደተደረገ ማንኛውም ተፈጥሯዊ ያልሆነ ግኡዝ ነገር ስርና ትስስር ያንሰዋል፡፡ እናም የመጀመሪያውን መጥፎ አጋጣሚ በተጋፈጠ ቅጽበት ይወድማል፡፡ በድንገት የገገርነትን ክብር የተጎናጸፉ ሰዎች እድል ከመዳፋቸው የጣለችላቸውን ሀይል ጠብቀው ማቆየት የሚችሉበትን መንገድ በፍጥነት መማር እስካልቻሉ ድረስ ወዲያው መውደማቸው የማይቀር ነው፡፡

ግዛትን ለመመስረት የሚያስችሉትን ሁለት መንገዶች (እንድም በጀግንነት አሊያም በእድል) በስፋት ለማብራራት በእኔ ዘመን የነበሩትን ሁለት አይነተኛ ምሳሌዎች፣ ፍራንሲስኮ ስፎርዛና ቄሳር ቦርጂያን እንደ አስረጂ ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

ፍራንሲስኮ ስፎርዛ በትክክለኛው አቀጣጫ፣ በገዛ ራሱ ታላቅ ጀግንነት ከተራ ዜጋነት የሚላን ሀገረ ገዥ መሆን የቻለ ሰው ነው፡፡ ፍራንሲስኮ ስልጣኑን ያገኘው ማለቂያ የለሽ በሆነ ረዥም ትግልና ተጋድሎ ቢሆንም በከባድ ተጋድሎ ያገኘውን ሀይል ጠብቆ ለማቆየት ብዙም አልተቸገረም፡፡ ስልጣኑን ጠብቆ ለማቆየት ትንሽዬ ጥረት በቂው ነበረች፡፡ ከፍራንሲስኮ ስፎርዛ በተቃራኒ ቄሳር ቦርጂያ ግዛቱን መመስረት የቻለው በአባቱ እርዳታ በቀላሉ ሲሆን፣ የአባቱ ድጋፍ በተለየው ቅጽበትም ግዛቱን ተነጥቋል፡፡ ይህ የተከሰተው ግን ቄሳር ማንኛውም ጀግናና ብቁ የሆነ ልኡል ስልጣኑን ለማጠናከርና ጠብቆ ለማቆየት ሊያደርግ የሚችለውን ጥረት ሁሉ አድርጎ ነው፡፡

ከዚህ በፊት አስቀድሜ እንዳስቀመጥኩት የተለየ ጀግንነት ያለው ብርቱ የሚሰኝ መሪ ግዛቱን ከተቆጣጠረ በኋላ ግዛቱን ጠብቆ ለማቆየት የሚረዳው አስተማማኝ የስልጣን መሰረት ይገነባል፤ ያጠናክራል፡፡ ይህም ሆኖ ግን በዚህ ሂደት ውስጥ ስልጣኑንም ሆነ የግዛቱን መሰረት የሚንጥ አደጋ ሊከሰት ይችላል፡፡ የቄሳር ቦርጂያን አካሄድም ጠቅለል አድርገን ስንመለከት፣ በርግጥ ሀገረ ገዥው ለመጻኢው ጊዜ ጠንካራ መሰረቶችን እንደጣለ እንረዳለን፡፡ በቄሳር አድራጎት ላይ ሰፋ ያለ ዳሰሳ ባቀርብ ከመንዛዛት እንደማይቆጠርብኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ምክንያቱም አንድ ልኡል ከቄሳር ቦርጂያ ምግባርና

ድርጊት ከሚቀስመው የተሻለ የማቀርበው አማራጭ የለኝም፣ ምንም እንኳ እርሱ የጣለው የስልጣን መሰረት በእንጭጩ ቢቀጭም ይህ የእሱ ጥፋት ሊሆን አይችልም - ከቁጥጥር ውጪ ከሆነ የእድል ክፋት የመነጨ እንጂ፡፡

ጳጳስ አሌክሳንደር ስድስተኛ ልጁ ቄሳር ቦርጂያን ለማንገስ ሲጠነስስ እውን የሆኑና ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ተጨባጭና ከፍተኛ ችግሮች ተጋርጠውበት ነበር፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በቤተ ክርስቲያኗ ስር ከሚተዳደሩት ግዛቶች በቀር ሌላ ለልጁ የሚሰጠው ግዛት ማግኘት አልቻለም፡፡ ከቤተ ክርስቲያኗ ግዛቶች መካከል አንዱን ለልጁ ቢሰጥ ደግሞ የሚላንና የቬኒዣ መሳፍንት ሊስማሙ እንደማይችሉ ያውቃል፡፡ ፌንዚ እና ሪሚኒ ቀድሞውኑ በቬኒዣ ጥበቃ ስር ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እጠቀምበታለሁ ብሎ ተስፋ የጣለበት የጣሊያን ጦር ደግሞ የጳጳሱን ሃያልነት ለመፍራት በቂ ምክንያት ባላቸው በኦርሲኒና በኮሎና ሰዎች ቁጥጥር ስር ነበሩ፡፡

ስለዚህ ፍላጎቱን እውን ለማድረግ ያገኘው የተሻለ አማራጭ በግዛቶቹ ውስጥ ብጥብጥ በመፍጠርና ስርአት አልበኝነትን በማስፈን፣ መንግስቶቻቸውን ሁከት ውስጥ መጣልና ፀጥታ በማስጠበቅ ሰበብ ገብቶ የተወሰኑ ግዛቶችን መቆጣጠር ነበር፡፡ ይህ በንዲህ እንዳለ ቬኒዣውያን የፈረንሳይን ጦር ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ወደ ጣሊያን ግዛቶች ለማስገባት ሲያደፋፍሯቸው በመገኘታቸው፣ ጳጳሱ ምቹ አጋጣሚ ተፈጠረለት፡፡ ስለሆነም ጳጳሱ ፈረንሳይ ያደረገችውን ወረራ አለመቃወም ብቻ ሳይሆን ከዚህም ባሻገር የንጉስ ሉዊን የቀድሞ ጋብቻ በማፍረስ ወረራውን ያለምንም ይሉኝታ ይገፋ ዘንድ አመቻቸለት፡፡ ንጉስ ሉዊ

በቬኒሻውያን ድጋፍና በጳጳሱ በጎ ፍቃድ ሚላን ከመድረሱ፣ ጳጳስ አሌክሳንደር ለሮማኛ ዘመቻ የሚሆነውን የእርዳታ ጦር ከንጉሱ ተቀብሎ ነበር፡፡

ቄሳር ቦርጂያ በዚህ መልኩ በአባቱ ድጋፍ ሮማኛን ድል ረትቶ ኮሎናን ቢደመስስም ሁለት ነገሮች ስልጣኑን በይፋ ከማወጅና ግዛቱን ከማስፋፋት አግደውት ነበር፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የወታደሮቹ ታማኝነት አጠራጣሪ የነበረ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የፈረንሳይ ፖሊሲ ሀይሉን የሚገዳደር ሆነበት፡፡ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፣ ቄሳር ቦርጂያ ይጠቀምበት የነበረው ጦር የአርሲኒ ወታደሮች ስለነበር የርሱን ግዛት መስፋፋት ካለመሻት በመነጨ ብቻ ሳይሆን ያገኘውን ግዛት ለመንጠቅ ከነበራቸው ፍላጎት የተነሳ ቄሳርን ለመክዳት በቂ ምክንያት ነበራቸው፡፡ የፈረንሳዩ ንጉስ አቋምና ፍላጎትም ከኦርሲኒዎች ብዙ የተለየ አይመስልም፡፡ ቄሳር በሁለቱ ሀይሎች ላይ የነበረውን ጥርጣሬ የሚያረጋግጥ ተሞክሮም ነበረው፡፡ ፌንዛን ከተቆጣጠረ በኋላ ወደ ቦሎኛ ሲዘምት የኦርሲኒ ወታደሮች ወደ ጦር ሜዳው የገቡት በግማሽ ልብ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ንጉሱን በተመለከተ ደግሞ አርቢኖን ተቆጣጥሮ ወደ ቱስካኒ ሲገሰግስ ንጉሱ ከመሀል ሜዳ መልሶታል፡፡

ስለዚህም ቄሳር ቦርጂያ በሌሎች ጦር ሀይልና እገዛ መተማመን እንደሌለበት ተረድቷል፡፡ ከዚህ በመነሳት በመጀመሪያ በሮም ውስጥ የኦርሲኒና የኮሎኛ አንጃዎችን ማዳከምና ሀይላቸውን መሸርሸር ጀመረ፡፡ የከፍተኛ መደብ (መኳንንትና መሳፍንት) የሆኑትን ታማኞቻቸውን ስልጣን፣ ጎበና ለደረጃቸው የሚመጥን ክብር በመስጠት በመካከላቸው ክፍፍል

ፈጠረ፡፡ በጥቂት ወራት ውስጥ በሮም የነበሩት አንጃዎች የእሱ ታማኝና የእሱ ተከታይ አደረጋቸው፡፡ ኮሎኛዎችን በታትኖ ከጨረሰ በኋላ የኦርሲኒ መሪዎችን ለማጥፋት አደባባ እንዲጋጣሚም ምቹ እድል ተፈጠረለት፡፡

ኦርሲኒዎች የጳጳሱ ጉልበት ማየልና የቄሳር መስፋፋት የራሳቸውን ውድቀት እያፋጠነው እንደሆነ ዘግይተውም ቢሆን ደረሱበት፡፡ በመሆኑም ከፔሩዥያ አቅራቢያ ማጊዮኔ ላይ ጉባኤ ጠሩ። ከዚህ ስብሰባ የኦርቢኖ ማመፅ በሮማኛ ላይ አመፅ ቀሰቀሰ፡፡ ቄሳር በፈረንሳይ እርዳታ አመጹን ደመሰሰ፡፡ በጣሊያን ውስጥ የነበረው የቀድሞ አቋምም ተመለሰ፡፡

ይህም ሆኖ ግን በፈረንሳይም ሆነ በሌላ የውጭ ሀይል መተማመን እንደማይችል ስለሚያውቅ ከጥገኝነት ለመላቀቅ የራሱን የማታለያ ስልት መንደፍ ያዘ፡፡ የማታለያ ስልቱ ሀያል በመሆኑ ኦርሲኒዎችም ሳይቀሩ በሲኞር ፓውሎ አማካይነት እርቅ ለማውረድ መጣር ጀመሩ፡፡ ቄሳር የተቻለውን ያህል ማንኛውንም ዲፕሎማሲያዊ ዘዴ በመጠቀም፣ ገንዘብና የተለያዩ ስጦታዎችን በማበርከት ፓውሎን በቁጥጥሩ ስር አውሎ የኦርሲኒን ርዝራዦች ሲኒጋግሊያ ላይ የወጥመዱ ሰለባ አደረጋቸው፡፡ የኦርሲኒ መሪዎች ሲወገዱ ተከታዮቻቸው ወደ ቄሳር ካምፕ ለመከተት ተገደዱ፡፡ በዚህም ቄሳር ቦርጂያ የወደ ፊት ሀይሉን ለማደላደል ጠንካራ መሰረት ጣለ፡፡ መላዋን ሮማኛ ያለምንም ተቀናቃኝ በቁጥጥሩ ስር ከማዋልም ባለፈ የዜጎቿን ወዳጅነትና አመኔታ ማግኘት ቻለ፡፡ በርግጥ በቄሳር አገዛዝ ዜጎቿ መረጋጋትና መበልጸግ ጀምረው ነበር፡፡

ይህ ነጥብ ለበርካቶች ትምህርት የሚሰጥ በመሆኑ ጠለቅ ብለን ልንመለከተው ይገባል፡፡ ቄሳር ሮማኛን ከተቆጣጠረ በኋላ ግዛቲቱ ዜጎቻቸውን በአግባቡ ከማስተዳደር ይልቅ ያላግባብ በሚበዘብዟት መሪዎች ስትመራ እንደቆየች ተገነዘበ፡፡ መሪዎቿ አንድነትን ከማስፈን ይልቅ ስርአት አልበኝነትን ሲያስፋፉ ስለከረሙ ከተማዋ በሽፍቶች፣ በወንበዴዎች፣ በነጥቆ አዳሪዎችና በተለያዩ አንጃዎች ታምሳ፣ በህገ ወጥነት ተበጥብጣ ነበር፡፡ ይህንን የተመለከተው ቄሳር ከተማይቱ ውስጥ የተንሰራፋውን ህገወጥነት ለማፅዳትና ህዝቡን ለልኡላዊው ሀይል ተገዢ ለማድረግ ፈርጠም ያለ አመራር ማስፈን እንደሚያስፈልግ ተረዳ፡፡ ከዚህ በመነሳት ምህረት የለሹን ሬሚሮ ደ ኦርኮን ሙሉ ስልጣን ሰጥቶ በግዛቲቱ ላይ ሾመው፡፡

በአጭር ጊዜ ውስጥ ሬሚሮ፣ ሮማኛን ከተዘፈቀችበት የስርአት አልበኝነት ማጥ አውጥቶ በከተማይቱ ላይ ሀይልና ታላቅ ከበሬታን ተጎናጸፈ፡፡ ቄሳር ይህንን ያህል የተንዛዛ ስልጣን መፍቀድ አስፈላጊ እንዳልሆነና ፈፅሞ ወደማይገታበት አቅጣጫ ሊያመራ እንደሚችል አስቀድሞ በማሰብ በማእከላዊው ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ከሁሉም ክልሎች የተውጣጣ በአንድ በታወቀ ብልህ ሰው ፕሬዝዳንትነት የሚመራ የህዝብ ምክር ቤት አቋቋመ፡፡

ያለፈው አመት የተፈፀሙት የእልቂትና የጭካኔ ተግባራት በህዝቡ ዘንድ ያተረፈለትንም ጥላቻ በመረዳት የህዝቡን ልብ ለማረቅና የእሱ ታማኝ ለማድረግ በግዛቱ ውስጥ የሚከሰት ማንኛውም አይነት ጭካኔ ያለርሱ እውቅና በበታች ሹማምንት እብሪት የሚፈጸም መሆኑን ማስነገር ጀመረ፡፡ ይህም ጥሩ ምክንያት ሆነና አንድ ቀን ጠዋት ፒያሳ አደባባይ ላይ የሬሚሮ

እካል ለሁለት ተቆርጦ ከጎኑ በደም ከጨቀየ ዱላና ስለት ጋር ወድቆ ተገኘ፡፡ ይህ በደም የጨቀየ ጭካኔ የሮማኛን ህዝብ በድንጋጤም በደስታም አደነዘዘው፡፡

በአንድ በኩል የራሱን ሰራዊት በማደርጀትና በሌላ በኩል አደጋ ሊያደርሱበት የሚችሉ ተቀናቃኞቹን በማስወገድ ከዚህ ሁሉ ጉዞ በኋላ የሮማኛው መስፍን ስልጣኑን ማረጋገጥ ቻለ፡፡

ቄሳር ቦርጂያ የግዛት ማስፋፋት ሂደቱን መቀጠል የፖሊሲውን ግድፈት ዘግይቶ የተረዳውን የፈረንሳይ ንጉስ የሚያስቆጣ መሆኑን ስለሚያውቅ መጠንቀቅ ነበረበት፡፡ ከዚህ በመነሳት የፈረንሳይ ሰራዊት ወደ ኔፐልስ ፊቱን ሲያዞር ቄሳር ከንጉሱ ተጽእኖ የሚላቀቅበትንና ሌላ አጋር የሚያፈራበትን መንገድ ማውጠንጠን ያዘ፡፡ ፍላጎቱ የስፔይንን ወዳጅነትና እርዳታ ማግኘት ነበር፡፡ በእርግጥ በመካከሉ አባቱ ጳጳስ አሌክሳንደር 6ተኛ ባይሞቱ እንደ አካሄዱ ብስለት ፍላጎቱን ማሳካት የሚሳነው አይመስልም ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ እርምጃዎች የሮማኛው ሀገረ ገዥ የቄሳር ቦርጂያ የቅርብ ጊዜ መርሀ ግብሮች ነበሩ፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ቄሳርን ያሳሰበው የነበረው አባቱን የሚተካው ቀጣዩ ጳጳስ የእሱ ተጻራሪ ሆኖ አባቱ የሰጠውን እንዳይነጥቀው ነበር፡፡ ይህንን ስጋቱን በአራት መንገድ ለመቅረፍም እቅድ ነበረው፡፡ አንደኛ ከዚህ ቀደም የመዘበራቸውን መሳፍንት ቤተሰቦች ርዝራዣቸውን ጨርሶ በማጥፋት ተተኪው ጳጳስ እነሱን ለራሱ ጥቅም እንዳያውላቸው ማገድ ነበር፡፡ ሁለተኛው በሮም ውስጥ የሚገኙ ፓትሪያርኮችን በስሩ ማድረግ ሲሆን ሶስተኛው እቅዱ ደግሞ

የሮማ ካርዲናሎች ማሰልጠኛ የሆነውን ኮሌጅ መቆጣጠር ነበር፡፡ የመጨረሻውና ዋንኛው መርህ ግብሩ ደግሞ አባቱ አሌክሳንደር ከመሞቱ አስቀድሞ የተቻለውን ሀይል መሰብሰብና ያለማንም እርዳታ በገዛ ራሱ ጦር በሁለት እግሮቹ መቆም ነበር፡፡

ከነዚህ አራት እቅዶቹ መካከል አሌክሳንደር በሞተ ጊዜ ሶስቱን ለማሳካት የቻለ ሲሆን አራተኛውን ለማሳካትም የቀረው ጥቂት እርምጃ ብቻ ነበር፡፡ በረዥም ጊዜ መርህ ግብሩ እንዳቀደው ማጥፋት ያለበትን ያህል በርካታ የመሳፍንት ቤተሰቦችን አጥፍቶ ያመለጡት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ፡፡ የሮማ ፓትሪያርኮች በእርሱ ስር የእሱ ደጋፊ አድርጓቸዋል፡፡ በካርዲናሎች ኮሌጅም ውስጥ በርካታ ተከታዮች ነበሩት፡፡ ሀይሉን በማስፋፋት ረገድ ቱስካኒን የመቆጣጠር እቅድ ነበረው፡፡ ፔሩጊያና ፒኦምቢኖን ተቆጣጥሯቸዋል፣ ፒሳም በርሱ ሞግዚትነት ስር የምትተዳደር ነበረች፡፡ ከፈረንሳይ ጫና ነጻ በመሆኑ (ፈረንሳይ ገና ድሮ ኔፕልስን በስፔይን በመነጠቋ ሁለቱም ወገኖች የእሱን ወዳጅነት ለማግኘት ይፎካከሩ ነበር) ፒሳን መጠቅለል ይችል ነበር፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሉካና ሲየና አንድም በፍሎረንቲናውያን ጥላቻ አንድም በፍራቻ ተገፍተው በቀላሉ እጅ ለመስጠት ይገደዱ ነበር፡፡ በዚህ አካሄድ ፍሎረንቲንም ከመዳፉ ትገባ ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ እቅዶች ቢሳኩለት (ኤሌክሳንደር በሞተ ጊዜ እንደተሳካለት) ወደር የለሽ ጥንካሬና ክብርን ይቀናጅ ነበር፡፡ ብቻውን መቆምና የማንም ድጋፍ ሳያስፈልገው በራሱ ሀይል መጽናት ይችል ነበር፡፡ ሆኖም አሌክሳንደር የሞተው ቄሳር ጦር ባነሳ በአምስት አመቱ ነበር፡፡ አሌክሳንደር ያለፈው ቄሳር

የሮማኛውን ስልጣን ጨብጦ ሌሎች ነገሮች ሁሉ በአየር ላይ እንደተንጠለጠለ፣ በሁለት ሀያላን ሀይሎች ተሰንን ከዚህም በከፋ የራሱ ጤና ተቃውሶ ነበር፡፡ ሆኖም ቄሳር ሰዎች አንድም ሙሉ ለሙሉ እጅ መስጠት አሊያም ሙሉ ለሙሉ መውደም አለባቸው ብሎ የሚያምን ደመ መራር ጀግና በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ የጣለው መሰረት በእጅጉ ጠንካራ ነበር፡፡ ጠሩ ውድቀቱን ባያፋጥንበት ወይም ጤንነቱ መልካም ቢሆን ኖሮ እያንዳንዱን እንቅፋት መሻገር ባልተሳነው ነበር፡፡ የጣለው መሰረት አስተማማኝ በመሆኑ ጤንነቱ ከህይወት ይልቅ ወደ ሞት ባጋደለበት ጊዜ እንኳን ሮማኛ ለወራት ያህል ጠብቃዋለች፡፡ ምህረት አልባ በመሆኑ ምንም እንኳ የባግሊዮኒ፣ የቪታሊና የኦርሲኒ ተቀናቃኝ አንጃዎች ወደ ግዛቱ ቢገቡም አላሳመጹበትም፡፡ የሚፈልገውን ሰው ጳጳስ አድርጎ መሾም ባይሳካለትም ቢያንስ ጵጵናው ወደማይፈልገው ሰው እንዳይሄድ ማድረግ ችሏል፡፡ አሌክሳንደር ሲሞት የርሱ ጤንነት ባይቃወስ ኖሮ ሁሉም ነገር ይቀልለት ነበር፡፡

ጁሊያስ 2ተኛ የተመረጠ ጊዜ ገጽ ለገጽ ስንገናኝ ቄሳር ራሱ አባቱ ሲሞት ሊከሰት የሚችለውን እያንዳንዱን ችግር ቀድሞ እንዳሰበውና ለሁሉም ችግር አስቀድሞ መፍትሄ እንዳበጀ ነግሮኝ ነበር፡፡ ሆኖም በዚህ ሂደት ውስጥ እኔ ራሴ ከሞት አፋፍ እገኛለሁ ብሎ አልጠበቀም ነበር፡፡

ያም ሆነ ይህ የቄሳርን ጉዞ ጠቅለል አድርጌ ስመለከት የምነቅፈው ነገር አይኖርም፡፡ በአንጻሩ ሀይላቸውን በእድልና በሌሎች ድጋፍ ላገኙ መሪዎች የሚሆን አይነተኛ ተምሳሌት አድርጌ ባቀርበው የምሳሳት አይመስለኝም፡፡ ቄሳር የከፍተኛ ወኔ

ባለቤትና ሰፊ ራዕይ ያለው መሪ ነበር፡፡ ቀድሞውኑ ከተላበሰው ሰብእናና ከተጓዘበት መንገድ የተሻለ እራሱን በምንም መልኩ ሊያንጽ አይችልም፡፡ እቅዶቹ አየር ላይ ተንሳፈው የቀሩት የአሌክሳንደር ህይወት በአጭሩ በመቀጨቱና እሱ ራሱም በከባድ ህመም በመያዙ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ አዲስ ልኡል እራሱን ከጠላት ለመከላከል፣ የወዳጆችን ድጋፍ ለማግኘት፣ በሀይልም ሆነ በዲፕሎማሲ ድል ለመቀናጀት፣ በተከታዮቹ ዘንድ ለመወደድና ለመፈራት፣ በወታደሮቹ ለመከበር፣ ጉዳት ሊያደርሱበት የሚችሉ ሀይሎችን ለማጥፋት፣ ጥንታዊ ተቋማትን ለማደስ፣ ከዳተኛ የሆኑ ወታደሮችን መንግሎ አዲስ ሰራዊት ለመገንባት፣ ከንጉሶችና ልኡላን ጋር ያለውን ግንኙነት በመከባበር እንዲደግፉት፣ ካልሆነም እሱ ላይ ጉዳት ከመጣል እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ለሚፈልግ አዲስ መሪ ከቄሳር የተሻለ የዘመናችን ተምሳሌት አይኖርም፡፡

የቄሳር አካሄድ ነቀፌታ ሊቀርብበት የሚችለው ጳጳስ ጁሊየስን ለማስመረጥ በወሰደው መጥፎ እርምጃ ብቻ ነው፡፡ እዚህ ላይ ርግጥ ጥሩ ውሳኔ አልወሰነም፡፡ አስቀድሜ እንደገለጽኩት የሚፈልገውን አይነት ጳጳስ ማግኘት ባይችልም በፍላጎቱ ውስጥ ያልተካተተ ጳጳስ ማስቀመጥም አልነበረበትም፡፡ እሱ ጉዳት ካደረሰባቸው ወይም እሱን ለመፍራት ምክንያት ካላቸው ካርዲናሎች መካከል ጳጳሱ እንዲመረጥ መፍቀድ አግባብ አልነበረም፡፡ በርግጥ ሰዎች የሚጎዱህ አንድም ስለሚፈሩህ አሊያም ስለሚጠሉህ ነው፡፡ ቄሳር ራሱ ጉዳት ካደረሰባቸው መካከል ሳን ፒየትሮ አድ ቪንኩላ፣ ኮሎና፣ ሳን ጆርጂዮ እና አስካኒዮ ይገኙበታል፡፡ ከነዚህ ውጭ ሌሎቹም ሁሉ ቢመረጡ

እንኳ ቄሳርን ለመፍራት በርካታ ምክንያቶች የነበራቸው ናቸው - ከስፔይኖቹና ከሮዌን በስተቀር:: ስፔይኖቹ የቄሳር ባለእዳ ነበሩ:: ሮዌን ደግሞ የፈረንሳዮች ድጋፍ ስለነበረው በራሱ በጣም ሀያለኛ ነበር:: የቄሳር የመጀመሪያና ተቀዳሚ ግብ መሆን የነበረበት ከስፔይ ተወላጆች መካከል አንዱን ማስመረጥ ነበር:: ይህ ካልተሳካም ሮዌን መሆን ነበረበት:: ሳን ፔየትሮ ደ ቪንኩላ ግን በፍፁም መመረጥ አልነበረበትም:: በታላላቅ ሰዎች ዘንድ "አዲስ በረከት የድሮ ጠባሳዎችን ይሽራል" ብሎ የሚያስብ ካለ በርግጥ እራሱን እያታለለ ነው:: ስለሆነ እዚህ ጋር የቄሳር ምርጫ የተሳሳተ ነበር:: ለውድቀቱ ዋነኛው መንስኤም ይኸው ነበር::

## 8. በትረ ስልጣንን በወንጀል መጨበጥ

አስቀድሜ ከገለጽኳቸው ስልጣንን የመጨበጫ ሁለት መንገዶች በተጨማሪ ወደ ልኡልነት ደረጃ የሚያደርሱ ሁለት ተጨማሪ መንገዶች አሉ:: አንደኛው መንገድ በወንጀልና ህገ ወጥነት የልኡልነትን በትር መጨበጥ ሲሆን ሌላኛው መንገድ አንድ ተራ ዜጋ የህዝቡን ድጋፍ አግኝቶ የገዢነት ክብር ሲሰጠው የሚከሰት ነው:: ለጊዜው የማተኩረው በልኡላዊ አስተዳደር ላይ እንደመሆኑ የመጀመሪያውን መንገድ ሁለት አይነተኛ ምሳሌዎችን በማቅረብ አብራራዋለሁ::

ሲሲሊያዊው አጋቶክሌስ የገገርነትን መንበር ከመጨበጡ በፊት ተራ ሰው ብቻ ሳይሆን ከዝቅተኛ ማህበረሰብ ተርታ

የሚመደብ ነበር፡፡ አጋቶክሌስ ከነበረበት ዝቅተኛ የህይወት ማጥ ተነስቶ ነበር የሲራከዝ ንጉስ መሆን የቻለው፡፡ የሸክላ ሰሪ ልጅ የነበረው አጋቶክሌስ ወደ መንበረ ስልጣኑ ለመውጣት የረገጠው እያንዳንዱ እርከን በወንጀልና በህገ ወጥነት የጨቀየ ነበር፡፡ ሆኖም ወንጀሎቹ ሁሉ ከፍተኛ የሆነ ወኔና ጀብዱ የተላበሱ ናቸው፡፡

አጋቶክሌስ የግዛቱን ሚሊሺያ ተቀላቅሎ በድፍረቱና በጀብደኘነቱ የተለያዩ እርከኖቹን ተሻግሮ የጦር ሹም ለመሆን በቃ፡፡ በርግጥ ለዚህ የስልጣን እርከን ከታጨ በኋላ ነበር የልኡልነት ህልሙን እውን ለማድረግ የቆረጠው፡፡ በፈቃደኝነት ሊገዙለት ይችሉ የነበሩትን እንኳን ምንም ከግንዛቤ ሳይከት ፍላጎቱን በሀይል ለማሳካት እቅድ ነደፈ፡፡ ሲሲሊ ውስጥ ዘመቻ ላይ ከነበረው ካርቴጊርያዊው ሀሚልካር ጋር ተመካክሮም ከጋራ ስምምነት ደረሰ፡፡

እናም በአንድ እለት ጀምበር የሳይራከዝን ህዝብና ሴኔት በአገራዊ ጉዳይ ላይ ለመመካከር በሚል ሰበብ ጉባኤ ጠራና ታስቦበት በታቀደ ቅድመ ዝግጅት የግዛቲቱን ሴናተሮችና ከበርቴዎች ሁሉ በሰራዊቱ አስፈጃቸው፡፡ የግዛቲቱ የከፍተኛ መደብ አባላት እንደ ቅጠል ሲረግፉ አጋቶክሌስ ምንም አይነት የውስጥ ተቀናቃኝ ሳይገጥመው የከተማይቱን መስተዳድር ከመዳፉ አስገባ፡፡ ምንም እንኳ ግዛቲቱ በካርቴጊርያውያን ተደጋጋሚ ወረራና ጥቃት ቢደርስባትም አጋቶክሌስ ግዛቱን በሚገባ ከመከላከልም አልፎ ከሰራዊቱ ገሚሱን ካርቴዥያውያንን ለመመከት መድቦ በተቀረው ሠራዊት ደግሞ አፍሪካን እስከ መውረር ደርሶ ነበር፡፡ ከዚህም ባሻገር በካርቴጊርያውያን ላይ

የከተት ዘመቻ አውጆ በጥቂት ሰርጦች ተገድበው ከፍተኛ ችግር ላይ እንዲወድቁ አስገድዷቸዋል፡፡ በመጨረሻም ካርቴጃያውያን በአፍሪካ ተወስነው ሲሲሊን ለአጋቶክሌስ ለመተው ተገደው ነበር፡፡

የአጋቶክሌስን አካሄድ ጠለቅ ብሎ የመረመረ ሰው ሊያገኝ የሚችለው ከእድል ጋር የተያያዘ ስኬት ጥቂት ወይም ምንም የሚባል መሆኑን ነው፡፡ ከላይ እንዳስቀመጥኩት ከሚሊሺያ ተነስቶ ደረጃ በደረጃ እስከደረሰበት የገዢነት እርከን ያደረገው ጉዞ በጠንካራ መሰናክልና አደጋ የተከበበ ነበር፡፡ ስልጣኑን ጠብቆ ለማቆየት የቻለውም በከፍተኛ ጀብዱና ተጋድሎ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን የራስን ዜጋ መጨፍጨፍ፣ ወዳጆችን መክዳት፣ እዝነትና እምነተ ቢስ መሆን ከቶም ጀግና ሊያስብል አይችልም፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ ሀይልን ሊያጎናጽፍ ቢችልም ታላቅነትን ሊያላብስ አይችልም፡፡ በርግጥ የአጋቶክሌስ አደጋን የመጋፈጥና የመቋቋም ወኔ፣ መሰናክሎችን በጽናትና በጥንካሬ የመወጣት ታላቅ ድፍረት አትኩሮትን ይስብ ይሆናል፡፡ ከሌሎች የጦር አበጋዞች ጋር በንጽጽር ሲታይም ከማንም ያነሰ ነው ብሎ መፍረድ አይቻልም፡፡ ነገር ግን አሰቃቂ ጭካኔው፣ ኢ-ሰብአዊነቱና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወንጀሎቹ ከክቡራን ጎራ ክቡር ከመሰኘት ያግዱታል፡፡ ስለዚህ የአጋቶክሌስን ስኬት ከእድልም ሆነ ከጀግንነት ጋር ማያያዝ አይቻልም - ከሁለቱም የሚመነጭ አይደለምና፡፡

በአሌክሳንደር 6ተኛ የማናለብኝነት ዘመን ደግሞ አንድ አልቬርቶ የሚባል የፌርሞ ሰው ነበር፡፡ ከአመታት በፊት አልቬርቶ አባት የለሽ ህጻን ስለነበር የእናቱ ወንድም በሆነው

ጂዮቫኒ ፎግሊያኒ በሚባለው አጎቱ እጅ ነው ያደገው:: ገና በጉርምስናው ወቅት በቂ የውትድርና ክህሎት ለመቅሰም ውትድርና ተቀጠረ:: ፓውሎ ቪቴሊ በሚባል ወታደር እጅ በደንብ ከሰለጠነም በኋላ በእሱ ስር ሆኖ ማገልገል ጀመረ:: ፓውሎ ሲሞት ደግሞ በወንድሙ በቪቴሎዞ ስር ሆኖ ውትድርናውን ቀጠለ:: አልቬርቶ ከአቻዎቹ በተለየ እጅግ ንቁ፣ ደፋርና ጀብደኛ ስለነበርም በአጭር ጊዜ የቪቴሎዞ ዋና የጦር አዛዥ ለመሆን በቃ:: ሆኖም ለሌሎች መታዘዝ ባርነት መስሎ ስለታየው ግዛታቸው ከቸረቻቸው ነጻነት ይልቅ ባርነቱ ካመዘነባቸው የፌርሞ ዜጎችና በቪቴሊ ውለታና እርዳታ ፌርሞን የግሉ ለማድረግ ቆረጠ::

ከዚህ በመነሳት ለፌርሞው ገዢ፣ የማደጎ አባቱ ጂዮቫኒ ፎግሊያኒ ደብዳቤ ከትቦ እነዚህን ሁሉ በርካታ አመታት ከቤቱ ርቆ ከቆየ በኋላ አሁን ተመልሶ እሱንና ከተማዋን ለመጎብኘትና እግረ መንገዱንም በግዛቱ ውስጥ የተወሰኑ ነገሮችን ለመመርመር እንደሚፈልግ ገልጾ መልእክት ላከ::

በእቅዱም መሰረት የሀገሩ ዜጎች እነዛን ሁሉ አመታት በከንቱ እንዳላባከነ ይረዱለት ዘንድ በመቶዎች የሚቆጠሩ አጃቢዎችና አገልጋዮች አስከትሎ ወደ ፌርሞ አቀና:: ወደ ግዛቱ ከመግባቱ አስቀድሞ የጂዮቫኒ የማደጎ ልጅ እንደመሆኑ ለርሱም ሆነ ለራሱ ክብርና ግርማ ሞገስ የሚያጎናጽፍ አቀባበል እንዲያሰናዳ ጂዮቫኒን ተማጸነ:: ጂዮቫኒም በዚህ ረገድ አልሰነፈም:: የፌርሞ ዜጎች አልቬርቶን በደማቅ አቀባበል እንዲቀበሉት አድርጎ ከእልፍኙ አሳረፈው::

ይኸኔ አልቬርቶ ድብቅ ሴራውን እያውጠነጠነ ጥቂት ቀናት ተቆጠሩ፡፡ ቅድመ ዝግጅቱ ካበቃ በኋላ የመሳፍንት ድግስ አዘጋጅቶ ጂዮቫኒንና የፌርሞን ግምባር ቀደም መሪዎች ጋበዘ፡፡ ሁሌም በመኳንንት ደምብ እንደሚደረገው ተበልቶ ተጠጥቶና ታዳሚው ተዝናንቶ ካበቃ በኋላ በጨዋታ መካከል አልቬርቶ ዋና ዋና ነጥቦችን በመላ መጎንታተል ጀመረ፡፡ ስለ ጳጳስ አሌክሳንደር፣ ስለ ልጁ ቄሳርና ስለ መርሀ ግብሮቻቸው ነካካ፡፡ በምላሹ ጂዮቫኒና ሌሎቹ በርእሱ ዙሪያ ሀሳብ መጣል ሲጀምሩ በድንገት ብድግ ብሎ እንዲህ አይነት ውይይቶች በድብቅ መካሄድ እንዳለባቸው ገልጾ ወደ ሌላ ክፍል ገባ፡፡ ጂዮቫኒና ሌሎችም ከበርቴዎች ወደ ክፍሉ ተከተሉት፡፡ ሆኖም ገና ከመቀመጣቸው አልቬርቶ የሸሸጋቸው ወታደሮች ከመሸጉበት ተኮልኩለው ጂዮቫኒን ጨምሮ ሁሉንም ረሸኗቸው፡፡

ጅምላ ፍጅቱ ከተገባደደ በኋላ አልቬርቶ ፈረሱን በከተማው መሀል እየጋለበ የሀገሪቱ የምክር ቤት አባላት ያሉበትን ቤተ መንግሥት ከበበ፡፡ የምክር ቤቱ አባላት በሙሉ በፍርሀት ስለተሸመደመዱ እሱ በልኡልነት የሚመራው ግዛት ለመመስረት ተገደዱ፡፡ ህጉን የማይከተሉትንና የሚቀናቀኑትን ሁሉ ፈጅቶ አዳዲስ የሲቪልና ወታደራዊ ተቋማትን በመገንባት ዙፋኑን አደላደለ፡፡ በዚህ መልኩ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ፌርሞ ውስጥ መንገስ ብቻ ሳይሆን አጎራባች ግዛቶችን የሚያሰጋ ግዛት መመስረት ቻለ፡፡ በስተመጨረሻ በቄሳር ቦርጂያ ወጥመድ ባይያዝ ኖሮ ልክ እንደ አጋቶክሌስ ሁሉ የእሱም አወዳደቅ በእጅጉ አዳጋች ይሆን ነበር፡፡ ሆኖም ቄሳር ኦርሲኒና ቪቴሊዎችን ሲኒጋግሊያ ላይ ያጠመዳቸው ጊዜ አልቬርቶም

ከሰለባዎቹ መካከል ነበር፡፡ እናም አሳዳጊውን በገደለ በአመቱ የከፋቱና የወንጀሉ አስጠ'ኚ ከሆነው ቪቴልዞ ጋር በስቅላት ተቀጣ፡፡

አጋቶክሌስና መሰል ሰዎች ለቁጥር የሚያታክቱ ግፍና ጭቆና እያደረሱ በድንበራቸው ዙሪያ በጠላት ተከበው በዜጎቻቸው ምንም አይነት ሴራ ሳይጠነሰስባቸው በሰላም ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው ሲያዙና ሲገዙ የተመለከተ በእጅጉ መገረሙ አይቀርም፡፡ በርካታ ጨናማ መሪዎች ስልጣናቸው በቋፍ ለማቆየት በሚብረከረኩበት አለም እንደ አጋቶክሌስ ያሉ መሪዎች በደም የጨቀየ ምግባር ይዘውና በውጭ ጦር እየታመሱ ቀርቶ በሰላሙም ጊዜ ቢሆን ስልጣናቸውን ጠብቀው ማቆየት መቻላቸው የሚጠበቅ አልነበረም፡፡

እንደኔ አመለካከት ይህ አይነቱ ሁኔታ እንደ ጭካኔው አይነት መጤን አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡ በጥሩ መልኩ የሚተገበር ጭካኔና በመጥፎ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ጭካኔ ዳራቸው ለየቅል ነው፡፡ ጭካኔ በጥሩ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል ለማለት የምንችለው (መጥፎ ምግባርን በዚህ መልኩ መግለጽ አግባብ ከሆነ) ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ብቻ ከተተገበረ፣ ደህንነታችንን የሚወስን ሆኖ ከተገኘና ተከታታይ ጉትጎታ ሳያስፈልገው በአንዴ አዎንታዊ ተረፈ ምርትን ወደ ሚያበረክትበት መንገድ ከተቀየረ ነው፡፡ በመጥፎ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ጭካኔ በተቃራኒው ሲጀመር የማይቀጥል ቢመስልም ጊዜ ባለፈ ቁጥር ከመጥፋት ይልቅ የሚባባስ የጭካኔ አይነት ነው፡፡ እነዚያ የመጀመሪያውን አይነት መንገድ የሚጠቀሙ በፈጣሪና በሰብአዊ ፍጡሮች እገዛ እንደ አጋቶክሌስ

የሥልጣን ደረጃቸውን ያሻሽሉበት ይሆናል፡፡ ሁለተኛዎቹ ጨካኞች ግን በምንም ሁኔታ በስልጣናቸው ሊቆዩ አይችሉም፡፡

ስለዚህ አንድ ልኡል አንድን ግዛት (የመንግሥት ስልጣን) ሲይዝ ሊያደርስ የሚችላቸውን ጉዳቶች ከቅድመ እሳቤ መከተት አለበት፡፡ የሚጥለውን ጉዳት አመዛዝኖ በማያዳግም አግባብ ላንዴም ለሁሌም ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የሚያደርሰው ጉዳት እለት ተእለት የሚታደስ መሆን የለበትም፡፡ በዚህ መልኩ የዜጎች አእምሮ እረፍትና እፎይታ እንዲያገኝ፣ መካሻ ሲበጅ እንዲጠገን ማድረግ ይቻላል፡፡

በመበርገግም ይሁን በመጥፎ ምክር ተነሳስቶ ከዚህ በተቃራኒ የሚገዝ ካለ ሁሌም ሊፈራና ሊሰጋ ይገባዋል፡፡ በጭራሽ ሎሌዎቹንና ተከታዮቹን ሊተማመን አይችልም፡፡ በየእለቱ በሚታደስ ሰቆቃና በማያቋርጥ ብጥብጥ የሚሰቃዩ ተከታዮች እንደዚህ ካለው መሪ ጋር እየኖሩ የደህንነት ስሜት ሊሰማቸው አይችልም፡፡ የጭካኔ በትር መጣል ያለበት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ሰዎች ጣእሙን ይረሱታል፡፡ ቅሬታቸውና ጥላቻቸውም እየተመናመነ ይሄዳል፡፡ በጊዜ ሂደት መካሻ ማበጀትም አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ሲሆን ደግሞ የተሻለ ጣእም ሊኖረው ይችላል፡፡

# ህገ መንግሥታዊ አገዛዞች

## 9. ህገ መንግሥታዊ አገዛዞች

የአንድ ሀገር ዜጋ ከወንጀልም ሆነ ማንኛውም አይነት ጠብ አጫሪ መንገድ በተቃራኒ በዜጎች ምርጫ የአንድ ግዛት አስተዳዳሪ ተደርጎ ሊቀመጥ ይችላል። በህገ መንግስታዊ ግዛቶች ውስጥ ስልጣን ለመያዝ ጀግንነት ወይም እድል ብቻውን በቂ አይሆንም፤ ከዚህ ባሻገር በእድል የታገዘ ብልህነት ያስፈልጋል።

አንድ ሰው በህዝቡ ወይም በመሳፍንቱ ምርጫ የአንድ ግዛት ሀገረ ገዥ ተደርጎ ሊመረጥ ይችላል። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሀይላት በማንኛውም ግዛት ውስጥ ይገኛሉ። ህዝቡ በመሳፍንቱ ላለመጨቆንና ላለመረገጥ ይፈልጋል። መሳፍንቱ ደግሞ ህዝቡን ጨፍልቀው ጨቁነው መግዛት ይፈልጋሉ። እነዚህ ተቃራኒ ፍላጎቶች በአንድ ሀገር ውስጥ ከሶስት ውጤቶች አንዱን ሊያስከትሉ ይችላሉ - ልኡላዊ አስተዳደርን፣ ወይም ነጻ ግዛትን፣ አሊያም ስርአት አልበኝነትን።

ልኡላዊ አስተዳደር በህዝቡ ወይም በመሳፍንቱ፣ ከሁለቱ ሀይሎች የሀይል ሚዛኑ ባጋደለው አማካኝነት ይፈጠራል። መሳፍንቱ ህዝቡን መቋቋም እንደማይችሉ ሲረዱ ከመካከላቸው

አንዱን ሀያል በማድረግ በርሱ ካባ ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ ይዘይዳሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ህዝቡ መሳፍንቱን መቋቋም ሲሳነው ከመካከላቸው አንዱን ልኡል አድርገው ሾመው በእሱ ጥበቃ ራሳቸውን ለመታደግ ይሞክራሉ፡፡

በመሳፍንቱ ምርጫ ስልጣን ላይ የወጣ ገገር በህዝቡ ከሚመረጠው በላቀ ስልጣኑን ለማስጠበቅ ይቸገራል፡፡ ከልኡሉ እንደማይተናነሱ ወይም የልኡሉ እኩያ ነን ብለው በሚያስቡ መኳንንት እንደመከበቡ የበታቾቹን በፈለገው መልኩ ለማዘዝና ለመቆጣጠር ይቸገራል፡፡ በህዝቡ ምርጫ ስልጣን ላይ የወጣ ልኡል ተቀናቃኝ ስለማይኖረው የማይታዘዘው ሰው ቁጥር ጥቂት ወይም ምንም ሊባል የሚችል ነው፡፡

ከዚህም ተጨማሪ አንድ ልኡል የመሳፍንቱን ክብር በጠበቀ መልኩ ሌሎችን ሳይጨቁን የመሳፍንቱን ፍላጎት ማሟላት አይችልም፡፡ የህዝቡን ፍላጎት በተመለከተ ግን ማንንም ሳይጨቁን ሊያሟላ ይችላል፡፡ ከመሳፍንቱ ይልቅ የህዝቡ ፍላጎት ፍትሀዊ ነው፡፡ ምክንያቱም የመሳፍንቱ ፍላጎት ህዝቡን መጨቆን ሲሆን የህዝቡ ፍላጎት ደግሞ በማንም አለመጨቆን ብቻ ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር አንድ ልኡል በሚጠላው ህዝብ መሀል ዋስትና ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም የህዝቡ ቁጥር የትየለሌ ነው፡፡ ከህዝቡ አንጻር ሲታይ የመሳፍንቱ ቁጥር ከግምት የሚገባ ባለመሆኑ ባንጻራዊ መልኩ ዋስትናውን ማረጋገጥ ይችላል፡፡

በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ አንድ ልኡል በህዝቡ ጥላቻ ሊደርስበት የሚችለው የከፋ ነገር በህዝቡ ገሸሽ መደረግ ብቻ

ነው፡፡ ከመሳፍንቱ የሚያተርፈው ጥላቻ ግን ከመተፋት ባለፈ ለንቅናቄ ሊያጋልጠው ይችላል፡፡ መሳፍንቱ አርቆ አስተዋዮችና ሥሌዎች ናቸው፡፡ ሁሌም ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ዝግጁ ናቸው፡፡ በማንኛውም አጋጣሚ ድል ካዘነበለችበት ጎራ ለመሰለፍ ፈቃደኛ ናቸው፡፡

አንድ ልኡል ሁሌም የሚኖረው ከህዝቡ ጋር ነው፡፡ ያለመሳፍንቱ ግን መኖር ይችላል፡፡ ሊሾማቸው፣ ሊሽራቸው፣ ሊያጠናክራቸውና ሊያዳክማቸው ይችላል፡፡ ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ መሳፍንቱን በተመለከተ ሁለት ከግንዛቤ ሊገቡ የሚገቡ እውነታዎች አሉ፡፡ አንድም የእጣ ፈንታህ አካል መሆናቸውን አምነው ጥገኛ ይሆናሉ፣ አሊያም እራሳቸውን ለመቻል ይታትራሉ፡፡ ጥገኛ የሆኑቱ በዝባዥ እስካልሆኑ ድረስ ክብርና ውዴታ ይገባቸዋል፡፡ ከጥገኝነት ለመላቀቅ የሚሹቱ በአንጻሩ ሁለት ምክንያት ይኖራቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በፍራቻ ወይም በተፈጥሮአቸው ጥገኛ መሆን አይፈልጉ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ልትጠቀምባቸው ትችላለህ፡፡ በተለይ ስሜት የሚሰጥ ምክርና ድጋፍ ማበርከት የሚችሉት፣ ስትበረታ አክብሮትን ስለሚቸሩ በችግር ወቅትም ቢሆን ሊያስጉህ አይገባም፡፡ ሆኖም ሆን ተብሎ ከስልጣን ጉጉት በመነጨ ከቁጥጥርህ ነጻ ለመውጣት የሚታገሉትን መጠንቀቅ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም አካሄዳቸው ካንተ ይልቅ ለራሳቸው እንደሚጨነቁ የሚያመላክት ነው፡፡ እንደዚህ አይነቶቹን መሳፍንቶች በተመለከተ ልኡሉ እራሱን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ውላቸውን ከለዩ ጠላቶች ተርታ ቀላቅሎ ማየት ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም በችግር ጊዜ ስልጣኑን ለመናድ ያደባሉ፡፡

በህዝብ ምርጫ የተሾመ ልኡል የህዝቡን ወዳጅነት ጠብቆ ለማቆየት ተግቶ መስራት ይኖርበታል፡፡ ይህ ደግሞ በጣም ቀላል ነው፡፡ ምክንያቱም ህዝቡ የሚፈልገው አለመጨቆንን ብቻ ነው፡፡ ከህዝቡ ፍላጎት በተቃራኒ በመሳፍንቱ ምርጫ የተሾመ ልኡልም ከሁሉ ነገር አስቀድሞ የህዝቡን ይሁንታ ለማግኘት መስራት ይኖርበታል፡፡ ህዝቡን መጠበቅና ከጭቆና መከላከል እስከቻለ ድረስ ይህም ቀላል ነው፡፡ ሰዎች ይጎዳናል ብለው ከሚያስቡት ሰው ያልጠበቁትን አይነት ጥቅም ሲያገኙ ከመቅጽበት በባለ ውለታቸው የውለታ እዳ ይታሰራሉ፡፡ በመሆኑም በእነሱ ምርጫ ከሚያስተዳድራቸው ሰው በላቀ ፍቅርና መልካም አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡

አንድ ልኡል የህዝቡን ቀልብ የሚገዛባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ሆኖም እንደሁኔታዎች የሚለያዩ በመሆናቸው ቋሚ ህግጋት ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ግን ለአንድ ልኡል የህዝቡን ወዳጅነት ማረጋገጥ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ አለበለዚያ በችግር ጊዜ መፍትሄ ማግኘት አዳጋች ይሆናል፡፡

የስፓርታውያኑ ልኡል ናቢስ፣ መላዋን ግሪክና ሀያሉን የሮማውያን ጦር ተቋቁሞ ግዛቱንና ስልጣኑን ማስጠበቅ የቻለ ሰው ነበር፡፡ አደጋ በተጋረጠበት ጊዜ ሁሉ እርምጃ የሚወስደው እፍኝ በማይሞሉ ዜጎቹ ላይ ብቻ ነበር፡፡ ሆኖም ህዝቡ በጠቅላላ ለልኡሉ ላይ ቢነሳበት ኖሮ ይህ የልኡሉ እርምጃ በቂ ባልሆነ ነበር፡፡

ይህንን እውነት ማንም ሰው "በህዝብ ላይ የሚገነባ በጭቃ ላይ የገነባ ነው" በሚለው በተለመደው ችኮ አባባል ሊቃረነው

አይገባም፡፡ ምክንያቱም ይህ ሊሆን የሚችለው አንድ ሰው ሥልጣኑን ህዝቡ ላይ መሰረት አድርጎና ይህንኑ ተማምኖ ህዝቡ ከጠላቱና ከከዳተኛ ባለስልጣናት ይታደገኛል ብሎ ሲቀመጥ ነው፡፡ ሆኖም አንድ ህዝቡን በአግባቡ መምራት የሚችል ደፋር፣ በአደጋ የማይበገር፣ ጥንቃቄ ከመውሰድ የማይዘናጋ፣ በባህሪውና በገነባቸው ተቋማት የብዙሀኑን አመኔታ ያተረፈ ልኡል ሀይሉን በህዝቡ ላይ ቢገነባ ህዝቡ አሳልፎ አይሰጠውም፡፡ ስልጣኑንም አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ለማረጋገጥ አይቸግረውም፡፡

በርካታ ግዛቶች ብዙውን ጊዜ ለውድቀት የሚዳረጉት ከተገደበ ስልጣን ወደ ፈላጭ ቆራጭነት በሚደረገው ሽግግር ነው፡፡ ይህንን እርምጃ የሚያካሂዱ ልኡላን አንድም በቀጥታ አሊያም በተዘዋዋሪ በጠቅላይ ግዛት ሹማምንት አማካይነት መግዛት ይችላሉ፡፡ በጠቅላይ ግዛት ሹማምንት በኩል ህዝባቸውን የሚመሩ ልኡላን ሀይላቸው ደካማና በአደጋ የተከበበ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ስልጣን ላይ ባስቀመጧቸው ሰዎች ፈቃድ ላይ ጥገኛ ለመሆን ይገደዳሉ፡፡ እነዚህ ሹማምንት በአደጋ ጊዜ ገጽ ለገጽ በመጋፈጥ ወይም ባለመታዘዝ ከዙፋናቸው ሊያወርዷቸው ይችላሉ፡፡ አደጋ ሲከሰት ልኡሉ ሙሉ ስልጣኑን የሚጨብጥበት አፍታ አያገኝም፡፡ ምክንያቱም ትእዛዝን ከሹማምንቶቹ መቀበል የለመዱት ዜጎች ቀውስ ሲከሰት በቀጥታ በልኡሉ መታዘዝ አይጀምሩም፡፡ ከዚህም ተጨማሪ ልኡሉ እምነት የጣለባቸው ሰዎች በአደጋ ጊዜ በቦታቸው ላይገኙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ልኡል በሰላሙ ጊዜ ህዝቡ የሱን አመራር በሚከተልበት ሰአት በሚያያቸው ሁኔታዎች መተማመን የለበትም፡፡ በሰላሙ ጊዜ ሁሉም ሰው አብሮህ ይቦርቃል፤ ሁሉም

ሰው ቃሉን ይሰጣል፣ ሁሉም ሰው ህይወቱን ሊሰጥህ አለሁ አለሁ ይላል - ሞት ቅርብ ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ!

ሆኖም በመከራ ጊዜ፣ ሀገር ዜጎቿን ከመቼውም በላቀ አጥብቃ በምትፈልግበት ወሳኝ ቅጽበት ከጎንህ የሚቆሙት ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ ይህ አይነቱ ታማኝነት ደግሞ ከሁሉ በከፋ አደገኛ ነው - ምክንያቱም ሁለተኛ እድል አይሰጥም፡፡ ስለሆነም ብልህ የሆነ ልኡል ዜጎቹ በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ሁኔታ የሱና የስልጣኑ ጥገኛ ይሆኑ ዘንድ ዘዴ መቀየስ አለበት፡፡ ይህ ሲሆን ሁሌም ታማኝ ሆነው ይገኛሉ፡፡

## 10. የቤተ-ክህነት አገዛዞች

በቤተ-ክህነት ግዛቶች ውስጥ የስልጣን መሰናክሎች የሚከሰቱት መሪው ስልጣን ከመጨበጡ አስቀድሞ ብቻ ነው፡፡ በእንደዚህ አይነቶቹ ግዛቶች ውስጥ ስልጣን ለመጨበጥ አንዳንድ ጊዜ ጀግንነት አንዳንዴም እድል ያስፈልጋል፡፡ አንድ ጊዜ መሪው ስልጣን ከጨበጠ በኋላ ግን ያለሁለቱም ድጋፍ ስልጣኑን ጠብቆ ማቆየት ይችላል፡፡

የቤተ-ክህነት ግዛቶች ሀያል በሆኑ ሀይማኖታዊ ተቋማት የሚመሩ በመሆናቸው የመሪው አመራርና ምግባር ምንም ይሁን ምን ተቋማቱ ስርዓቱን ይጠብቁታል፡፡ እስካሁን ከጠቀስናቸው ግዛቶች በተለየ የቤተ-ክህነት ግዛት መሪዎች ግዛት ቢኖራቸውም ግዛታቸውን የመከላከልና ዜጎቻቸውን የመቆጣጠር ግዴታ አይጣልባቸውም፡፡ ግዛታቸው ጠባቂና ተከላካይ ባይኖረውም

ወራሪ ጠላት ወይም ተቀናቃኝ ሀይልም አይፈጠርባቸውም፡፡ የግዛቱ ነዋሪዎች ፖለቲካዊ አስተዳደር ባይኖራቸውም የአስተዳደሩ ሁኔታ ሳያሳስባቸው ህይወታቸውን በራሳቸው መንገድ ይቀጥላሉ፡፡ መሪያቸውን በሌላ የመተካት ፍላጎቱም ሆነ ስልጣኑ አይኖራቸውም፡፡ በመሆኑም እስካሁን ካየናቸው ግዛቶች በተለየ የቤተ-ክህነት ግዛቶች ብቻ ደህንነታቸው የተረጋገጠ፣ ፍጹም ሰላማዊ ግዛቶች ናቸው፡፡

የቤተ-ክህነት ግዛቶች የሰው ልጅ አእምሮ በማይደርስበት ልእለ ሀያል የሚመሩ በመሆናቸው ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሙግት መግጠም አልሻም፡፡ እነዚህ ግዛቶች በእግዚአብሄር ፍቃድ የሚመሰረቱና የሚመሩ እንደመሆናቸው እንዲህ አይነቱን ጉዳይ የመሞገት ድፍረት የሚኖራቸው ፈሪሀ እግዚአብሄር የራቃቸው ብቻ ናቸው፡፡ ሆኖም እስከ አሌክሳንደር ዘመን ድረስ እያንዳንዱ ሀያል ነኝ ባይ ንጉስ፣ ትንንሽ ባላባትና ከበርቴዎች እንኳ ሳይቀሩ የሚፈነጩባት የጳጳሱ ግዛት አሁን በድንገት የፈረንሳዩ ንጉስ ሲንበረከክላት፣ ቬኒዥያውያን ሲወድሙላት አይቶ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ የሚል ጥያቄ ለሚያነሳ የቤተ-ክህነትን ግዛት ጉዞ ማስታወሱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

የፈረንሳዩ ንጉስ ቻርለስ ጣሊያንን ከመውረሩ በፊት ሀገሪቱ በጳጳሱ፣ በቬኒሻውያን፣ በኔፕልሱ ንጉስ፣ እንዲሁም በሚላንና በፍሎሬንቲናውያን ሀገረ ገዥዎች ትተዳደር ነበር፡፡ እነዚህ ሀይላት ምንም የተከፋፈሉ ቢሆኑ ሁለት ዋና ዋና የጋራ ሃሳቦች ሳይኖራቸው አልቀረም፡፡ አንደኛው ማንኛውም አይነት የውጪ ጦር ጣሊያንን መውረር የለበትም የሚለው ሲሆን፣ ሌላኛው በመካከላቸው ያለ ማንኛውም ሀይል ግዛትን የማስፋፋት እርምጃ

መውሰድ የለበትም የሚል ነበር፡፡ ከነዚህ የተከፋፈሉ ግዛቶች ውስጥ የጳጳሱ ግዛትና ቬኒዥያ ለየት ያለ ጥንቃቄ ይደረግላቸው ነበር፡፡

ቬኒዣውያንን ለመቆጣጠርና ለመጠበቅ እንዲያመች ከሁሉም የተውጣጣ የጋራ ሀይል አስፈላጊ ነበር፡፡ የጳጳሱን ግዛት መጠበቅ ደግሞ የሮማውያኑ ባላባቶች ሚና ነበር፡፡ እነዚህም ኦርሲኒና ኮሎና በሚባሉ ሁለት አንጃዎች የተከፋፈሉ ሲሆኑ በአንጃዎቹ መካከል ሁሌም የድርሻ አለመግባባት ይከሰታል፡፡ በግዛቱ ውስጥ ጦር ያላቸው ብቸኛ መደቦች በመሆናቸውም የጳጳሱን ግዛት አቅመ ቢስና ዋስትና አልባ አድርገውት ነበር፡፡ ከስንት ጊዜ አንዴ እንደ ሲክስተስ አይነት መንፈሳዊ ጥንካሬ የተላበሱ ጳጳሳት ቢከሰቱም እንዲህ አይነቶቹ ብርቱዎች እንኳን የደጋፊዎቻቸውን ሀይልና የግዛቲቱን ጥሪት ተጠቅመው ከአንጃዎቹ ጫና መላቀቅ ይሳናቸዋል፡፡ አንድ ጳጳስ በአማካኝ አስር አመት ሲገዛ ከአንጃዎቹ አንዱን ለማጥፋት የሚታደልበት ጊዜ በእጅጉ የመነመነ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ጳጳስ እድል ቀንቶት የኮሎናን አንጃ ማጥፋት ቢችል የኦርሲኒ ተቃዋሚ የሆነ ሌላኛው ይመጣና ኮሎናዎችን መልሶ ያለመልማል፡፡ ሆኖም ኦርሲኒዎችን ለማጥፋት በቂ ጊዜ አይኖራቸውም፡፡

ይህ በመሆኑ ጳጳሱ በጣሊያን ውስጥ የነበረው ሀይል የተገደበ ነበር፡፡ ሆኖም የአሌክሳንደር ጊዜ ደረሰና ከሱ ቀደም ከነበሩ ጳጳሶች ሁሉ በላቀ፣ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ አንድ ጳጳስ ገንዘብና የወዳጆቹን የእርዳታ ጦር በመጠቀም ምን ያህል ርቀት መጓዝ እንደሚችል አሳየ፡፡ አሌክሳንደር ልጁ ቄሳር ቦርጂያን መሳሪያው አድርጎ፣ የፈረንሳይን ወረራ እንደ ምቹ

አጋጣሚ በመጠቀም ቀደም ብዬ የቄሳርን አካሄድ በጠቀስኩት መልኩ በርካታ መርህ ግቦችን እውን አደረገ። ምንም እንኳን አላማው ቤተ ክርስቲያኗን ሳይሆን ልጁን ማንገስ ቢሆንም የጳጳሱ ድርጊት የቤተክርስቲያኗን ታላቅነት ጨምሮታል። አሌክሳንደር ከሞተ፣ ልጁም ከስልጣን ሽሚያው ከተወገደ በኋላ ቤተ ክርስቲያኗ የድካማቸውን ፍሬ ለመሰብሰብ ታድላለች።

ከአሌክሳንደር በኋላ ጳጳስ ጁሊየስ ተከሰተ። በርግጥ ጳጳሱ ቀድሞውኑ ቤተ ክርስቲያኗ ታላቅ ሆና ነበር ያገኛት። ሮማኛ በቤተ ክርስቲያኗ ቁጥጥር ስር ነበረች፣ በአሌክሳንደር ሀያልነት የቀድሞዎቹ የሮማ አንጃዎች ወድመዋል። በተጨማሪም ከዚህ ቀደም ታይቶ በማያውቅ መልኩ የሀብት ማከማቻ መንገዶች ተፈጥረዋል። ጳጳስ ጁሊየስ በነዚህ መርህ ግብሮች ከመቀጠል ባሻገር የቀደምቶቹን ይዞታ ማሻሻልም ጭምር ችሎ ነበር። ቦሎኛን ለመያዝ፣ ቬኒሻኖችን ለመደምሰስና ፈረንሳይን ከጣሊያን ግዛት ለማባረር አቅዶ እቅዶቹ ሁሉ ግብ መተውለታል። ከሁሉ በላቀ ደግሞ መርህ ግብሩ የቤተ ክርስትያኗን ታላቅነት እውን ለማድረግ እንጂ ከቤተ ክርስትያኗ ውጪ ማንንም ግለሰብ ለማንገስ ታቅዶ የተካሄደ ስላልነበር ለአስተዋጽኦው የሚቸረው ክበሬታ ከፍ ያለ ነው።

ከዚህም ሌላ የግዛቱን ቀንደኛ ተቀናቃኝ አንጃዎች ኦርሲኒና ኮሎናን በነበሩበት ደረጃ ተቆጣጥሯቸዋል። ከነዚህ ተቀናቃኞች ውስጥ አንዳንድ ችግር ለመማስ የሚጥሩ መሪዎች ባይጠፉም በአንድ በኩል በቤተ ክርስቲያኗ ታላቅነት በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸው የሆኑ ካርዲናሎች ስለሌላቸው ከእቅዳቸው ይሰናከሉ ነበር። አሁን ብፁዕነታቸው አቡነ ሊዮ የጳጳሱን አገዛዝ

በጣም በጠንካራ ሁኔታ ከሀያልነት ጫፍ ላይ ደርሳ ተረክበዋል፡፡ ቀደምት መሪዎቿ በጦር ሀይል ታላቅነቷን እንደገነቡ ሁሉ የአሁኑም ብፁዕነታቸው በደግነታቸውና ተቆጥሮ በማያልቀው ሰናይ ምግባሮቻቸው ይበልጥ ታላቅና ቅዱስ አድርገው እንደሚያዘልቋት ተስፋችን ነው፡፡

# ወታደራዊ ተቋማትና ቅጥረኛ ወታደሮች

## 11. ወታደራዊ ተቋማትና ቅጥረኛ ወታደሮች

የልኡላዊ ግዛቶችን ሁለገብ ጠባዮች፣ (ለምን እንደሚበለፅጉና ለምን እንደሚከስሙ የውድቀትና የብልጽግና መንስኤዎቻቸውን፣ እንዲሁም ግዛቶቹን ለመመስረትና ጠብቆ ለማቆየት የሚረዱ መፍትሄዎችን) ካመላከትኩ በኋላ አሁን ደግሞ አንድ በመሳፍንት የሚተዳደር ግዛት በምን መልኩ እራሱን ከጠላት መከላከልና ማጥቃት እንዳለበት ለማውሳት እወዳለሁ፡፡ አስቀድሜ እንደገለጽኩት አንድ ልኡል በግዛቱ ውስጥ አስተማማኝ መሰረት መጣል ካልቻለ መጨረሻው ውድቀት እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡ እያንዳንዱ ግዛት፣ አዲስም ይሁን ነባር አስተማማኝ መሰረት ሊኖረው የሚችለው ጥሩ ህግና ጠንካራ ሰራዊት ሲኖረው ነው፡፡ ያለጥሩ ሰራዊት ጥሩ ህግ ሊኖር ስለማይችልና ጥሩ ሰራዊት ባለበት ጥሩ ህግ መከተሉ የማይቀር በመሆኑ ህግጋትን ትቼ በሰራዊቱ ላይ አተኩራለሁ፡፡

አንድ ልኡል ግዛቱን ለመከላከል የሚመሰርተው ጦር አንድም የራሱ አሊያም ቅጥረኛ ወይም በእርዳታ የተገኘ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንዴም ሰራዊቱ ከሁሉም የተውጣጣ ሆኖ ይገኛል፡፡ ቅጥረኛና በእርዳታ የሚገኝ ሰራዊት ጥቅም አልባና ጎጂ ነው፡፡ አንድ ልኡል ጦሩን በቅጥረኞች ከገነባ በግዛቱ ውስጥ መረጋጋትን ሊያሰፍንም ሆነ ስልጣኑን አስጠብቆ ሊቆይ አይችልም፡፡ ቅጥረኛ ወታደሮች እርስ በርስ የተከፋፈሉ፣ የስልጣን ጥማት ያሰከራቸው፣ ምግባረ ብልሹና ከዳተኛ ናቸው፡፡ ከወዳጆቻቸው ፊት ጀብደኛ መስለው ቢታዩም ከጠላት ፊት ፈሪ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ቅጥረኛ ወታደሮች ፈሪሀ እግዚአብሄር ያልፈጠረባቸው፣ የአጋሮቻቸውን እምነት ጠብቀው ማቆየት የማይችሉ ከሀዲዎች ናቸው፡፡ ሽንፈትን ስለሚፈሩ ውጊያ ይጠላሉ፡፡ በሰላሙ ጊዜ ቅጥረኞችህ ይመዘብሩሀል፤ በጦርነት ወቅት ደግሞ ጠላት ይደመስስሀል፡፡

ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ ከሚያገኙት ክፍያ ባሻገር ቅጥረኞቹን በታማኝነት የሚያስተሳስር መንገድ አለመኖሩ ነው፡፡ ገንዘብ ብቻውን ደግሞ በሰዎች ላይ እስከሞት መስዋዕትነት የሚያደርስ መሰጠትን አያሰርጽም፡፡ በመሆኑም ቅጥረኞች ሰራዊቱን ለማገልገል ቁርጠኝነት የሚታይባቸው ጦርነት እስከሌለ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ጦርነት ሲከሰት ግን ወይ ይከዱሀል ወይም ይበታተናሉ፡፡ የእውነት ለመናገር በዚህ ጉዳይ ላይ ሀይሌን መጨረስ አልሻም፡፡ ምክንያቱም ለጣሊያን መውደቅ መንስኤው ምንም ሳይሆን ለረዥም ዘመን በቅጥረኛ ወታደሮች ላይ ጥገኛ መሆናችን ነው፡፡ ምንም እንኳን አንዳንዶች በአግባቡ የተጠቀሙባቸው ጊዜያት ቢኖሩም፣ በተለይ ቅጥረኞች

ከቅጥረኞች ጋር ሲዋጉ የተወሰነ ጀብደኝነት ቢታይባቸውም ጣሊያን በውጫዊ ሀይሎች ስትወረር ግን እውነተኛ ማንነታቸው ገሀድ ይታያል፡፡ በዚህ የተነሳ ነበር የፈረንሳዩ ንጉስ ቻርልስ በደካማ ሰራዊት ጣሊያንን መርታት የቻለው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የራሳችን ጥፋት ነው ብሎ የሚያምን ትክክል ነው፡፡ ሆኖም ለሽንፈታችን ምክንያቱ ከላይ የጠቀስኩት እንጂ እሱ በሚያስበው መልኩ አይደለም፡፡ በርግጥ ጥፋቱ የመሪዎቻችንም ጭምር በመሆኑ እነሱም የቅጣቱን ዋጋ መካፈል ነበረባቸው፡፡

ቅጥረኛ ወታደሮችን መጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት ይበልጥ ዘርዘር ባለ መልኩ ለማንሳት እወዳለሁ፡፡ የቅጥረኛ ሰራዊት የበላይ ሀላፊዎች በጦር ስልት የተካኑ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ፡፡ በሁለቱም በኩል ግን ለውድቀት ይዳርጉሀል፡፡ በጦር ስልት የተካኑ የጦሩ ሀላፊዎች የራሳቸውን ታላቅነት ለማስመሰከር ቀጣሪዎቻቸውን ሊገፉ ወይም ከቀጣሪዎቻቸው ፍላጎት በተቃራኒ በሌሎች ላይ ጫና ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ደካማ የሆኑ የቅጥረኛ ጦር ሹማምንት ደግሞ በተለመደው መልኩ ለውድቀት ይዳርጉሀል፡፡ ይህ እውነት ቅጥረኛ በሆነም ባልሆነም ማንኛውም ሰራዊት የሚታይ እውነታ ነው ብሎ የሚሞግት ካለ ምላሼ የታጠቁ ሀይሎች በልኡሉ ወይም በህዝባዊ አስተዳደሩ ቁጥጥር ስር መሆን አለባቸው የሚል ይሆናል፡፡

አንድ ልኡል የራሱን ጦር ሰራዊት ራሱ በግሉ የመቆጣጠር ስልጣኑን ይዞ ወታደሮቹንም ቀጥታ ራሱ ማዘዝ ይችላል፡፡ በህዝባዊ አስተዳደር የሚመራ ግዛትም ከዜጎቹ አንዱን የሰራዊቱ አዛዥ አድርጎ መሾም ይኖርበታል፡፡ የተመረጠው ሰው ደካማ ሆኖ ሲገኝ መቀየርና ሀያል ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ስልጣኑን በህገ

ደንብ መገደብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ቀደም የተስተዋሉ ተጨባጭ ተሞክሮዎች እንዳሳዩን እንደ አለት የጠነከረ ስኬት መቀናጀት የቻሉት የራሳቸው ጦር ያላቸው ልኡላንና ህዝባዊ መንግስታት ብቻ ናቸው፡፡ ቅጥረኞች ከሽንፈት በቀር የሚያተርፉት ነገር የለም፡፡ በራሱ ዜጎች የተዋቀረ ህዝባዊ አስተዳደር የራሱ ጦር ከሌለው በተሻለ በራሱ ዜጋ የመወረር እድሉ ዝቅተኛ ነው፡፡

ሮማ እና ስፓርታ የራሳቸውን ጦር የታጠቁ በመሆናቸው ለበርካታ ክፍለ ዘመናት ነጻ ሆነው ኖረዋል፡፡ ስዊዞችም በሚገባ ስለታጠቁ ሙሉ ለሙሉ ነጻ ሆነው ኖረዋል፡፡ ካርቴዣውያን በተቃራኒው ቅጥረኛ ሰራዊት ላይ ጥገኛ መሆን ምን ያህል ጎጂ እንደሆነ በሚገባ ያመለክታሉ፡፡ ካርቴዣውያን፣ ምንም እንኳን የአመራሩን ቦታ የያዙት የራሳቸው ዜጎች ቢሆኑም ከሮማውያን ጋር የነበራቸው የመጀመሪያ ውጊያ እንደተጠናቀቀ እራሳቸው በቀጠሯቸው ቅጥረኛ ወታደሮች ቁጥጥር ስር ሊውሉ ምንም አልቀራቸውም ነበር፡፡

ኤፓሚኖንዳስ ከሞተ በኋላ ቴቤናውያን የሜቄዶንያውን ፍሊጶስን የሰራዊታቸው ጠቅላይ አዛዥ አድርገው ሾሙት፡፡ ሆኖም ጦርነቱን ካሸነፈላቸው በኋላ ፊሊጶስ የራሳቸውን ነጻነት ገፍፏቸው ነበር፡፡ ሚላኖች ሀገረ ገዢቸው ፊሊጶስ ከሞተ በኋላ ፍራንሲስኮ ስፎርዛን ከቬኒዣውያን ጋር ለነበረባቸው ፍልሚያ ቀጥረውት ነበር፡፡ ሆኖም ካራቫጊዮ ላይ ጠላታቸውን ድል ከነሳ በኋላ ወደ ቀጣሪዎቹ ፊቱን አዙሮ ጦር አነሳ፡፡ የስፎርዛ አባት በኔፕልሷ ንግስት ጆአና ከተቀጠረ በኋላ ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ከድቷት ንግስቲቱ ግዛቷን ለመጠበቅ ለአራጎኑ ፈርዲናንድ ቸሮታ እራሷን አሳልፋ ለመስጠት ተገዳለች፡፡

በርግጥ ቬኒሻውያንና ፍሎረንቲናውያን ሀይላቸውን ለማስፋፋት ቅጥረኛ ወታደሮችን ተጠቅመው ቅጥረኞቹ የቀጣሪዎቻቸውን ስልጣን ሳይቀናቀኑ ተጋድለውላቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ እንደኔ አመለካከት ፍሎረንሶች የሌሎቹ እጣ ያልገጠማቸው እድለኛ ስለነበሩ ነው፡፡ ጠንካራ ቅጥር የጦር አዛዦችን ቢያሰልፉ ኖሮ ውጥረት መከሰቱ አይቀሬ ነበር፡፡ ሆኖም አንዱ ቅጥረኛ የጦር አዛዥ ወታደራዊ ስኬትን መቀናጀት ተስኖታል፤ ሁለተኛው እንደሱ ባለ ተቀናቃኝ ተወጥሮ ነበር፤ ሌላኛው ቅጥረኛ ደግሞ ፍላጎቱ ወደሌላ ነበር፡፡

ከዚህ ባሻገር ከጥቂት ጊዜ በፊት ስለሆነው ክስተት እንመልከት፡፡ ፍሎረንሶች ጦራቸውን ይመራላቸው ዘንድ ብልጣ ብልጡን ፓውሎ ቪቴሊን መረጡ፡፡ ፓውሎ በቅልስልስ ባህሪው ጉዞውን ጀምሮ አቋሙን ቀላል በማይባል ደረጃ አደርጅቶ ነበር፡፡ ፒሳን መቆጣጠር ቢችል ኖሮ በርግጠኝነት ፍሎረንሶች በመዳፉ ስር ይውሉ ነበር፡፡ ምክንያቱም ጠላቶቻቸውን ከፈጀላቸው በኋላ እሱን የመጋፈጥ አቅም አይኖራቸውም ነበር፡፡ እነሱ አገልጋያቸው ሆኖ በግልጋሎቱ እሱን ለመገዛት ይገደዱ ነበር፡፡

የቬኒሻውያንን ጉዳይ ከተመለከትን ደግሞ ድል የሚቀናጁት በራሳቸው ክልል ውስጥ ብቻ እንደነበር እንረዳለን፡፡ ከራሳቸው የጎሳ ወይም የአንጃ መሪዎች ጋር ሲፋለሙ ታላቅ ጀግንነት ይታይባቸዋል፡፡ ሆኖም ከግዛታቸው ወጣ ሲሉ ጀግንነታቸው ተሰልቦ ወደ ተለመደው የጣሊያን ወታደራዊ ልምድ ይመለሳሉ፡፡ መጀመሪያ ላይ መስፋፋት ሲጀምሩ ግዛታቸው የተገደበ ስለነበር አቋማቸውም ቀላል የሚባል ባለመሆኑ ቅጥረኛ የጦር አዛዦቻቸው ስጋት ሊሆኑባቸው

አይችሉም ነበር፡፡ ሆኖም ካራማኞላን የጦሩ አዛዥ አድርገው መስፋፋት ሲጀምሩ የውሳኔያቸውን ግድፈት መጎንጨት ጀመሩ፡፡ በርግጥ ካራማኞላ የሚላኑን ሀገረ ገዥ ድል ነስቶ ጀግንነቱን ማስመስከር ችሎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሂደት ቬኒሻውያን የጦር አዛዡ ተነሳሽነት ከአንገት በላይ መሆኑና ከዚህ በኋላም ሌላ ድል እንደማያመጣላቸው ገባቸው፡፡ ግን ሊያባሩት አልደፈሩም፣ ያስገኘላቸውን እንዳያጡ ሰጉ፡፡ ስለዚህም ለደህንነታቸው ሲሉ ካራማኞላን ለመግደል ተገደዱ፡፡ ከዛም በርቶሎሚዮ ደ ቤርጋሞ፣ ሮቤርቶ ዳ ሳን ሶቨሪኖ እና ፒቲግሊያኖን የመሳሰሉ ሰዎችን የጦር አዛዣቸው አድርገው መረጡ፡፡ በነዚህ ሰዎች የጦር አመራር ወቅት መሰረታዊው ጥያቄ ተጨማሪን የማግኘት ሳይሆን የያዙትን ማስጠበቅ ሆነ፡፡ በቫይላ የተከሰተውም ይኸው ነበር፡፡ ቬኒሻውያን በቫይላ ውጊያ ላይ ስምንት መቶ አመታት ለፍተው የገነቡትን በአንድ ጀምበር ነው የተነጠቁት፡፡

ቅጥረኛ ሰራዊት ቀርፋፋ፣ ዝግመታዊና ረብ አልባ ድልን መጽውቶ ድንገተኛ የሆነ አስደንጋጭ ውድመት ያከናንባል፡፡ ከላይ በጠቀስኳቸው ምሳሌዎች ለረዥም ዘመን በቅጥረኞች ስትነዳ ወደኖረችው ጣሊያን ከተመለስኩ አይቀር ይህን ጉዳይ ይበልጥ ሰፋ አድርጌ ለመዳሰስ እወዳለሁ፡፡ በርግጥ ጅማሮአቸውና አስተዳደጋቸው በሚገባ ከተጤነ ወደ መፍትሄዎቹ ለመቅረብ ይቀላል ብዬ አምናለሁ፡፡

ጣሊያን ከነባሩ ግዛቷ መቆራረጥ የጀመረችው፣ ወደ ተለያዩ ንኡስ ክፍለ ግዛቶች የተበታተነችውና የጳጳሱ ግዛት አቋም የፈረጠመው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተፈጠረው ምህዳር ነው፡፡ ይህም የተከሰተው በበርካታ ትላልቅ ከተሞች በንጉሰ ነገስቱ

አይዞህ ባይነት በሚታገዙት መሳፍንት ጭቆና የተማረሩ ዜጎች አመጽ በማቀጣጠላቸውና ቤተክርስቲያኗም ይዞታዋን ለማዳበር አመጾችን በመደገፏ ነበር፡፡ በዚህ ሂደት በበርካታ ከተሞች ከዜጎች መካከል ልኡላን መፍለቅ ጀመሩ፡፡ በመሆኑም መላዋ ጣሊያን በቤተክርስቲያኑና በተወሰኑ ህዝባዊ መስተዳደሮች ቁጥጥር ስር ወደቀች፡፡ ካህናትና ከተሜዎች በወታደራዊው መስክ ላይ ልምድ ስላልነበራቸው ወታደሮችን ከውጪ መቅጠር ጀመሩ፡፡ በእንዲህ አይነቱ ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ አቋሙን ማዳበር የቻለው የሮማኛው አልቤርጎ ዳ ኮኒዮ ነበር፡፡ ከሱ በኋላ በዘመናቸው የጣሊያን የበላይ የነበሩት ብራቺዮ እና ስፎርዛ ተከሰቱ፡፡ በመቀጠል ደግሞ እስከዚህ ዘመን የነበሩት ቅጥረኞች ተከተሉ፡፡ በውጤቱም ሁላችን እንዳየነው ጣሊያን በቻርልስ ተወረረች፣ በሉዊ ተመዘበረች፤ በፈርዲናንድ ተያዘች፣ በስዊዞች ተጨቆነች፤ ተመዘበረች፤ ተሰቃየች፡፡

ጣሊያን ውስጥ እግረኛ ጦርን የመቀነስ ፖሊሲ መተግበር የጀመረው በነዚህ ሰዎች አማካኝነት ነበር፡፡ ይህንን ያደረጉበት ምክንያት ለገንዘብ ሲሉ የሚያስለጥኑ ሀገር የለሾች እንደመሆናቸው በርካታ ወታደሮችን መቆጣጠር አዳጋች በመሆኑና ጥቂት ወታደሮችን መምራት ደግሞ ዋጋቸውን (ዝናቸውን) ከፍ ሊያደርገው ስለማይችል ነበር፡፡ በመሆኑም ፈረሰኛ ሰራዊትን መጠቀም ከፍተኛ ክብርና ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት የተመቸ ሆኖ አገኙት፡፡ ይህም ሆኖ የፈረሰኞቹ ብዛት የሚችሉትን ያህል መሆን ነበረበት፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሀያ ሺህ ሰራዊት ሁለት ሺህ እግረኛ ጦር ማግኘት እንኳ አዳጋች ሆነ፡፡

ከዚህም ባለፈ ራሳቸውንም ሆነ ወታደሮቻቸውን ስጋት ከሚፈጥሩባቸው ወይም ከፍተኛ ልፋት ከሚጠይቁ ተልእኮዎች ለማራቅ የተቻላቸውን ሁሉ ይጥራሉ፡- የጦር ሰፈሮችን በምሽት አጥቅተው አያውቁም፣ በክረምት ዘመቻ አያደርጉም፣ በጠላት ጦር የተከበቡ እንደሆነ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ አይወስዱም፣ ካምፖቻቸው ዙሪያ ምሽግ ስለመቆፈር ወይም ቦይ ስለመቦርቦር አይጨነቁም፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በወታደራዊ ደንቦቻቸው የተፈቀዱ ናቸው፡፡ ይህን ፖሊሲ የሚከተሉትም አደጋና ልፋትን ለመራቅ ብለው ነው፡፡ ይህን ፖሊሲ ስለሚከተሉም ጣሊያንን ለባርነትና ለሀፍረት ዳርገዋታል፡፡

## 12. የእርዳታ ጦርና ሌሎች ወታደራዊ አመሠራረቶች

የእርዳታ ጦር ሌላኛው ጥቅም አልባ የሰራዊት አይነት ሲሆን ግዛትህን ለመከላከል የሌላ ሀያል ግዛትን እርዳታ በመጠየቅ የሚመሰረት ጦር ነው፡፡ የሮማው ጳጳስ ጁሊየስ በፌራራ ዘመቻ ቅጥረኞችን በማሰለፉ የደረሰውን አሳዛኝ ጉዳት በማጤን ፊቱን ወደ ስፔይኑ ፈርዲናንድ በማዞር የእርዳታ ጦር ይሰጠው ዘንድ ተማጽነዋል፡፡ ከውጫዊ ሀይል የሚገኝ የእርዳታ ጦር ለሰጪው ጠቃሚ ሆኖ ሊገኝ ቢችልም ለተቀባዩ ግን ባብዛኛው ጎጂነቱ ያመዝናል፡፡ የእርዳታ ጦሩን ይዘህ ከተረታህ ትፍረከረካለህ፤ ድል ካደረግክ ደግሞ በቁጥጥራቸው ስር ትውላለህ፡፡ ጥንታዊው ታሪክ በንደዚህ አይነት በርካታ ምሳሌዎች

የተሞላ ቢሆንም ለጊዜው የዘመናችንን ጳጳስ ጁሊየስ ሁለተኛ አስረጂ ማቅረብ በቂ ነው።

ጳጳሱ ፌራራን ለመቆጣጠር ለውጭ ሀይሎች እጁን አሳልፎ ከመስጠት የከፋ አደጋ ፈጽሞ የማይታሰብ ነበር። ሆኖም እንደ እድል ሆኖ የዘራውን ከማጨድ ተረፈ። የእርዳታ ጦሩ ራቬናን እንደደመሰሰ ስዊዞች ከስፍራው ደርሰው ወራሪውን አጠፉት። እራሱ ጁሊየስን ጨምሮ ሁሉንም ባስደመመ ተአምር ጳጳሱ በጠላቶቹ ቁጥጥር ስር ከመዋልም ሆነ የእርዳታ ጦሩ ሎሌ ከመሆን ተረፈ።

ፍሎረንሶች ፒሳን ለመቆጣጠር 1000 የፈረንሳይ ወታደሮችን ቀጠሩ። በዚህ የተነሳ ከመቼውም ጊዜ ለከፋ አደጋ ተዳረጉ። የኮኒስታንቲኖፕሉ ንጉስ አጎራባቾችን ለመቋቋም 1000 ቱርኮችን ወደ ግሪክ ምድር ላከ። ጦርነቱ እንደተገባደደ ግን ጦሩ ግሪክን ለመልቀቅ አሻፈረኝ አለ። እንግዲህ አረመኔዎቹ ግሪክን መግዛት የጀመሩት ከዚህ ጊዜ ወዲህ ነበር።

የእርዳታ ጦር ከቅጥረኛ ሰራዊት የበለጠ ጎጂ ነው። ፍጹም አንድ የሆነና በሆነ ሰው ሙሉ ትእዛዝና ቁጥጥር የሚተዳደር ጦር በመሆኑ በእጅጉ አውዳሚ ነው። ቅጥረኛ ሰራዊት ድል ካደረገ በኋላ በቀጣሪዎቹ ላይ ጉዳት ለማድረስ ጊዜና አጋጣሚ እስኪመቻችለት መታገስ ይኖርበታል። የራሳቸው ወጥ መዋቅር የሌላቸው ባንተ ፈቃድና ክፍያ የሚደራጁ በመሆናቸው የእርዳታ ጦርን ያህል ጉዳት አያደርሱም። ከዛም በተጨማሪ አንተ በመረጥከው ሹም የሚመሩ በመሆናቸው መሪው በአጭር ጊዜ ጉዳት ለማድረስ በቂ ስልጣን አይኖረውም። ጠቅለል ባለ መልኩ

የቅጥረኛ ጦር ጉዳት ወኔ ቢስ መሆኑ ሲሆን የእርዳታ ጦር ጉዳት ከአቅም በላይ ሀያል መሆኑ ነው።

በመሆኑም አስተዋይ የሆነ ልኡል ሁሌም ከእርዳታ ጦር መራቅና የራሱን ሀይል ማደርጀት ይኖርበታል። እውነተኛ ድል በሌሎች ሀይል የሚገኝ ባለመሆኑ አንድ ልኡል በሌሎች እርዳታ ድል ከሚያደርግ ይልቅ በራሱ ጦር በጀግንነት ተጋድሎ ቢሸነፍ ይሻላል።

እዚህ ጋር የቄሳር ቦርጂያን አካሄድ እንደ ምሳሌ ላነሳ እወዳለሁ። ቄሳር መጀመሪያ ላይ ሮማኛን ለመውረር የተጠቀመው የፈረንሳይን የእርዳታ ጦር ነበር። በዚህ ጦር በመታገዝም ኢሞላና ፎርሊን መቆጣጠር ቻለ። ከዚያ በኋላ ግን በእርዳታ ጦር ላይ ጥገኛ መሆን አስተማማኝ አለመሆኑን ተረድቶ ቅጥረኛ ሰራዊት መመልመል ጀመረ። ከእርዳታ ጦር ይልቅ ቅጥረኛ ጦር ዝቅተኛ ጉዳት እንዳለው አመዛዝኖ የኦርሲኒና የቪቴሊ ወታደሮችን ቀጠረ። ሆኖም ተቀጣሪው ሰራዊት አጠራጣሪ፣ የማይታመንና ጎጂ ሆኖ ስላገኘው ቅጥረኞቹን ገሸሽ አድርጎ የራሱን ጦር መገንባት ጀመረ። ቄሳር ከፈረንሳይ የእርዳታ ጦር፣ ከዛም ከኦርሲኒና ቪቴሊ ቅጥረኛ ሰራዊት፣ በመጨረሻም ከራሱ ጦር ጋር በነበረ ጊዜ የነበረውን የአቋም ልዩነት ጠለቅ ብሎ የተመለከተ ማንኛውም ሰው በሶስቱ ሀይሎች መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ መረዳት ይችላል። በእያንዳንዱ ደረጃ የልኡሉ ግርማዊነት እያደገና እየዳበረ ነበር። እውነተኛውን ታላቅነት የተጎናጸፈው ግን ሁሉም ሰው በራሱ ፍጹም የበላይነት የሚተዳደር የራሱ ሰራዊት እንዳለው ሲመለከት ነበር።

ከዚህ ቀደም ያነሳሁትን የሳይራከዙን ሂየሮ ታሪክም ማውሳት ይቻላል:: ሳይራከዞች የሰራዊታቸው አዛዥ አድርገው ሲሾሙት ሂየሮ የሳይራከዛውያን ቅጥረኛ ሰራዊት ረብ አልባ እንደሆነ ለመረዳት ጊዜ አልወሰደበትም:: ይሁን እንጂ ከሰራዊቱ ጋር መቀጠልም ሆነ ጠሩን መበተን የማይቻል ነገር ነበር:: እናም ሂየሮ ቅጥረኛውን ጦር ለያይቶ ከፋፈለው:: ከዛም ከባዕዳውያን ጋር ሳይሆን ከራሱ ወታደሮች ጋር መፋለም ጀመረ::

አንድ በብሉይ ኪዳን ላይ የተጻፈ ታሪክም ላነሳ እወዳለሁ:: ዳዊት የፊሊስጥኤሙን ወደር የለሽ ጎሊያድን ለመፋለም ለሳኦል ጥያቄ አቀረበ:: ሳኦልም ዳዊትን ለማበረታታት የራሱን መሳሪያና ጥሩር አስታጠቀው:: ዳዊት የሳኦልን ጥሩር ከሞከረ በኋላ እንደማይሆኑት ገልጾ ጠላቱን በራሱ ቀስትና ቢላ መጋፈጥ እንደሚፈልግ ገለጸ:: ባጭሩ የሌላ ሰው ጥሩር ሊያንስብህ፣ ሊበዛብህ ወይም ሊጣበቅብህ ይችላል::

የንጉስ ሉዊ 7ተኛ አባት ቻርልስ 11ኛ እርዳታና ጀግንነት በተቀላቀለ ተጋድሎ ፈረንሳይን ከእንግሊዝ ቁጥጥር ነጻ ሲያወጣ የራሱ የሆነ ጦር እንደሚያስፈልገው ተረድቶ ነበር:: ከዚህ በመነሳት ከእግረኛና ፈረሰኛ የተዋቀረ ሚሊሺያ መገንባት ችሎ ነበር:: ሆኖም በቻርልስ እግር የተተካው ልጁ ንጉስ ሉዊ እግረኛውን ሰራዊት እየበተነ የስዊዝ ወታደሮችን መቅጠር ጀመረ:: ይህ ስህተት ከሌሎች የተሳሳቱ እርምጃዎቹ ጋር ተዳምሮ የግዛቲቱን ደህንነት የሚገዳደሩ መሰናክሎች መንስኤ ሆነ:: በሰራዊቱ ውስጥ የስዊዞች የበላይነት ማየል የተቀረውን ጦር በራስ የመተማመን መንፈስ ሰባበረው:: እግረኛው ሰራዊት ሙሉ

ለሙሉ ሲወገድ ፈረሰኛው ደግሞ በውጪ ሀይሎች ላይ ጥገኛ ለመሆን ተገደደ፡፡ የፈረንሳይ ሰራዊት ከስዊዞቹ ጋር መሰለፍን በመላመዱ ያለነሱ እርዳታ ማሸነፍ እንደማይችሉ እራሳቸውን ማሳመን ጀመሩ፡፡ በዚህ የተነሳ ፈረንሳዮቹ ከስዊዞቹ ጋር ሊመጣጠኑ አልቻሉም፡፡ ያለ ስዊዝ እርዳታም ማንኛውንም ሀይል እንደማይመጣጠኑ ያስቡ ነበር፡፡ ፈረንሳይ ትጠቀም የነበረው ከቅጥረኛና ከራሷ ዜጎች የተዋቀረ ጥምር ጦር ነበር፡፡

በርግጥ እንዲህ አይነቱ ጦር ሙሉ ለሙሉ ቅጥረኛ ወይም የእርዳታ ጦር ከሆነ ሰራዊት ይሻላል፡፡ ሙሉ ለሙሉ በዜጎች ከተዋቀረ ጦር አንጻር ሲታይ ግን በእጅጉ ኋላ ቀር ሊባል የሚችል ነው፡፡ የፈንሳይ ታሪክ ብቻውን ምርጥ ማሳያ ነው፡፡ ምክንያቱም ቻርልስ የገነባው ተቋም ቢዳብርና ተጠብቆ ቢቆይ የፈረንሳይ ሰራዊት ወደር የለሽ መሆን በቻለ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሰዎች አስተዋይ ባለመሆናቸው የጎረሱት ምግብ መጣፈጥ ከጀመረ መርዝ ሊኖረው ይችላል ብለው ማሰብ ያቆማሉ፡፡

መጥፎ ነገሮች ሲከሰቱ በወቅቱ መመልከት የማይችል ልኡል አስተውሎ ይጎድለዋል፡፡ በርግጥ ይህ አይነቱን አስተዋይነት የተላበሱ መሪዎች ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ የሮም አወዳደቅ መንስኤ ምን እንደሆነ ጠለቅ ብለን እንመርምር ከተባለ የአወዳደቋ አጀማመር ጎተዎች በቅጥረኛ ሰራዊትነት መካተት ከመጀመራቸው ጋር የሚነሳ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ ትንሽዬ ጅማሮ በራሱ ለሮማውያን ግዛት መዳከም መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ጎተዎች ደግሞ ሮማውያን ያጡትን ጀግንነት እየወረሱ ነበር፡፡

ነገሮችን ለማጠቃለል፡- በራሱ የሚመራ ጦር የሌለው ማንኛውም ግዛት ዋስትናው የተረጋገጠ አይደለም፡፡ በተቃራኒው

አደጋን የሚቋቋምበት ጠንካራና ታማኝ ሀይል ስለሌለው በሌሎች እርዳታ ላይ ጥገኛ ይሆናል፡፡ አስተዋይ የሆኑ ሰዎች ሁሌም እንደሚሉት በራስ ጥንካሬ ላይ ያልተመሰረተ የሀይል ጥማትን የመሰለ ደካማና ተጨባጭ ያልሆነ ነገር የለም፡፡

## 13. አንድ ልኡል ሠራዊቱን ማዋቀር ያለበት እንዴት ነው?

በመሆኑም አንድ ልኡል በማንኛውም ረገድ ሌላ አላማ፣ ሌላ አስተሳሰብ ወይም ክህሎት አያስፈልገውም - ከጦርነት፣ ከጦር ተቋማቱና ከወታደራዊ ግብረ ገብነት በቀር፡፡ ከአንድ መሪ የሚጠበቀው መሰረታዊ ነገር የጦርነትን ጥበብ ማወቅ ነው፡፡ ጠንካራ የጦር ጥበብ በውርስ ያገኙትን ግዛት ከማስጠበቅም ባሻገር ተራ ግለሰቦች የገዢነትን መንበር ይጨብጡ ዘንድ ያስችላቸዋል፡፡

ከጦራቸው ይልቅ ስለ ደስታቸው አዘውትረው የሚጨነቁ መሪዎች ግዛታቸውን ለመነጠቅ ይገደዳሉ፡፡ ግዛትን የመነጠቂያው የመጀመሪያው መንገድ የጦርነትን ጥበብ መዘንጋት ሲሆን ግዛትን ለመመስረት የመጀመሪያው መንገድም በጦርነት ጥበብ መካን ነው፡፡

ፍራንሲስኮ ስፎርዛ በጦር ስልት የተካነ በመሆኑ ከተራ ግለሰብነት ተነስቶ የሚላን ገገር ለመሆን በቅቷል፡፡ ልጆቹ በተቃራኒው የጦርነትን ምንነት በመርሳታቸው ከገገርነት ወደ ተራ ግለሰብነት ወርደዋል፡፡ ካልታጠቅክ እድል ፊቷን

ታዦርብህለች፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች ተግዳሮቶች ተጨማሪ ሰዎች ይንቁህል፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ፊት እንደምናየው አንድ ልኡል አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሎ ሊያስወግዳቸው ከሚገቡ አዋራጅ ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

ግልጽ በሆነ መልኩ በታጠቀና ባልታጠቀ ሀይል መካከል ያለው ልዩነት ከቶውኑ ከንጽጽር የሚገባ አይደለም፡፡ የታጠቀ ሀይል ባልታጠቀ አካል ይገዛል፤ ወይም በታጣቂ ሎሌዎች የተከበበ ያልታጠቀ መሪ ህልውናውን አስጠብቆ ይቆያል ብሎ መጠበቅ አመክንዮን መጻረር ነው፡፡ ነፍጥ ያነገቡ ሎሌዎችን የሚመራ ያልታጠቀ መሪ በአንድ ጎን ሎሌዎችን ሲጠራጠር በሎሌዎች ጎን መሪያቸውን የመናቅ ባህሪ ይሰርጻል፡፡ በሁለቱ ተጻራሪ ጎኖች መካከል ህብርና ስምምነት ሊከሰት አይችልም፡፡ በመሆኑም የጦር ስልት ያልቀሰመ ልኡል ከሚጋበዘው እድለ ቢስ እጣ ፈንታዎች ውስጥ አንዱ በወታደሮቹ አለመከበርና በሎሌዎቹ እምነት ማጣት ነው፡፡

ስለሆነም አንድ ገገር ሀሳቦቹ ከወታደራዊ ስልጠናዎች ፈር እንዳይለቁ መጠንቀቅ አለበት፡፡ ይህንን ልምድ ከጦርነት በላቀ በሰላሙም ጊዜ ቢሆን ያለማቋረጥ መከታተል ይኖርበታል፡፡ ወታደራዊ ስልጠናዎቹ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

አካላዊ ልምምዶችን በተመለከተ አንድ ልኡል ወታደሮቹን በሚገባ ከማሰልጠንና ከማዋቀር ባለፈ አካሉን ከችጋር ለማላመድ አደን መውጣትንና የምድርን አቀብ ቁልቁለቶችን መጋፈጥ የመሳሰሉ የመስክ ልምዶችን ማዳበር አለበት፡፡ ከዚህም ተጨማሪ

የቦታዎችን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥም ማጤን ይኖርበታል፡፡ ተራሮች ምን ያህል ግዝፈት እንዳላቸው፣ ሸለቆዎች ምን ያህል ክፍተት እንዳላቸው፣ ሜዳዎች ምን ያህል ዝርግ እንደሆኑ መመልከትና መሞከር አለበት፡፡ ወንዞች፣ ቁጥቋጦዎች ረባዳማና ረግረጋማ መልክአ ምድሮች ምን እንደሚመስሉ ማጤንና ገፈታቸውን መቅመስ አለበት፡፡

ይህ አይነቱ እውቀትና ተሞክሮ ሁለት አይነት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ አንድ መሪ የቀዬውን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ በሚገባ ከተረዳ የመከላከል ስልቱን በምን መልኩ መቀየስ እንደሚችል የተሻለ ግንዛቤ ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ስለሀገሩ መልክአ ምድር ያለው እውቀትና ተሞክሮ የሌሎች ግዛቶችን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ለማወቅ ይረዳዋል፡፡ ለምሳሌ የቱስካኒ ጉብታዎችና ሸለቆዎች፣ ሜዳዎቹ፣ ወንዙና ረባዳው ስፍራ ከሌሎች ግዛቶች ጋር በእጅጉ የሚያመሳስል በርካታ የጋራ አቀማመጥ ይታይባቸዋል፡፡ ስለዚህ የአንድን ግዛት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ማወቅ የሌሎቹን በቀላሉ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ይህ አይነቱ እውቀት የሚጎድለው ልኡል የልኡልነት መስፈርት ከሚባሉ ባህሪያት አንዱን፣ የጦር መሪነትን ባህሪ ያጓድላል፡፡ ይህ አይነቱ እውቀት የጠላትን መሸሸጊያ ለማወቅ፣ የሰራዊቱን አሰላለፍ ለመምራትና ለውጊያ ለማቅረብ እንዲሁም ምቹ አጋጣሚን ተጠቅሞ ከተማዋን ለመከበብ ይጠቅማል፡፡

የአቼያንሱ መሪ ፍሊፓሚን በታሪክ ተመራማሪዎች ዘንድ ከሚወደስበት ባህሪው አንዱ በሰላሙም ጊዜ ቢሆን ከወታደራዊ ስልቶች በቀር የሚያስበው ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ በሀገሩ ውስጥ

ከወዳጆቹ ጋር እየተዘዋወረ በድንገት ይቆምና የውይይት መድረክ ይከፍታል፡፡ የጠላት ጦር ከወዲያኛ ጉብታ ላይ የእኛ ጦር ደግሞ ከጉብታው ግርጌ እዚያ ቢሰፍር ከሁለታችን የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆነው ማን ነው? ሲል ጥያቄ ያነሳል፡፡ አንድ ወታደር ምድቡን ሳይቆርጥ ሊያጠቃቸው የሚችለው እንዴት ነው? ማፈግፈግ ከፈለግንስ አሰላለፋችን በምን መልኩ መዋቀር ይኖርበታል? እነሱ ሲያፈገፍጉ ለማሳደድ ምቹው መንገድ የቱ ነው?

በውይይታቸው ላይ ይከሰታሉ የሚላቸውን ተግዳሮቶችና መፍትሄዎቻቸውን በዝርዝር ያብራራል፡፡ የነሱን ሀሳብ ያደምጣል፤ የራሱን ያቀርባል፤ በምክንያት ያስተሳስራል፡፡ በዚህ ልምዱ የተነሳ ሰራዊቱን ሲመራ ማንኛውንም አይነት ድንገተኛ ክስተት በአግባቡ የማስተናገድ ብቃቱ በእጅጉ የዳበረ ነበር፡፡

አእምሯዊ ስልጠናዎችን በተመለከተ አንድ ልኡል ታሪኮችን በማንበብ፣ የብልህ ሰዎችን አካሄድ በማጤን፣ በጦርነት ጊዜ የሚከተሉትን ስልት በመመልከት ለድሎቻቸውና ለውድቀቶቻቸው መንስኤዎችን በመመርመር ድሎቻቸውን ለመድገምና ውድቀቶቻቸውን ለማስወገድ መሞከር አለበት፡፡

## 14. ሰዎች፣ በተለይ ልኡላን የሚወደሱባቸውና የሚወገዙባቸው ባህሪያት

አሁን አንድ ልኡል ከወዳጆቹ ወይም ከዜጎቹ ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ በምን መልኩ ባህሪውን መቆጣጠር እንዳለበት

እንመልከት፡፡ በርግጥ ይህን ጉዳይ በተመለከተ በርካታ ጽሁፎች እንደመጻፋቸው አመለካከቴን፣ በተለይም ከተለምዶ የተለዩ ህግጋቶችን ማስቀመጤ ከዘልማድ ያፈነገጠ ደፋር እንደማያሰኘኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ሆኖም ነገራትን ከምናባዊነት ይልቅ እውነታን በተመረከዘ እይታ ማስቀመጡ ጠቃሚ እንደመሆኑ በገሀዱ አለም ተግባራዊ ሊሆኑ በሚችሉት ላይ ማተኮር አግባብ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

በርካቶች ህዝባዊ መንግስታትና ልኡላን በገሀዱ አለም እውን ሊሆን በማይችል መልኩ እንዲሆኑ ይመኛሉ፡፡ ሰው መሆን አለበት ብሎ በሚያስበውና በርግጥ እየሆነ ባለው መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ በመሆኑ በገሀዱ አለም ተግባራዊ የሆኑትን ትቶ በምናባዊ አለም መደረግ አለባቸው ብሎ በሚያስባቸው ላይ ከተጣበቀ እራስን ከማነጽ ይልቅ እራስን ለመናድ ሂደት ይዳረጋል፡፡ በማንኛውም ረገድ በበጎነት ለመንቀሳቀስ የሚዳክር በጎ ላልሆኑ በርካታ ተረፈ ምርቶች ይጋለጣል፡፡ በመሆኑም አንድ ልኡል ገገርነቱን አስጠብቆ ለማቆየት የበጎነትን ተቃራኒ መማርና ጥቅም ላይ ማዋል ይኖርበታል፡፡

ምናባዊ ነገሮችን ገሸሽ አድርገን ነባራዊውን የገሀዱ አለም እውነታን ተመርኩዘን የሰዎችን ባህሪ ስንመለከት (በተለይም ለበርካቶች እይታ የተጋለጡ መሪዎችን)፣ ውዳሴ ወይም ውግዘት የሚቸራቸው የተለያዩ ባህሪያትን እናያለን፡፡ አንዳንዶቹ ቸር ሲሆኑ ሌሎች ንፉግ ናቸው፣ አንዳንዶች ለጋስ ሲሆኑ አንዳንዶች ስግብግብ ይሰኛሉ፣ አንዳንዶች ጨካኝ ሌሎች ሩህሩህ፣ አንዳንዱ እምነት-ቢስ ሌላው አማኝ፣ አንዳንድ ሴታ-ሴት ፈሪ ሌላው ልበ ሙሉ ደፋር፡፡ አንዳንዶች ትሁት አንዳንዶች ኩሩ፣ አንዳንዱ

ሴሰኛ አንዳንዱ ታማኝ፣ አንዳንዱ መሰሪ፣ አንዳንዱ የዋህ አንዳንዱ ሀይማኖተኛ አንዳንዱ ሀይማኖተ ቢስ......

ከላይ ከዘረዘርኳቸው ባህሪያት ውስጥ ልኡላን በጎ የሚያሰኙትን ባህሪያት ማዳበር አለባቸው ቢባል ብዙዎችን የሚያስማማ እንደሚሆን አውቃለሁ:: ይሁን እንጂ በነባራዊው አለም ላይ በሚስተዋሉ ሁናቴዎች አስገዳጅነት የተነሳ ልኡላን እነዚህን ሁሉ በጎ ባህሪያት ሊላበሱ አይችሉም:: በመሆኑም አንድን ልኡል ከመጥፎ ሰብእና ጋር በማቆራኘት ግዛቱን ከሚያስነጥቁት ክፉ ባህሪያት የሚያመልጥበትን መንገድ የሚያውቅ አስተዋይና አርቆ አሳቢ መሆን አለበት:: ሲሆን ያን ያህል የከፋ ጉዳት ከማያደርሱ መጥፎ ምግባሮችም ጭምር መራቅ ቢችል ጥሩ ነው:: ካልቻለ ግን ያን ያህል የከፋ ጉዳት ለማያደርሱ መጥፎ ምግባሮች አብዝቶ መጨነቅ አይኖርበትም:: ግዛቱን ጠብቆ ለማቆየት አስፈላጊ ሆኖ እስከተገኘ ከውግዝ ምግባሮችም ቢሆን ማፈግፈግ የለበትም:: ምክንያቱም ሁሉንም ነገር ከግንዛቤ በማስገባት በጎ ተብለው የሚታሰቡ ምግባሮችን መተግበር ግዛቱን እንደሚያናጉት፣ መጥፎ የሚያሰኙ አንዳንድ ምግባሮች በተቃራኒው ብልጽግናና ዋስትናውን እንደ ሚያረጋግጡለት ይረዳል::

## 15. ለጋስነትና ንፉግነት

ከላይ ከዘረዘርኳቸው የተለያዩ ባህሪያት የመጀመሪያውን ነጥለን ስንመለከት፣ አንድ ሰው ሁሌም ለሁሉም ለጋስ መሆን

ቢችል መልካም በሆነ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የለጋስነትን ባህሪ ስታዳብር መጨረሻህ ክስረት ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ለጋስነትህ ፍጹም በጎና ቅን ሆኖም በሰዎች ዘንድ ከግንዛቤ ሳይገባ ሊታለፍ፣ የምግባርህን ተቃራኒ ገፈት ከመጎንጨት ላይታደግህ ይችላል፡፡

ለጋስ የመባልን ማእረግ ለማግኘት የሚፈልግ የመታያን ገንዘብ በየቦታው መርጨት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መልኩ የሚንቀሳቀስ ልኡል ያለውን ሀብት ከመቅጽበት አሟጦ ይጨርሳል፡፡ እናም ሰብእናውን ጠብቆ ለማቆየት በዜጎቹ ላይ ተገቢ ያልሆነ ቀንበር ለመጫንና ገንዘብ በመሰብሰብ ሰበብ በከፍተኛ ግብር ዜጎቹን ለማንገላታት ይገደዳል፡፡ በዚህም በተከታዮቹ ዘንድ ጥላቻን ያተርፋል፡፡ እራሱን በማደህየቱም በብዙዎች ዘንድ ይናቃል፡፡ በርካቶችን ደቁሶ ጥቂቶችን በሚያበለጽግ ለጋስነቱ የተነሳ የመጀመሪያውን መሰናከል ለመጋፈጥ ይገደዳል፡፡ ይህ መሰናከል ለከባድ ኪሳራም ይዳርገዋል፡፡ ይህን እውነት ተገንዝቦ ወደ ቀድሞ መስመር ለመግባት ሲዳክር ንፉግነትን ይላበሳል፡፡

በመሆኑም አንድ ልኡል በራሱ ኪሳራ ካልሆነ በቀር በብዙዎች ዘንድ ከግንዛቤ የሚገባ ለጋስነትን መላበስ አይችልም፡፡ አርቆ አሳቢ የሆነ ልኡል የንፉግነት ተቀጽላ ቢበጅለት ሊያሳስበው አይገባም፡፡ ንፉግ ሆኖ የራሱ ሀብት ለራሱ በቂ እስከሆነ፣ እራሱን ከጠላት መከላከል ከቻለና በዜጎቹ ላይ ጫና ሳያሳድር አላማውን ማሳካት ከቻለ የለጋስነት ክብር ሊቸረው ይችላል፡፡ በርግጥ ምንም ነገር እንዳልሰጣቸው በሚያስቡ አናሶች

ዘንድ ንፉግ ቢስኝም ከሀብታቸው ምንም እንዳልነጠቃቸው በሚያስቡ ብዙሀን ለጋስነቱን ያረጋግጣል፡፡

በታሪክ ውስጥ እንደተመለከትነው ታላላቅ ትልሞች እውን የሚሆኑት በነዛ ግዛታቸውን በንፉግነት ረግጠው በያዙት መሪዎች ነው፡፡ ጳጳስ ጁሊየስ ሁለተኛ የጳጳስነቱን ግርማ ለመቀናጀት ለጋስነትን የሰብእናው አርማ አድርጎት ነበር፡፡ ስልጣኑን ካረጋገጠ በኋላ ግን አልቀጠለበትም፡፡ ምክንያቱም ጦርነቶቹን በአግባቡ ለመወጣት ስራዊቱን መደጎም ነበረበት፡፡ የፈረንሳይ ንጉስ እነዛን ሁሉ ጦርነቶች ዜጎቹን ተገቢ ባልሆነ ግብር ሳያስቃይ መወጣት የቻለው ከጥንት ጀምሮ ይከተለው የነበረው ንፉግነት የጦርነቶቹን ወጪዎች በራሱ ለመደጎም ስላስቻለው ነበር፡፡ የስፔይኑ ንጉስ በለጋስነት ለመጠራት የሚባዝን አይነት ቢሆን እነዛን ሁሉ እልፍ አእላፍ መርሀ ግብሮቹን በድል ማጠናቀቅ በተሳነው ነበር፡፡

ስለዚህ አንድ ልኡል ተከታዮቹን እስካልመዘበረ፣ እራሱን በራሱ መከላከል እስከቻለ፣ እስካልደኸየና እስካልተናቀ እንዲሁም የድሆችን ንብረት እስካልነጠቀ ድረስ ንፉግ የተሰኘ ተቀጥላ ቢበጅለት ያን ያህል ሊያሳስበው አይገባም፡፡ ምክንያቱም ንፉግነት ግዛቱንና ስልጣኑን ጠብቆ ከሚያቆይባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ምናልባት አንዳንዶች ታሪክን በማጣቀስ እንደቄሳር ያሉ መሪዎች ወደ ስልጣን የወጡትና ከከፍተኛ እርከን የደረሱት በለጋስነታቸው የተነሳ ነው የሚል ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ ለዚህ አመለካከት የሚኖረኝ ምላሽ እንደሚከተለው ነው፡፡ አንደኛውን

ልኡል በሆነ ሰውና ልኡል በመሆን ሂደት ላይ ባለ ሰው መካከል ልዩነት አለ፡፡ ቀድሞውኑ በስልጣን ማማ ላይ የተቆናጠጠ ሰው ለጋስ ሊሆን የሚችለው አስቀድሜ እንደገለጽኩት በራሱ ኪሳራ ብቻ ነው፡፡ ወደ ስልጣን በማምራት ጉዞ ላይ ያለ ሰው ግን ለጋስ ሊሆን ይገባል፡፡ ቄሳር ሮማን ለመቆጣጠር በመፋለም ላይ ከነበሩ ልኡላን መካከል አንዱ ነበር፡፡ ሮማን ከተቆጣጠረ በኋላ ገንዘብ አወጣጡን መግራት ባይችል ኖሮ ግን ከመንበረ ስልጣኑ በተወገደ ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሰራዊታቸው ሀይል ከፍተኛ ስኬትን የተቆናጠጡ በሁሉም ሰው ዘንድ በለጋስነታቸው የሚወሱ ልኡላንም አሉ የሚል ጥያቄም ሊነሳ ይችላል፡፡ ለዚህ ጥያቄ የምሰጠው ምላሽ፡- የራስንና የህዝብን ንብረት በመስጠትና የሌሎችን ንብረት ነጥቆ በመስጠት መካከል ልዩነት አለ፡፡ የራስህን ሀብት በተመለከተ ቁጥብ መሆን ይኖርብሀል፡፡ የምትሰጠው ሀብት የሌሎች እስከሆነ ድረስ ግን ያሻህን ያህል ለጋስ መሆን ትችላለህ፡፡ ሰራዊቱን በባእድ ምድር አዝምቶ የባእዳንን ሀብት በመንጠቅ፣ በማጋዝና በማውደም ጉዞ ላይ ያለ ልኡል የግድ ለጋስ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ አለበለዚያ ሰራዊቱ ልኡሉን ለመከተል ሊያንገራግር ይችላል፡፡ ልክ እንደ ቄሳር፣ ሳይረስና አሌክሳንደር የራስህና የዜጎችህ ባልሆነ ንብረት የፈለግከውን ያህል ቸር መሆን ትችላለህ፡፡ የባእዳንን ንብረት ማከፋፈል ከሀገር ቤት ተቃውሞ አያስነሳብህም፡፡ እንዳውም በለጋስነት ሊያስወድስህ ይችላል፡፡

እራስህን ለጉዳት የምትዳርገው የራስህ የሆነውን ነገር ስትሰጥ ነው፡፡ እንደ ለጋስነት እራስን የሚጎዳ ነገር የለም፡፡ ለጋስ

በመሆን ሂደት ውስጥ የመስጠት ሀይልህን ትነጠቃለህ፡፡ ወይ ትደኸያለህ አሊያም ትናቃለህ፡፡ ከድህነትህ ለማምለጥ ቀማኛ ትሆናለህ ትጠላለህ፡፡ አንድ ልኡል ከማንኛውም ነገር በከፋ መደኸየትና መናቅ የለበትም፡፡ ለጋስነት ደግሞ ለሁለቱም ይዳርግሀል፡፡ በመሆኑም ንፉግነትን መላበስ በእጅጉ የተሻለ ብልህነት ነው፡፡ ንፉግነት ሊያስወግዝህ ቢችልም ለመጠላት አይዳርግህም፡፡ የለጋስነትን ስብእና ለመላበስ መውተርተር ግን ለቀማኛነት በመዳረግ ለጥላቻም ሆነ ለውግዘት አሳልፎ ይሰጣል፡፡

## 16. ጭካኔና ርህራሄ፡- ከመወደድና ከመፈራት የትኛው ይበጃል?

አስቀድሞ ከተዘረዘሩት ባህሪያት ሌላኛው የጭካኔና የርህራሄ ጉዳይ ነው፡፡ በርግጥ በበርካቶች ዘንድ እንደሚታመነው አንድ ልኡል ከጭካኔ ይልቅ ርህራሄን መላበስ ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ ርህራሄን ያላግባብ ከመጠቀም መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ቄሳር ቦርጂያ በጨካኝነት ከሚታወቁት ገዢዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሆኖም ሮማኛን የለወጣት፣ ስርአትንና ለህግ ተገዢነትን አስፍኖ ህብርና አንድነትን የፈጠረው በጨካኝነቱ የመሰረተው አስተዳደር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጨካኝ ላለመባል ሰግተው ፒስቶሪያ እንድትደመሰስ ከፈቀዱት ፍሎረንሶች በላቀ ቄሳር ቦርጂያ ሩህሩህ ነበር ለማለት ያስችላል፡፡

በመሆኑም አንድ ልኡል የዜጎችን አንድነትና ታማኝነት ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ጨካኝ ተብሎ ቢወሳ ሊጨነቅ

አይገባም፡፡ ምክንያቱም አንድ ሁለት ተሞክሮዎችን በማሳየት ከመጠን በበዛ ርህራሄ ተሸብበው ስርአት አልበኝነትን እንዲሰፍን በመፍቀድ ለከባድ ሁከትና የዜጎች እልቂት ከሚዳርጉት በተሻለ ርህራሄ በውስጡ እንዳለ ማሳየት ይችላል፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ ገዢዎች ለጉዳት የሚዳርጉት መላውን ማህበረሰብ ሲሆን ከአንድ ልእል የሚተላለፍ ብይን የሚጎዳው ጥቂቶችን ብቻ ነው፡፡

ከሁሉ በተለየ አዲስ የሆነ ልእል የጭካኔን ምግባር ገሸሽ ማድረግ ፍጹም የማይቻል ሆኖ ያገኘዋል፡፡ በአዲሱ ግዛት ውስጥ የሚስተዋሉ እልፍ አእላፍ ደንቃራዎች ጨካኝነትን ሊወገድ የማይችል ምግባር ያደርጉታል፡፡

ነገር ግን ጨካኝ በመሆን ሂደት ውስጥ ልእሉ የራሱን ጥላ ከመፍራት ደረጃ የሚያደርስ ተጠራጣሪነት እንዳይሰርጽበት መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡ ባህሪው በሰብአዊነት መገራት ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ከልክ ባለፈ በራስ የመተማመን መንፈስ ታውሮ ችኩል ቀንድ ነካሽ እንዳይሆን ወይም ከልክ ያለፈ ጠርጣራነት አቅሉን እንዳያስተው መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡

በዚህ አካሄድ ውስጥ አንድ ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው - ለአንድ ልእል የሚበጀው መወደድ ነው ወይስ መፈራት?

በእኔ አመለካከት መወደድም፣ መፈራትም ሁለቱንም መላበስ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱን በጋራ ማስኬድ በእጅጉ አዳጋች በመሆኑ ሁለቱንም መሆን ካልተቻለ ከመወደድ ይልቅ መፈራት ይበጃል፡፡

የሰው ልጅን ባህሪ በተመለከተ ከአንድ ድምድሜ መድረስ ይቻላል፡- ሰዎች ምስጋና የማያውቁ፣ አስመሳይ፣ ዋሾ፣ አታላይና

ለጥቅም የሚስገበገቡ ፍጥሮች ናቸው፡፡ እስከተንከባከብካቸው ድረስ ያንተ ናቸው፡፡ ደማቸውን ያፈሱልሀል፣ ላንተ ሲሉ ንብረታቸውን፣ ህይወታቸውን፣ ልጆቻቸውን መስዋዕት ያቀርቡልሀል - ግን ይህ እውነት የሚሆነው በዙሪያቸው አደጋ እንደሌለ እርግጠኛ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው፡፡ አደጋ ውስጥ ስትሆን ግን ጦራቸውን ወዳንተ ያዞራሉ፡፡ ሰዎችን ተማምኖ እጅና እግሩን አጣጥፎ የተቀመጠ ገገር ይዞታውን እየናደ መሆኑን መረዳት አለበት፡፡ በታላቅነት ሳይሆን በገንዘብና በጥቅማጥቅም የተገነባ ወዳጅነት የገበያ ሸቀጥ ነው፡፡ ዘላቂነት ሊኖረውም ሆነ ምንም አይነት ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡ ሰዎች ከሚፈሩት ሰው ይልቅ በሚወዱት ሰው ላይ ጉዳት ለመጣል ይደፍራሉ፡፡ በውዴታ ላይ የተገነባ ግንኙነት ሰዎች ረብ አልባ እንደመሆናቸው ግንኙነታቸውን መናድ ጠቃሚ ሆኖ ባገኙበት ቅጽበት ይፈርሳል፡፡ ፍርሀትን መሰረት ያደረገ ግንኙነት ግን ከበስተጀርባው ቅጣትን ያዘለ በመሆኑ ሁሌም ውጤታማ ነው፡፡

ውዴታን ከማትረፍ ይልቅ ፍርሀትን በማስረጽ የተሳካለት ልኡል መወደድን ቢያጣም ከመጠላት ይድናል፡፡ መፈራት መጠላት አይደለም፡፡ ደግሞም የዜጎቹን ንብረት ከመመዝበርና ሴቶቻቸውን ለሀፍረት ከመዳረግ እስከተቆጠበ ድረስ ከጥላቻ መዳን ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ በአንዳንድ ሰዎች ላይ የሞት ብይን ማሳለፍ አስፈላጊ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ መሆን ያለበት ምክንያታዊነትን የተከተለ አግባብነት ያለው መንስኤ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ ከሁሉ ነገር በላቀ ግን የሰዎችን ንብረት ከመንጠቅ መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ፈጠነም ዘገየ ከአባታቸው ቅርስ ይልቅ የአባታቸውን ሞት መርሳታቸው

አይቀርም፡፡ የሰዎችን ንብረት ለመውረስ ሁሌም ሰበብ መፍጠር አያቅትም፡፡ አስተዳደሩን በምዝበራ መምራት የለመደ ልኡል የዜጎችን ሀብት ለመንጠቅ የሚሆን አጀንዳ አያጣም፡፡ የሆነ ሰው ላይ የግድያ ብይን ለማስተላለፍ ግን በቀላሉ ምክንያት ማቅረብ አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ በቀለለ መልኩ ከሰዎች ልቦና ተፍቆ ይጠፋል፡፡

ከሁሉ በላቀ ግን ከሰራዊቱ ጋር በዘመቻ ላይ የተጠመደ፣ ሰፊ ሰራዊት የሚመራ ልኡል ጭካኔን ከመላበስ ማመንታት የለበትም፡፡ ምክንያቱም ይህ ካልሆነ በሰራዊቱ መሀል አንድነትና ወታደራዊ ግብረ ገብነትን ማስረጽ አይቻልም፡፡

በበርካቶች ዘንድ ከሚደነቁ የንጉስ ሀኒባል ጥንካሬዎች ውስጥ አንዱ ያንን ያህል ከተለያዩ ብሄሮችና ጎሳዎች የተውጣጣ ሰፊ ጦር ይዞ ወረራ ሲያካሂድ ነገሮች በመጥፎም ሆነ በጥሩ መንገድ ሲያመሩ በሰራዊቱም ሆነ በአመራሩ መካከል ምንም አይነት አለመግባባት አለመኖሩ ነው፡፡ ለዚህ አይነቱ ስርአትና አንድነት ዋነኛው ተጠቃሽ የንጉሱ ሰብአዊ ያልሆነ ጭካኔ ነበር፡፡ ይህ ባህሪው ነበር ከሌሎች ምግባሮቹ ጋር ተዳምሮ በሰራዊቱ ዘንድ እንዲፈራና እንዲከበር ያስቻለው፡፡ ጭካኔው ባይቀላቀልበት ኖሮ የንጉሱ ሌሎች ምግባሮች በቂ ባልሆኑ ነበር፡፡ የታሪክ ተመራማሪዎች ለዚህ እውነት ተገቢውን አጽንኦት ሳይሰጡ የሀኒባልን ውጤታማነት ያሞካሻሉ፡፡ የጥንካሬው መሰረት የሆነውን ባህሪውን እያወገዙ ውጤታማነቱን ያደንቃሉ፡፡

ከጭካኔው ውጪ ያሉት ሌሎች ጠንካራ ጎኖች ብቻቸውን ለደረሰበት የታላቅነት ደረጃ በቂ እንዳልሆኑ ለማሳየት በጊዜውም

ሆነ በታሪክ መዝገብ ላይ ልዩ ስፍራ የነበረውን ሮማዊ የጦር አዛዥ ሲፒዮን ታሪክ እንመልከት፡፡ በአንድ ወቅት የሲፒዮ ወታደሮች በስፔይን ውስጥ አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ለገሙበት፡፡ ለዚህ ችግር መንስኤው የሲፒዮ ልዝብተኝነት ነበር፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ሰራዊቱ ወታደራዊ ስርአትን ባልተከተለ መልኩ ባልባለገ ነበር፡፡ በዚህም ፋቢየስ ማክሲሙስ ሲኔት ቀርቦ "የሮማውያንን የጦር ብሂል ያጨቀየ!" ሲል ዘልፎታል፡፡ በዚህም ሳያበቃ በድጋሚ ሎክሪ ከባለስልጣናቱ በአንዱ ስትዘረፍ ሲፒዮ የሎክሪን ነዋሪ ለመካስም ሆነ ባለስልጣኑን ለመቅጣት የወሰደው እርምጃ አልነበረም፡፡ የዚህም መንስኤው የሲፒዮ ልል የሆነ ተፈጥሮ ነው፡፡ ጥፋቱን ለማስተዛዘን የተወሰኑ ሴናተሮች በርካቶች እራሳቸውን ከስህተት በማረቅ የተካኑ የሆኑትን ያህል ሌሎችን ከስህተታቸው ማረቅ አይችሉም በሚል ማስተባበያ ተሟገቱለት፡፡ ሲፒዮ በልዝብተኝነቱ ቢቀጥል ኖሮ ባህሪው ዝናውንና ታላቅነቱን ባኮላሸበት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሲፒዮ ይህንን ለዘብተኛ ባህሪውን ከመግራት ባሻገር ታላቅ የጦር አበጋዝ ለመሆን ችሎ ነበር፡፡

ስለዚህ መፈራትንና መወደድን በማነጻጸር ለሚነሱ ጥያቄዎች፣ አንዳንድ ሰዎች ልኡሉን የሚወዱት በፈቃዳቸው ሲሆን የሚፈሩት ግን በልኡሉ ፍቃድ ነው። አስተዋይ ልኡል ደግሞ የሚቆጣጠረውን ነገር ትቶ ሊቆጣጠር የማይችለውን ነገር መምረጥ የለበትም ስል አጠቃልላለሁ፡፡

# 17. ልኡላን ቃላቸውን ማክበር ያለባቸው በምን መልኩ ነው?

አንድ ልኡል ሁሌም ቃሉን መጠበቅ ቢችልና ከማጭበርበር ይልቅ ግልጽና ቀጥተኛ ቢሆን ምን ያህል መልካም እንደሚሆን ሁሉም ሰው ያውቃል፡፡ ነገር ግን የዘመናችን ሁነኛ ተምሳሌቶች እንደሚያመላክቱት ታላላቅ ትልሞችን እውን ለማድረግ የቻሉ ልኡላን ቃላቸውን በቀላሉ የሚሰጡ፣ በብልጠታቸው እንዴት ሰዎችን ማታለል እንዳለባቸው የሚያውቁና በስተመጨረሻ ክፍተቶቻቸውን በብዙሀኑ ዘንድ ተቀባይ በሆኑ መርሆዎች ማሰር (ሥራ ላይ ማዋል) የሚችሉ ገዢዎች ናቸው፡፡

ስለሆነም ሁለት አይነት የፍልሚያ መንገዶች እንዳሉ መረዳት ያስፈልጋል - አንድም በህግ አሊያም በጉልበት፡፡

የመጀመሪያው መንገድ ለሰዎች ተፈጥሯዊ የሆነ መንገድ ሲሆን ሁለተኛው የአራዊቶች ተፈጥሮ ነው፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያው መንገድ አብዛኛውን ጊዜ በቂ ሆኖ ስለማይገኝ በሁለተኛው መንገድ መታገዝ ተገቢ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ አንድ ልኡል ሰዋዊነትንም ሆነ አራዊትነትን እንከን አልባ በሆነ መንገድ የመጠቀም ምርጥ ችሎታ ሊኖረው ይገባል፡፡

አውሬነትን መላበስ አስፈላጊ እንደመሆኑ አንድ ልኡል የአውሬነትን ባህሪ ከቀበሮና አንበሳ መቅሰም ይኖርበታል፡፡ አንበሳ እራሱን ከወጥመድ መታደግ አይችልም፤ ቀበሮ ደግሞ ተኩላን መቋቋም ይቸግረዋል፡፡ ስለዚህ ወጥመዶችን ለማወቅ ሰው

ቀበሮን መሆን አለበት፤ ተኩላዎችን ለማስበርገግ ደግሞ አንበሳ መሆን ይኖርበታል፡፡ እነዛ እንደ አንበሳ ብቻ የሚንቀሳቀሱት ደደቦች ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት አስተዋይ ልኡል የገባው ቃል አደጋ ላይ የሚጥለው ሆኖ ሲገኝ ወይም በወቅቱ ቃል የገባበት ምክንያት አሁን እንገብጋቢ ጉዳይ ካልሆነ ወይም በዚህ ሰዓት ህልውና ከሌለው የግድ ቃሉን መጠበቅ (ማክበር) አይጠበቅበትም፡፡ ማድረግም የለበትም፡፡

ሁሉም ሰው ጥሩ፣ ደግ ቢሆን ኖሮ ይህ አካሄድ መጥፎ ሊባል ይችል ነበር፡፡ ሆኖም ሰዎች ረብ አልባ በመሆናቸው የገቡልህን ቃል እንደሚያፈርሱ ሁሉ አንተም የገባህላቸውን ቃል የመጠበቅ ግዴታ አይኖርብህም፡፡ ደግሞም መጥፎነቱን በበጎ ማስተዛዘኛ (በጥሩ ጥሩ ምክንያቶች) መቀባባት የሚሳነው ገዢ አይኖርም፡፡ በገዢዎች መጥፎነት ሳቢያ የተሰረዙ ውሎችና የፈረሱ ቃሎችን በመዘርዘር እልፍ አእላፍ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዛ ቀበሮነትን በሚገባ የተካኑቱ በርግጥ ከሁሉ በላይ ነጥረው ይወጣሉ፡፡ በዚህ አካሄድ ድል ለመንሳት መጥፎ አድራጎትን ቀባብቶ ማቅረብ፣ የተካነ ዋሾና አታላይ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች እንደየሁኔታው የሚለዋወጡ ቀላል ፍጡራን በመሆናቸው ለማታለል ዝግጁ የሆነ ሰው የሚታለልለት አካል አያጣም፡፡

አሌክሳንደር 6ተኛ ሰዎችን ከማታለል የዘለለ ተአምር ሰርቶ አያውቅም፡፡ ሁሌም የብልጠቱ ሰለባ የሚሆኑ ተጠቂዎችም አጥቶ አያውቅም፡፡ እንደሱ ማህላ የሚደረድር፣ ግን በቀላሉ ቃሉን የሚያፈርስ ሰው የለም፡፡ ይህም ሆኖ የማታለል ተግባሩ

ሁሌም የታለመውን ግብ ይመታል፡፡ ምክንያቱም ጳጳሱ በመስኩ የረቀቀ ጠቢብ ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ልኡል የግድ በጎ የተባሉ ምግባሮችን ሁሉ ተላብሶ መገኘት አይጠበቅበትም፡፡ ሆኖም በብዙሀኑ ዘንድ እንደ መልካምነት የሚቆጠሩ ምግባሮችን የተላበሰ መስሎ መታየት አለበት፡፡ እንዳውም እነዚህ ባህሪያት እውነተኛ ባህሪዎቹ ከሆኑና ሁሌም በጎ ባህሪን ተመስርቶ የሚንቀሳቀስ ከሆነ ለጉዳት ይዳረጋል፡፡ መልካምነትን ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻለው መስሎ በመታየት እንጂ በመተግበር አይደለም፡፡ በመሆኑም ሁሌም ሩህሩህ፣ ቃሉን ጠባቂ፣ ደግ፣ የዋህና አላማ ጽኑ መስሎ መታየት አለበት፡፡ በርግጥ ሆኖ መገኘትም ይኖርበት ይሆናል፡፡ ነገር ግን ባህሪው ተቃራኒውን ሆኖ መገኘት በሚያስፈልግበት ወቅት በምን መልኩ መሆን እንደሚቻል ጠንቅቆ ማወቅ አለበት፡፡

ከግንዛቤ መግባት ያለበት ሀቅ፣ አንድ ልኡል በተለይ አዲስ ልኡል በሰዎች ዘንድ መልካምነትን የሚያላብሱ ባህሪዎችን ሁሉ ሊከተል እንደማይችል ነው፡፡ ምክንያቱም ግዛቱን ጠብቆ ለማቆየት ደግነትን፣ ቸርነትን፣ ሀቀኝነትንና ሀይማኖተኛነትን... ገሸሽ ለማድረግ የሚገደድባቸው አጋጣሚዎች የትየለሌ ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑ እድልና ሁኔታዎች በሚያዙት መልኩ የሚለዋወጥ ባህሪ ሊኖረው ይገባል፡፡ አስቀድሜ እንደገለጽኩት በጎነትን ማንጸባረቅ በሚችልበት አጋጣሚ ሁሉ ከመልካምነት ማፈንገጥ የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰይጣናዊነትንም መላበስ መቻል አለበት፡፡

ነገር ግን አንድ ልኡል አስቀድሜ ከዘረዘርኳቸው አምስት የበጎነት ባህሪያት የማይመነጭ አንድም ቃል ትንፍሽ እንዳይል

አበክሮ መጠንቀቅ አለበት፡፡ በዙሪያው በቅርበት ሆነው ለሚታዘቡትና ለሚያደምጡት ሁሉ ለርህራሄ፣ ለደግነት፣ ለጽናት፣ ለሀቀኝነትና ለሀይማኖነተኝነት የተሰጠ መስሎ መታየት አለበት፡፡

ሰዎች ባጠቃላይ ከእጃቸው ይልቅ በአይናቸው ይመዝናሉ፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ሰው የመመልከት እድል አለው፣ ቀርቦ ለመንካት የሚታደለው ግን ጥቂቱ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ሁሉም ሰው መስለህ ለመታየት የምትሞክረውን ነው የሚመለከተው፡፡ አንተን በተግባር የሚፈትኑህ ወይም እውነተኛ ማንነትህን የሚያውቁ ጥቂቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥቂቶች ደግሞ በግዛቱ ግርማዊነት ጥላ ስር በታቀፉ ብዙሀን ላይ ተቃውሞ የማንሳት ድፍረቱ አይኖራቸውም፡፡ የማንኛውም ሰው ድርጊት በተለይ የልኡላን፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት እስከሌለ ድረስ የሚዳኘው በሚያስመዘግበው ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ልኡሉ ግዛቱን በሚገባ መቆጣጠርና ጠብቆ ማቆየት ብቻ ይቻል፡፡ ይህ ሲሆን የሚጠቀማቸው መንገዶች ሁሉ የተከበሩና በአለም ዙሪያ የሚወደሱ ይሆናሉ፡፡ ተርታው ማህበረሰብ ሁሌም በታይታና በውጤት እንደተደመመ ነው፡፡ ትኩረት ሊቸረው የሚገባው ደግሞ ለብዙሀኑና ለተርታው ነው፡፡ ብዙሀኑ በግዛቲቱ (በመንግሥቱ) እስከተደገፈና እስከታቀፈ ጊዜ ድረስ ለጥቂቶቹ የሚሆን ቦታ አይኖርም፡፡ የአራጎኑ ፈርዲናንድ ከሰላምና ከመልካም እምነት ውጪ አንዳችም ነገር ሰብኮ አያውቅም፡፡ በተግባር ግን የሁለቱም ነገሮች ጠላት ነው፡፡ በርግጥ ከሁለቱ ለአንዱ ከበሬታ ቢኖረው ኖሮ ሀይሉን ወይም ግዛቱን ስንት ጊዜ በተነጠቀ ነበር፡፡

# የህዝብ ጥላቻንና ንቀትን የማስወገድ ጠቀሜታ

## 18. የህዝብ ጥላቻንና ንቀትን የማስወገድ ጠቀሜታ

አስቀድሜ ከዘረዘርኳቸው ባህሪያት ዋና ዋናዎቹን በስፋት ተመልክተናል፡፡ የተቀሩትን ባህሪያት ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ እሞክራለሁ፡፡ ከሁሉም ነገር በላይ አንድ ልኡል ለመጠላትና ለመናቅ የሚዳርገውን ማንኛውም ነገር ማስወገድ አለበት፡፡ እነዚህን ሁለት አስከፊ ነገሮች ማስወገድ ከቻለ የሚያደርገው ነገር ሁሉ መደረግ ያለበትን ይሆናል፡፡ የህዝብ ጥላቻና ንቀትን ማስወገድ እስከቻለ ድረስ በሌሎች የከፋት ባህሪያቱ ከሚገጥመው አጸግብሮት ስጋት መዳን ይችላል፡፡

ከሁሉ ነገር በላቀ አንድ ልኡል ሊጠላ የሚችለው የህዝቡን ንብረት ያላግባብ ሲመዘብርና እንስቶቻቸውን ሲያዋርድ ነው፡፡ በመሆኑም ከነዚህ አፍራሽ ባህሪያትና ድርጊቶች መታቀብ ይኖርበታል፡፡ የብዙሀኑን ንብረት እስካልነጠቀና የክብር ግዛታቸውን እስካላደፈረሰ ድረስ ዜጎች በልኡሉ ሳይከፉ የእለት ተእለት ኑሯቸውን በሰላም ይቀጥላሉ፡፡ ከዚህ በተረፈ

የሚጠበቅበት ከጥቂቶቹ ወገኖች ጋር መታገል ብቻ ነው፤ ይህም ቢሆን ለየት ባለ አካሄድና ቀላሉ ሊፈታው ይችላል፡፡

በሌላ መልኩ አንድ ልኡል በህዝቡና በሎሌዎቹ ዘንድ ንቀትን ሊያተርፍ የሚችለው በአቋሙ ልል፣ ደካማ፣ ፈሪና ወላዋይ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ እንደዚህ ያሉትን መራኸ ባህሪያት በቆራጥነት በመፋለም አቋሙ ጽኑነትን፣ ድፍረትንና ጥንካሬን በማዳበር ማስወገድ ይኖርበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሎሌዎቹ መካከል የሚከሰቱ ቅራኔዎችን ሲፈታ፣ ፍርዶቹ ፍጹም የማይቀለበሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ማንም ሰው እሱን የማታለል ወይም የማጭበርበር ቀቢጸ ተስፋ እንዳያድርበት ነገሮችን ጥልቅ በሆነ አትኩሮት መከታተል አለበት፡፡ በዚህ መልኩ እራሱን ማነጽ የቻለ ንጉስ ስለራሱ ያለው አመለካከት በሚገባ የዳበረ ይሆናል፡፡ በእንዲህ አይነቱ በከፍተኛ ክብርና ግርማ በታጀበ ልኡል ላይ ማሴርም ሆነ ጥቃት መቃጣት በእጅጉ አዳጋች ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ልኡሉ ታላቅነቱን ማስመስከርና የህዝቡን ከበሬታ ማረጋገጥ ሲችል ነው፡፡

አንድ ልኡል ስልጣኑን በተመለከተ ሁሌም ሊፈራቸው የሚገባ ሁለት ነገሮች አሉ፡፡ አንደኛው የሎሌዎቹን ውስጣዊ መፈንቅለ መንግስት ሲሆን ሌላኛው የውጫዊ ሀይሎች ወረራ ነው፡፡ ሁለተኛውን እንቅፋት ለመከላከል ጠንካራ ሰራዊትና መልካም አጋሮች ሊኖሩት ይገባል፡፡ ውስጣዊ ንቅናቄዎች በውጫዊ ግንኙነቶች እስካልታገዙና ውስጣዊ ሴራዎች ሁከት እስካልፈጠሩ ድረስ የሀገር ውስጥ ጉዳዮች በአስተማማኝ ሁኔታ በቁጥጥር ስር ሊውሉ ይችላሉ፡፡ ከውጫዊ ሀይሎች ሁከት ቢከሰት እንኳ ልኡሉ አስተዳደሩን በሚገባ መምራት ከቻለ፣ እስካሁን

በጠቀስኩት መልኩ ከተንቀሳቀሰና ለውጫዊ ሀይሎች በቀላሉ እስካልተንበረከከ ድረስ እያንዳንዱን ድንገተኛ አደጋ መሻገር ይችላል፡፡

አንድ ልኡል ከውጫዊ ሀይሎች ሁከት ነጻ ከሆነ ዋነኛው የስጋት ምንጩ ሊሆን የሚገባው ውስጣዊ የሆኑ ድብቅ ሴራዎች ጉዳይ ነው፡፡ ልኡሉ ከዚህ አይነቱ ፈተና እራሱን ማዳንና መከላከል የሚችለው ደግሞ የብዙሀኑን ጥላቻና ንቀት በማስወገድና የህዝቡን ፍላጎት በማሟላት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም እንደገለጽኩት ስልጣንን ጠብቆ ለማቆየት ይህ በእጅጉ ወሳኝ ነገር ነው፡፡ አንድ ልኡል ከውስጣዊ ሴራዎች እራሱን ከሚከላከልባቸው መንገዶች ውስጥ ዋንኛውና ሀያሉ መፍትሄ በህዝብ መጠላትን ማስወገድ ነው፡፡ ምክንያቱም ድብቅ ሴራዎችን የሚጠነስስ ሰው ሁሌም የሚያስበው ንጉሱን በመግደል ህዝቡን ማስደሰት እንደሚችል ነው፡፡ ሆኖም ንጉሱን መግደል ህዝቡን የሚያስቆጣ ድርጊት እንደሆነ ካወቀ እቅዱን ከጫፍ የማድረስ ድፍረት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም በመንገዱ ላይ የሚጋረጡ ህልቆ መሳፍርት የሌላቸው መሰናክሎች አሉና፡፡

ከታሪክ እንደምንረዳው በአለማችን ላይ በርካታ ሴራዎች ተካሂደዋል፤ ግባቸውን መምታት የቻሉት ግን ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ሴራውን የሚጠነስሰው ሰው የሌሎችን እርዳታ ማግኘት ስላለበት ነው፡፡ ድጋፍ ሊያደርጉለት የሚችሉት ደግሞ በአስተዳደሩ እርካታ ያጡ፣ የተማረሩና ተስፋ የቆረጡ ብቻ ናቸው፡፡ ሆኖም ሴራ ጠንሳሹ ምስጢሩን ባዋየ ቅጽበት ለሰሚው ፍላጎቱን የሚያሟላበትን እድል ይከፍትለታል፡፡ ምክንያቱም የሚያውቀውን በመናገር ያጣውን ሁሉ የማግኘት

ተስፋ ሊያድርበት ይችላል፡፡ ሴራውን በማሳበቅ የሚያገኘውን ትርፍና በሴራው መካፈል የሚያስከትለውን አደጋ አመዛዝኖ አብሮህ ለመጓዝ የሚፈቅድ ካለ አንድም በርግጥ ፍጹም የሆነ ወዳጅ መሆን አለበት አሊያም በምንም የማይመለስ የንጉሱ ፍፁም ጠላት መሆን አለበት፡፡ በአጭሩ ለማስቀመጥ በጠንሳሹ ወገን መፈንቅለ መንግስት ማሰብ ከፍርሀትና አሰቃቂ ቅጣት በቀር የሚታየው ነገር አይኖርም፡፡ በልኡሉ ወገን የሚኖረው ደግሞ የገዥነቱ ግርማዊነት አለ፤ ግርማዊነቱን የሚጠብቁ ጽኑ ህጎች አሉ፤ የግዛቲቱና የግዛቲቱ አጋሮች ሀይልም አለ፡፡ በዚህ ሁሉ የህዝቡ ድጋፍ፣ የህዝቡ መልካም ይሁንታ ተጨምሮበት፡፡ ታዲያ ይህንን ሁሉ እየተመለከቱ ማሴር የማይታሰብ ነገር ነው፡፡ በተለምዶ ሴረኛውን የሚያስፈራው ሴራውን እውን ከማድረጉ በፊት የሚገጥመው እንቅፋት ሲሆን ህዝብ በሚወደው ላይ የሚያሴር ግን ሴራውን ማሳካት ቢችል እንኳ የሚገጥመውን የህዝብ ጥላቻ በማሰብ ይፈራል፡፡ ወንጀሉን ማሳካት ቢችል እንኳ መላው ህዝብ ተጻራሪው ስለሚሆን የሚሸሸግበት ጥግ አይኖረውም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ እልፍ ምሳሌዎችን መዘርዘር ቢቻልም በአባቶቻችን ዘመን የተከሰተ አንድ ምሳሌ በማውሳት አስረጂ ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡ የካኔቺ ቤተሰቦች በሴራ ተነሳስተው የቦሎኛውን ልኡል አኒባል ቦንቲቮግሊን ገደሉት፡፡ ከቦንቲቮግሊ የቀረው ብቸኛው ወራሽ ገና የሽንት ጨርቁን ያልጣለው አልጋ ወራሽ ጂዮቫኒ ነበር፡፡ የልኡሉ ሞት መንስኤ የሰው እጅ መሆኑ በግዛቲቱ ውስጥ በታወቀ ቅጽበት ህዝቡ በአድሞ ተነስቶ መላው የካነስቺን ቤተሰብ ፈጀው፡፡ ህዝቡ በካኔቺ ላይ በአንድነት አብሮ እንዲነሳ የገፋፋው ሀይል ለቦንቲቮግሊ የነበረው ድጋፍና ይሁንታ

ነበር፡፡ አስደናቂው ነገር ከቦንቲቮግሊ የተረፈ ሀላፊነት ለመቀበል የሚበቃ የቤተሰብ አባል ባይኖርም የቦሎኛ ነዋሪዎች በፍሎረንስ ውስጥ የሚኖር የብረት ቀጥቃጭ ልጅ ነው ተብሎ ይታሰብ የነበረ አንድ ቦንቲቮግሊ እንዳለ ጭምጭምታ ሰምተው ሊፈልጉት ሄዱ፡፡ ከዚያም እንደ ባላደራ አስተዳደር ስልጣን ሰጥተውት ህጻኑ ጂዮቫኒ የግዛቲቱን መስተዳድር ለመቀበል እስኪበቃ ድረስ ቦሎኛን ሲያስተዳድር ቆየ፡፡

ከዚህ በመነሳት፣ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀመጥ አንድ ልኡል የህዝብ ይሁንታ እስካለው ድረስ ድብቅ ሴራዎች ሊያሳስቡት አይገባም፡፡ ሆኖም ህዝቡ የልኡሉ ተጻራሪ ሆኖ ልኡሉን በጥላቻ አይን የሚመለከት ሲሆን ልኡሉ እያንዳንዱን ሰውና አጋጣሚ ሊፈራ ይገደዳል፡፡ በአግባቡ የተዋቀሩ ግዛቶችና አስተዋይ ገገርዎች መሳፍንቶቻቸውን ላለማማረርና የህዝባቸውን ፍላጎት ለማሟላት አስቸጋሪ የሆኑ መሰናክሎችን ሁሉ ይጋፈጣሉ፡፡ በርግጥ አንድ ልኡል ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገቡ ወሳኝ ነገሮች አንዱ ይህ መሆን አለበት፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን በጥሩ ሁኔታ ከተዋቀሩና በአግባቡ ከሚተዳደሩ ግዛቶች መካከል አንዷ የፈረንሳይ ግዛት ነች፡፡ ፈረንሳይ የንጉሱን የውሳኔ ነጻነትና የስልጣኑን ደህንነት ጠብቀው የሚያቆዩ በእጅጉ ጠቃሚ ተቋማት አሏት፡፡ ከነዚህ ተቋማት አንዱ የሀገሪቱ ፓርላማ ነው፡፡ የፈረንሳይ ግዛት መስራች የመሳፍንቱን የስልጣን ጥማትና ብልግና በመረዳት የተወሰነ ድርሻ ሰጥቶ መገደብ እንዳለበት የተረዳ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ ለመሳፍንቱ ያለውን ፍርሀትና ጥላቻ በመገንዘብ በተወሰነ መልኩ ዋስትናውን ማረጋገጥም ተገቢ ነበር፡፡ ሆኖም

ይህ የንጉሱ ሀላፊነት መሆን እንደሊለበት ያውቃል፡፡ ምክንያቱም መሳፍንቱ ለህዝቡ በማድላቱ ህዝቡ ደግሞ በፊናው ለመሳፍንቱ በመወገኑ እንዳይወቀስ መጠንቀቅ ነበረበት፡፡ ከዚህ በመነሳት የመሳፍንቱን ሀይል አዳክሞ ህዝቡን ለመደገፍ ንጉሱ ላይ ምንም ወቀሳ በማይጋርጥ መልኩ ነጻ የሆነ ተቋም መሰረተ፡፡ በርግጥ የንጉሱንና የግዛቱን ዋስትና ለማረጋገጥ ከዚህ የተሻለ ምቹ መፍትሄ ሊኖር አይችልም፡፡

ከዚህ ተሞክሮ አንድ በትኩረት ሊታይ የሚገባ ነገር አለ፡፡ አንድ ልኡል ህዝባዊ ተቀባይነትን የሚያሳጡ አስከፊ እርምጃዎችን ሲወስድ የተጠያቂነቱን ድርሻ ለበታች ሎሌዎች ማከፋፈል አለበት፡፡ ህዝባዊ ውዳሴን ከሚያጎናጽፉ እርምጃዎች ደግሞ የእራሱን ድርሻ መቀበል አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ልኡል በስሩ ለሚገኙ መሳፍንት የሚገባቸውን ዋጋ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህም ሆኖ ግን የህዝብ ጥላቻን እንዳያተርፍ መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡

እዚህ ጋር የሮማውያን ነገስታትን አኗኗርና አሟሟት በጥልቀት ያጤኑ በርካቶች የነገስታቱን ታሪክ አስረጂ በማድረግ ሀሳቤን ሊሞግቱ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስጥ መንገድ የተከተሉ፣ ጠንካራ አስተዳደራዊ ሰብእና ያሳዩ ነገስታት ከጥንካሬያቸው በተቃራኒ ከስልጣናቸው ወድቀዋል፡፡ ከዚህም በከፋ አንዳንዶቹ በራሳቸው የቅርብ ሰዎች ሴራ ተገድለዋል፡፡ ለነዚህ ሙግቶች አጥጋቢ ምላሽ ለመስጠትና፣ የአወዳደቃቸው መንስኤ እኔ ከጠቀስኳቸው የተለየ እንዳልሆነ ለማመልከት የተወሰኑ የሮም ነገስታትን ታሪክ ላወሳ እወዳለሁ፡፡ ከፈላስፋው ማርከስ እስከ ማክሲሙንስ ድረስ የነገሱትን ኮሞደስ፣ ፐርቲናክስ፣

ሴቨሩስ፣ ካራካላ፣ ማክሪናስ፣ ሄሊዮጋባላስና የአሌክሳንደርን የስልጣን አካሄዶች እጠቅሳለሁ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ከግንዛቤ ሊገባ የሚገባው ጉዳይ ብዙዎቹ ልኡላን የሚገጥማቸው ተግዳሮት የመሳፍንቶቻቸውን የስልጣን ጉጉትና የህዝባቸውን ስርአት አልበኝነት መጠበቅ ሲሆን፣ የሮም ነገስታት ከዚህ ባለፈ ሶስተኛ መሰናክል አለባቸው፡፡ የሮም ነገስታት ከመሳፍንቶቻቸውና ከህዝባቸው በተጨማሪ የጨካኝ፣ ጨቋኝ ወታደሮቻቸውን ፍላጎትም ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ በእጅጉ አዳጋች በመሆኑ ለበርካቶች መውደቅ መንስኤ ሊሆን ችሏል፡፡ ምክንያቱም የወታደሩንና የህዝቡን ፍላጎት በአንድ ላይ ማሟላት በቀላሉ የሚሳካ አይደለም፡፡ በአንድ ጎን ህዝቡ ሰላም ወዳድ እንደመሆኑ አደገኛ ያልሆኑ ሰላማዊ ነገስታትን ይፈልጋል፡፡ በሌላ መልኩ ከህዝቡ በተቃራኒ ወታደሩ ጦረኛ የሆነ እብሪተኛ፣ ጨካኝና ነጥቆ አዳሪ ነገስታትን ይፈልጋል፡፡ ወታደሮቹ ከፍ ያለ ክፍያ ለማግኘት ብሎም ለጭካኔያቸውና ብልግናቸው መሰረት ለማግኘት ነገስታቱ መጥፎ ባህሪያት እንዲላበሱ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ የተነሳ እነዛ ተፈጥሯዊ የአመራር ብቃት ወይም ወታደሩንና ህዝቡን ማስታረቅ የሚችል ጠንካራ አቋም የሌላቸው ነገስታት በጾና ይቸገራሉ፡፡

ብዙዎቹ፣ በተለይም ለስልጣን አዲስ የሆኑቱ የሁለቱን ሀይላት ተቃራኒ ፍላጎት ማሟላት በእጅጉ አዳጋች እንደሆነ ሲገባቸው ወታደራቸውን በማስደሰት ለህዝባቸው ጉዳት ደንታ ቢስ ይሆናሉ፡፡ በርግጥ ይህ አካሄድ አስፈላጊና ሊወገድ የማይችል ነው፡፡ ምክንያቱም ነገስታቱ በተወሰነ ወገን የሚከሰቱ ጥላቻዎችን የመግታት አቅም አይኖራቸውም፡፡ መጀመሪያ ላይ

በሁሉም ሰው ላለመጠላትና በማንኛውም መደብ ገሸሽ ላለመደረግ ይታገላሉ፡፡ ይህ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ግን ከሁሉ በላይ ሀያል የሆነውን መደብ ጥላቻ ለማምለጥ መትጋት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ብዙዎች ከህዝቡ ይልቅ ዕጣ ፈንታቸውን ከወታደሩ ጋር ያስተሳስራሉ፡፡ ይህም ሆኖ ግን የዚህ አካሄድ ጠቀሜታ ገዢዎች ወታደሮቻቸውን የመቆጣጠር አቅም ላይ የሚወሰን ነው፡፡

ከላይ የተገለጸውን እውነታ ተመርኩዘን የጥንታዊዎቹን የሮማ ነገስታት ማርከስ፣ ፐርቲናክስና አሌክሳንደር ባህሪያት ስናጤን እነዚህ ነገስታት ጭካኔን የሚጠሉ፣ ፍትህ ወዳድ፣ ቸርና ትሁት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ሆኖም ከማርክስ በስተቀር የሁሉም አጨራረስ አሳዛኝ ነበር፡፡ ከነዚህ ነገስታት ውስጥ ማርክስ ብቻ ነበር በህይወትም ሆነ በኋላ ክብሩን ማስጠበቅ የቻለው፡፡ ማርከስ በዘመኑ ሀይሉን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ስልጣኑን ለወራሾቹ ማስተላለፍም የቻለ ነበር፡፡ ሆኖም ላበረከተው አስተዋፅዖ ወታደሩንም ሆነ ህዝቡን እጅ መንሳት አልተጠበቀበትም፡፡ ታላቅ ከበሬታ የሚገባው ጠንካራ አቋም የነበረው በመሆኑ ማርከስ የህዝቡንም ሆነ የሰራዊቱን ስርአት አልበኝነት ያለምንም ጥላቻና ንቀት መቆጣጠር ችሎ ነበር፡፡ ፐርቲናክስ ግን ገና በማለዳው ነበር ከአስተዳዳሪነት ክብሩ የተወገደው፡፡ ቀድሞውኑ ፐርቲናክስ የነገሰው ከወታደሩ ፍላጎት ውጪ ከመሆኑም ባሻገር በቀድሞው ገዢ ኮሞደስ ስር በልቅነት ይተዳደሩ ለነበሩት ስርአት አልበኛ ወታደሮች ፐርቲናክስ የሚጥልባቸውን አይነት ግብረገብነት መላበስ የማይቋቋሙት አይነት ነበር፡፡ በመሆኑም ንጉሱ የወታደሩን ጥላቻ ከማትረፍ ሊያመልጥ አልቻለም፡፡ ከዚህም

በከፋ በእድሜው አዛውንት በመሆኑም ሰራዊቱ ለንጉሱ ከፍተኛ ንቀት ነበረው፡፡

እዚህ ጋር ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ አንድ ሰው በክፋነቱ የሚጠላውን ያህል በጥሩነቱም ሊጠላ እንደሚችል ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ቀደም እንደገለጽኩት ስልጣኑን ለማስጠበቅ የሚፈልግ ልኡል ብዙውን ጊዜ ጥሩ ላለመሆን ይገደዳል፡፡ ምክንያቱም ስልጣንህን የምትጥልበት ማንኛውም መደብ (ህዝቡ፣ ሰራዊቱም ይሁን መሳፍንቱ) የተበላሸ ሆኖ ሲገኝ የመደቡን ፍላጎት በአግባቡ ለማስተናገድ ተመሳሳይ የሆነ አቋም ለመያዝ ትገደዳለህ፡፡

ወደ አሌክሳንደር ስንመጣ ደግሞ የንጉሱ መልካምነት ወደር የለሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አሌክሳንደር የሚወደስባቸው ሌሎች ጎኖች እንደተጠበቁ ሆነው በስልጣን በቆየባቸው አስራ አራት አመታት ያለፍርድ ሂደት በአንድም ሰው ላይ የሞት ብይን አለማስተላለፉ ይነገርለታል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ሴታሴት በመቆጠሩና በእናቱ መመራትን የፈቀደ ወንድ በመሆኑ በሰራዊቱ ይናቅ ነበር፡፡ ስለዚህ ጦሩ በአሌክሳንደር ላይ አሴረበትና ገደለው፡፡

ከነዚህ ነገስታት በተቃራኒ የኮሞደስ፣ ሴቨሩስ፣ የአንቶንዮስ ካራካላንና ማክሲሙንስን ባህሪያት ስንመለከት ደግሞ ሁሉም አረመኔና በዝባዥ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ የሰራዊቱን ፍላጎት ለማሟላት በህዝቡ ላይ የማይጥሉት ስቃይና ሰቆቃ አልነበረም፡፡ ከነዚህ ነገስታት ውስጥ ከሴቨሩስ በቀር የሁሉም መጨረሻ የማያምር ነበር፡፡ ሴቨሩስ ወደር የለሽ ጀግና ስለነበር ህዝቡን ቢጨቁንም የሰራዊቱን ወዳጅነት አስጠብቆ እስከመጨረሻው

መንገስ ችሏል፡፡ ጀግንነቱ ህዝቡንም ሆነ ወታደሩን የሚያስደምም ስለነበር ህዝቡ በአድናቆት ወታደሩ በታላቅ አክብሮት ይገዛው ነበር፡፡

የሴቭሩስ አስተዋጽኦ ለአንድ ንጉስ ትምህርት የሚሰጥ ተጠቃሽ ብቃት በመሆኑ ከዚህ ቀደም የገለጽኳቸውን የቀበሮና አንበሳነት ተፈጥሮን እንዴት በአግባቡ መላበስ እንደቻለ በአጭሩ ለማሳየት እወዳለሁ፡፡

የንጉስ ጁሊየስን ዳተኝነት የሚያውቀው ሴቭሩስ በፕሪቶሪያ ዘቦች የተገደለውን ንጉስ ፐርቲናክስ ግድያ ለመበቀል በሚል ሰበብ ስሎቬንያ የሚገኘው ሰራዊቱን አሳምኖ ወደ ሮም ዘመተ፡፡ በዚህ ሰበብ ተነሳስቶ ምንም ፍንጭ ሳይሰጥ ጦሩን ወደ ሮም አንቀሳቅሶ፣ መነሳቱ እንኳ ሳይታወቅ ጣሊያን ግዛት ደረሰ፡፡ ሮም በደረሰ ጊዜ ካቢኔው በፍርሀት ተቀፍድዶ ሴቭሩስን የግዛቲቱ ንጉስ አድርጎ በጁሊያን ላይ የሞት ፍርድ በየነ፡፡ ከዚህ ጅማሮ በኋላ ሴቭሩስን የአካባቢው ልእለ ሀያል ከመሆን የሚያግዱት መሰናክሎች ሁለት ነበሩ፡፡ አንደኛው በኤዥያ የሚገኘው እራሱን ንጉሰ ነገስት አድርጎ የሾመው የጠቅላይ ጦሩ አዛዥ ፔሴኒዮስ ኒገር ሲሆን ሌላኛው በምእራብ በኩል ለንጉሰ ነገስትነት ያቆበቆበው አልቢኒዮስ ነበር፡፡ ለሁለቱም ተቀናቃኞቹ በአንድ ጊዜ ባላንጣነቱን ማሳየት አደገኛ እንደሆነ የተገነዘበው ሴቭሩስ ኒገርን ለማጥቃትና አልቢኒዮስን ለማሞኘት አቀደ፡፡ ከዚህ በመነሳት ለአልቢኒዮስ ደብዳቤ ጽፎ በሴኔቱ ንጉሰ ነገስት ተደርጎ መሾሙንና ግርማዊነቱን ከሱ ጋር የመካፈል ፍላጎት እንዳለው ገለጸለት፡፡ ከዚያም የቄሳርነት ማእረግንና በካቢኔው አርቃቂነት ተባባሪ ንጉሰ ነገስት የሚል ሹመት አጽድቆ ላከለት፡፡ አልቢኒዮስ

ይህንን ሹመትና ሽልማት ያለምንም ጥርጥር እንዳመጣጡ ተቀበለ፡፡ ሆኖም ሴቨሩስ ኒገርን ድል ነስቶ ከገደለ በኋላ ወደ ሮም ተመልሶ ለካቢኔው አልቢኒዮስ ውለታውን ገሸሽ አድርጎ ሊገድለው እያሴረ መሆኑን ገለጸ፡፡ በዚህ የተነሳ ወደ አልቢኒዮስ ሄዶ ለምስጋና ቢስነቱ ተገቢውን ቅጣት መስጠት እንዳለበት ካቢኔውን አሳመነ፡፡ እናም ወደ ፈረንሳይ አቅንቶ የአልቢኒዮስን ግዛትና ህይወት ነጥቆ ተመለሰ፡፡

የሴቨሩስን አካሄድ ጠለቅ ብሎ የመረመረ ማንኛውም ሰው ሰውዬው የአንበሳን አይነት አውሬነትና የቀበሮን ብልጠት እንደተጎናጸፈ መረዳት ይችላል፡፡ በመሆኑም ሴቨሩስ በሁሉም ሰው ዘንድ ይከበርና ይፈራ ነበር፡፡ ከዚህ አንጻር የሴቨሩስ ሀያልነት እንደ ተአምር የሚቆጠር አይሆንም፡፡ የተጎናጸፈው ገደብ አልባ ከበሬታ የሰራዊቱ ቀማኛነት በህዝቡ ላይ ሊያሰርጽ ከሚችለው ጥላቻ ይታደገዋል፡፡

ወደ ሴቨሩስ ልጅ፣ አንቶኒዮስ ካራካላ ስንሸጋገር ደግሞ፣ ይህ ሰው ልክ እንደ አባቱ ህዝቡን የሚያነሆልል፣ በሰራዊቱ ዘንድ የሚያስከብር ጥንካሬ የተላበሰ ነበር፡፡ ማንኛውንም አይነት ተጽእኖ የማሳደር ብቃት ያለው ጦረኛ ስለነበር በጠረጴዛ ዙሪያም ሆነ በማንኛውም ቦታ የሚስተዋል ልልነትን አይወድም፡፡ ይህ ባህሪው የወታደሩን መሰጠት አትርፎለታል፡፡ ነገር ግን አውሬነቱና ጭካኔው ገደብ የለሽና የማይቋቋሙት አይነት በመሆኑ (እልፍ አእላፍ ንጹሀንን ፈጅቷል፣ በሮምና በአሌክሳንድሪያ የበርካቶችን ነፍስ ቀጥፏል) አለም አቀፋዊ ጥላቻን አትርፏል፡፡ በቅርብ ያሉ ወዳጆቹ እንኳን ሳይቀሩ

ሰውዬውን መስጋት ስለጀመሩ የሆነ ቀን በወታደሮቹ ተከቦ በተቀመጠበት በገዛ የጦር አዛዡ ተገደለ፡፡

እዚህ ጋር መታወስ ያለበት ሀቅ አንድ ልኡል ከሆነ ጽንፈኛ የመግደል ሴራ ከደባበት ከሞት ሊያመልጥ እንደማይችል ነው፡፡ ምክንያቱም ለመሞት የቆረጠ ማንኛውም ሰው መግደል ይችላል፡፡ በርግጥ እንዲህ አይነቱ የነፍስ ግድያ ከስንት ጊዜ አንዴ የሚከሰት በመሆኑ ብዙ መስጋት አያስፈልግም፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ልኡል በግዛት ማስተዳደሩ ሂደት ውስጥ ተካፋይ በሆኑ የቅርብ ሰዎቹ ላይ የከፋ ጉዳት ከማድረስ መቆጠብ አለበት፡፡ አንቶኒዮስ የተሳሳተው እዚህ ጋር ነበር፡፡ የዛን የጦር አዛዡን ወንድም አሳፋሪ በሆነ መንገድ በሞት ቀጥቶት ነበር፡፡ የጦር አዛዡን በየእለቱ ያስቃየው ነበር - ምንም እንኳ ከጠባቂዎቹ አንዱ ቢሆንም፡፡

የሌላኛውን የሮማ ንጉስ ኮሞደስን ታሪክ ስንመለከት ደግሞ ንጉሱ የማርከስ ልጅ እንደመሆኑና ንግስናውን በውርስ ያገኘው በመሆኑ ግዛቱን ማስተዳደር ቀላል ሀላፊነት ነበር፡፡ አባቱ የጣለለትን አሻራ በመከተል ብቻ የወታደሩንም ሆነ የህዝቡን ፍላጎት ማሟላት ይችል ነበር፡፡ ሆኖም ኮሞደስ ጨካኝና የአውሬነት ባህሪ የተላበሰ በመሆኑ ወታደራዊው መደብ የሱን በዝባዥነት ያለከልካይ ይፈጽም ዘንድ መረን ለቀቀ፡፡ ከዚህም በከፋ ክብሩንና ማእረጉን ረስቶ ከግላዲያተሮች ጋር በመፋለም ደረጃውን ያወርድ ነበር፡፡ ከዚህም ተጨማሪ የዙፋኑን ግርማዊነት የሚያጎድፉ በርካታ ክብረ ነክ ነገሮችን ያደርግ ነበር፡፡ በመሆኑም በወታደሮቹ ዘንድ ተናቀ፡፡ በአንድ ጎን በመጠላቱ በሌላ ጎን

ደግሞ በመናቁ የሎሌዎቹ ሴራ ሰለባ ሆኖ ህይወቱን ለማጣት ተዳረገ፡፡

ሌላኛው የሮም ንጉስ ማክሲሙንስ ደግሞ በጦረኝነቱ የታወቀ ንጉስ ነበር፡፡ በአሌክሳንደር ሴታ ሴትነት የተሰላቹት የሮም ወታደሮች ከአሌክሳንደር ህልፈት በኋላ ማክሲሙንስን ንጉሳቸው አድርገው መረጡት፡፡ ይሁን እንጂ ንጉስ ነገስትነቱን ለረዥም ጊዜ ማስጠበቅ አልቻለም፡፡ ምክንያቱም በብዙሀኑ ዘንድ እንዲጠላና እንዲናቅ ያደረጉት ሁለት ምክንያቶች ነበሩ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የንጉሱ ስረ መሰረት ከተናቀ መደብ ነበር፡፡ በልጅነቱ በትሬስ ውስጥ እረኛ ነበር (ይህ ሀቅ በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ በመሆኑ የህዝቡ አመለካከት የወረደ ነበር) በሁለተኛ ደረጃ ዙፋኑን ሲረከብ በደንቡ መሰረት ወደ ሮም ሄዶ ንጉስ ነገስትነቱን በአደባባይ አልተቀባም፡፡ ከዚህም በከፋ ማክሲሙንስ በሮምና በሌሎች ግዛቶች ላይ በሾማቸው ሀገረ-ገዥዎች በሚያደርሳቸው ግፍና ጭቆና ህዝቡን ያስበረግግ ነበር፡፡ በአስተዳደጉና ስረ መሰረቱ ላይ የተመረኮዘ ንቀትና በአረመኔነቱ ባተረፈው ጥላቻ የተነሳ በመላው ግዛቱ ውስጥ አመፅና ተቃውሞ ተንሰራፋ፡፡ መጀመሪያ አፍሪካ አመጸ፤ ከዚያም ካቢኔው በመላው የሮም ህዝብ ድጋፍ ታግዞ በማክሲሙንስ ላይ ተነሳ፡፡ በስተመጨረሻ መላዋ ጣሊያን በንጉሱ ላይ አሴረች፡፡ ወታደሮቹም የሴራው ተካፋይ ሆኑ፡፡ የአኩሊያንን ግዛት ከበው በማጥቃት ላይ ሳሉ ከተማውን መያዝ ሲሳናቸው በማክሲሙንስ መሪር ጭካኔ የተሰላቹት፣ በእልፍ አእላፍ ጠላት መከበቡን የተመለከቱት ወታደሮች ፍራቻቸው ተቀዛቀዘ፡፡ እናም ንጉስ ማክሲሙንስን ገደሉት፡፡

የተቀሩትን የሮማን ነገስታት ሄሊዮጋባላስ፣ ማክሪናስም ሆነ ጁሊያን በእጅጉ የተናቁ በመሆናቸው የስልጣን ጉዟቸው በአጭሩ የተቀጨ ነበር፡፡ በመሆኑም የነዚህን ነገስታት ታሪክ በስፋት ማውሳት አልፈልግም፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የዚህ ዘመን ልኡላን የወታደሩን መረን የለቀቀ ፍላጎት የማሟላት ተጨማሪ ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡ የተወሰነ ትኩረት መስጠት ብቻ በቂ ነው፡፡ ምክንያቱም የዚህ ዘመን ገዢዎች የሮማውያንን አይነት መጠነ ሰፊ ሰራዊት የላቸውም፡፡ በሮማውያን ዘመን ከህዝቡ ፍላጎት ይልቅ የወታደሩን መጠበቅ አስፈላጊ ነበር፡፡ ለምን ቢባል ወታደሩ ከህዝቡ የላቀ ሀይል ነበረውና፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ግን ከቱርክና ከሱልጣኑ በቀር ሁሉም ገዢዎች ከወታደራቸው ይልቅ ህዝባቸውን ማስቀደም ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ባለንበት ዘመን ከወታደሩ ይልቅ የህዝቡ ሀይል ያጋድላል፡፡ የቱርክና የሱልጣኑ ግን ከሌሎቹ ይለያል፡፡ የቱርክ ገዢ 12000 እግረኛና 15000 ፈረሰኛ የያዘ በመሆኑ ሰራዊቱ ለግዛቱ ጥንካሬና ደህንነት ወሳኝ ሀይል ነው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ እርምጃ የሰራዊቱን ታማኝነት የሚደግፍ መሆኑ ሊጤን ይገባል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የሱልጣኑም መንበር በሰራዊቱ መዳፍ ውስጥ በመሆኑ የህዝቡ ሁናቴ ምንም ይሁን ምን የሰራዊቱን አጋርነት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የሱልጣኑ አስተዳደራዊ ስርአት ከሌሎቹ ፍጹም የተለየ ነው፡፡ ከጳጳሳዊ ግዛት ጋር የሚመሳሰል እንደመሆኑ በውርስ የሚተላለፍ ወይም አዲስ የተመሰረተ ሊባል አይችልም፡፡ በሱልጣኑ ግዛት ውስጥ የቀዳሚው ገዢ ልጅ ሳይሆን ስልጣን የሚወርሰው የመሾምና የመሻር ስልጣኑ ባላቸው አካላት

የተሾመው ነው፡፡ በዚህ ስርአት ውስጥ አዲስ የተሾመውን ልኡል የሚገዳደሩ ተግዳሮቶች አይኖሩም፡፡ ምክንያቱም ልኡሉ አዲስ ቢሆን እንኳ የሹም ሽር ተቋማቱ እድሜ ጠገብ ናቸው፡፡

ወደ ርእሰ ጉዳዩ ስንመለስ፣ የአካሄዴን አመክንዮ ተከትሎ የተመለከተ ማንኛውም ሰው ከላይ ለዘረዘርኳቸው ነገስታት መውደቅ መንስኤው ጥላቻ ወይም ንቀት መሆኑን መረዳት ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተወሰኑት በአንድ መንገድ አንዳንዶቹ በተለየ መንገድ ተጉዘው በሁለቱም መንገድ አንዱ ፍጻሜው ሲያምር ሌላኛው በአሳዛኝ ሁኔታ እንደሚቀጭ መረዳት ይችላል፡፡ ፐርቲናክስና አሌክሳንደር አዳዲስ ነገስታት እንደመሆናቸው በትረ ስልጣኑን ከልጅ ልጅ እስከማውረስ ደረጃ የደረሰውን ማርከስ ኤውሬልዮስን ለመምሰል መሞከር ረብ አልባ ብሎም ጎጂ ይሆን ነበር፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ካራካላ፣ ኮሞደስና ማክሲሙንስ ሴቨሩስን ለመምሰል ቢሞክሩ የሱን አሻራ ለመከተል የሚበቃ ጀግንነት ስላልነበራቸው ለከባድ ስህተት ይዳረጉ ነበር፡፡ ስለዚህ አንድ አዲስ ልኡል ማርከስን መስሎ መታየት ወይም የሴቨሩስን ፈለግ መከተል አይጠበቅበትም፡፡ ትክክለኛው መንገድ ከሴቨሩስ ጥንካሬ ግዛቱን ለማዋቀር የሚረዳውን ትምህርት መቅሰም፣ ከማርከስ ደግሞ ግዛቱን ከመሰረተ በኋላ ግዛቱንና የግዛቱን ታላቅነት ጠብቆ የሚያቆይበትን ባህሪ መቅሰም ነው፡፡

# 19. የተለያዩ የአገዛዝ ስልቶች

ግዛታቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቆጣጠር አንዳንድ ልኡላን ሎሌዎቻቸውን ትጥቅ ያስፈታሉ። አንዳንዶች የከፋፍለህ ግዛን ፖሊሲ ይጠቀማሉ፤ አንዳንዶች ሆን ብለው በራሳቸው ላይ ተግዳሮት ይፈጥራሉ፤ አንዳንዶች የሚጠራጠሯቸውን ሀይሎች ለማውደም ይጥራሉ፤ አንዳንዶች ምሽግ ይገነባሉ፤ ሌሎች ደግሞ የተገነቡትን ያወድማሉ።

በርግጥ የግዛቶቹን ሁናቴ ሳናጤን የነዚህንና መሰል ፖሊሲዎችን አግባብነት መመዘን ባይቻልም ጠቅለል ባለ መልኩ የፖሊሲዎቹን ተጽእኖ ለመቃኘት እሞክራለሁ።

የመጀመሪያውን ፖሊሲ ስንመለከት አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ብዙዎቹ መሪዎች ዜጎቻቸውን ትጥቅ ሲያስፈቱ አይስተዋሉም። በተቃራኒው ያልታጠቁትን ሲያስታጥቁ ይታያል። ምክንያቱም ዜጎችን ማስታጠቅ እራስን ከማስታጠቅ ተናንሶ የሚታይ አይደለም። ትጥቅ በማስታጠቅ ሂደት ውስጥ ተጠርጣሪ የሆኑት ሀይላት ተአማኒ ይሆናሉ። ታማኝ የነበሩትም ከታማኝነት ባሻገር እራሳቸውን አሳልፈው የሚሰጡ አጋሮች ይሆናሉ።

ይሁን እንጂ ሁሉንም ወገን ማስታጠቅ የማይቻል በመሆኑ ለአንዱ ይህን እድል ስትሰጥ ሌላውን መንፈግ ይኖርብሀል። ይህም ሆኖ፣ ይህ አይነቱ መድልዎ በሁሉም ወገን ከግንዛቤ ሲገባ አንዱን ይበልጥ ባለእዳህ ሲያደርገው ሌላኛው ወገን በበኩሉ ይበልጥ በአደጋ የተከበቡትና የላቀ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው

አካላት ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ በመረዳት ውሳኔህን በጸጋ ይቀበላል፡፡

ነገር ግን በተቃራኒው ዜጎችህን ትጥቅ ማስፈታት ስትጀምር ቅያሜ ታተርፋለህ፡፡ የትጥቅ ማስፈታት እርምጃህን አንድም የፍርሀት አሊያም የተጠራጣሪነት ምልክት አድርገው ይወስዱታል፡፡ በሁለቱም መንገድ ግን የዜጎችህን ጥላቻ ታተርፋለህ፡፡ ከዚህም ባለፈ ያለ ትጥቅ መቆየት ስለማይቻል ዜጎችህን ትጥቅ ካስፈታህ ቅጥረኛ ወታደሮችን ለመመልመል ትገደዳለህ፡፡ ከዚህ ቀደም የቅጥረኛ ወታደሮችን ባህሪ በስፋት እንደዳሰስኩት ቅጥረኞችህ አስተማማኝ ሊሆኑ ቢችሉ እንኳ ከብርቱ ጠላቶችም ሆነ ከማታምናቸው ሎሌዎችህ ሊታደጉህ አይችሉም፡፡ በመሆኑም አዲስ ግዛትን የሚመራ አዲስ ልኡል ዜጎቹን ትጥቅ ማስፈታት ሳይሆን በተቃራኒው የተቻለውን ያህል ለማስታጠቅ መሞከር አለበት፡፡ ታሪክም የሚያመላክተው ይህንኑ ነው፡፡

ሆኖም አንድ ልኡል ቀድሞ ከነበረው ግዛት ጋር የሚዋሀድ አዲስ ግዛት ወይም ክንፍ ሲመሰርት ከታማኝ አጋሮቹ በቀር በአዲሱ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ሀይሎችን በሙሉ ትጥቅ ማስፈታት አለበት፡፡ የታመኑትም መደቦች ቢሆኑ እንደየሁኔታው መዳከምና መሳሳት ይኖርባቸዋል፡፡

ወደ ሌላው ፖሊሲ ስንሸጋገር በጣሊያን የነበሩ አስተዋይ የሚባሉ ቀደምት አያቶቻችን እንደሚሉት እንደ ፒስቶያ ያሉትን ግዛቶች በአንጃዎች በመከፋፈል በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ መመራት ሲኖርባቸው እንደ ፒሳ ያሉት ምሽግ ያስፈልጋቸዋል ብለው

ያምኑ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳት በርካቶች በግዛቶቻቸው የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ሁከት በመቀስቀስ ግዛቶቻቸውን በቀላሉ ለመቆጣጠር ይሞክሩ ነበር፡፡ በርግጥ በወቅቱ ጣሊያን በአንጻራዊ መረጋጋት ውስጥ ትገኝ ስለነበር ይህን ፖሊሲ መከተል አመቺ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ ሆኖም አሁን ባለንበት ሁኔታ ይህ ፖሊሲ አግባብነት ይኖረዋል ብዬ አላምንም፡፡ በተቃራኒው ጠላታቸውን በተመለከተ የተከፋፈሉት ግዛቶች በአንድ ላይ ሊነሱ ይችላሉ፡፡ የደከመው ሀይል በወራሪ ላይ ነፍጥ ካነሳ ሌሎች ላያብሩ አይችሉም፡፡

ቬኒሻውያን በዚህ እሳቤ ተነሳስተው በግዛታቸው የሚገኙ የገልፍና የጊበሊን አንጃዎችን ያምሱ ነበር፡፡ የጎላ ደም መፋሰስ እንዲከሰት ባይፈቅዱም በመካከላቸው ሁከት በመቆስቆስ ዜጎች በራሳቸው አለመግባባት ተጠምደው በአገዛዙ ላይ ማበር እንዳይችሉ አድርገው ለማዳከም ይሞክሩ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ ፖሊሲ ባቀዱት መስመር ሊጓዝ አልቻለም፡፡ ቫይላ ላይ በጦር ሲጠመዱ አንዱ አንጃ ወኔውን አሰባስቦ መላውን ይዞታቸውን ነጠቃቸው፡፡ ስለዚህ እንደዚህ አይነቱን ፖሊሲ መከተል የመሪዎች ደካማ ጎን ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ ጠንካራ በሆኑ ግዛቶች ውስጥ በተለይ እንዲህ ያለው በአንጃ ከፋፍሎ የማመስ ስልት ሊተገበር አይገባም፡፡ ይህ መንገድ ጠቀሜታ ሊኖረው የሚችለው በሰላሙ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ጦርነት ሲነሳ ግን የዚህ ፖሊሲ ድክመት ይፋ ይወጣል፡፡

የአንድ ልኡል ታላቅነት መሰናክሎችን ተጋፍጦ ተቃዋሚዎቹን ድል የመንሳት ብቃት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ እድል የአንድን ልኡል ታላቅነት ለመገንባት

ስትፈልግ ጠላቶቹን ታበዛለች፡፡ የክብር ግዛቱን ይቀናቀኑ ዘንድ ትደግፋለች፡፡ ልኡሉም ወደር የለሽ ድልን ተቀዳጅቶ ጠላቶቹ ባቀረቡለት የስልጣን መሰላል ተረማምዶ ሀይልንና ታላቅነትን ይቀናጃል፡፡ በዚህ የተንሳ በርካቶች አንድ ልኡል እድሉን ካገኘ የሆነ አመጽ በማነሳሳትና አመጹን በመደምሰስ ክብሩን ማደስ ይችላል ብለው ያምናሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ መሪዎች በተለይም አዳዲስ ገዢዎች በአገዛዛቸው ጅማሬ ላይ የሚጠረጠሩ ዜጎቻቸው መጀመሪያ ላይ አጋርና ደጋፊ ከነበሩት በላቀ ታማኝና ጠቃሚ ሆነው ያገኟቸዋል፡፡ የሲዬናው ሀገረ-ገዢ ፖንዶልፎ ፔትሩቺ ግዛቱን ያስተዳድር የነበረው መጀመሪያ ላይ ከሌሎች በተለየ ጥርስ ውስጥ በገቡ ተከታዮች ድጋፍ ነበር፡፡ ሆኖም ነገሮች እንደ የሁኔታው ስለሚለዋወጡ ካጠቃላይ ድምዳሜ መድረስ አይቻልም፡፡ ነገር ግን መጀመሪያ ላይ ጠላት ሆነው የቀረቡት ወገኖች የሚረዳቸው አካል የሚያስፈልጋቸው አይነት ከሆኑ ልኡሉ ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ አይቸገርም ለማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ አካላት መጀመሪያ ላይ ያሰረጹትን የጠላትነት ምስል በድርጊታቸው መፋቅ እንዳለባቸው ስለሚያውቁ በታማኝነትና በትጋት ለማገልገል ይገደዳሉ፡፡ በመሆኑም የልኡሉ ወዳጆች እንደሆኑ በማሰብ ከሚዘናጉት በላቀ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል፡፡

ውስጣዊ ንቅናቄን በመፍጠር ግዛትን የሚይዙ ገዢዎች የደጋፊዎቻቸውን የእርዳታ ምክንያት በጥንቃቄ ማጤን ይኖርባቸዋል፡፡ ወዳጅነታቸው አዲስ አገዛዝ ከመሻት በመነጨ ሳይሆን በነባሩ አመራር ካለመርካት የመነጨ ከሆነ ልኡሉ

ወዳጅነቱን ጠብቆ ለማቆየት የሚችለው ቀላል የማይባሉ እንቅፋቶችንና ጫናዎችን ተቋቁሞ ነው፡፡ ምክንያቱም እሱም በተራው ፍላጎታቸውን ማሟላት ይሳነዋል፡፡ ከጥንታዊዎቹም ሆነ ከዘመናችን ታሪክ ምሳሌዎች ወስደን ካየን አንድ አዲስ ልኡል በነባሩ አገዛዝ ባለመርካታቸው ከደገፉት ወዳጆች ይልቅ በነባሩ አገዛዝ ረክተው የአዲሱ ተቃዋሚ የነበሩ ዜጎችን ወዳጅነት ማግኘትና ወዳጅነታቸውን ጠብቆ ማቆየት ይቀለዋል፡፡

አንዳንድ ሀገረ ገዢዎች ደግሞ ስልጣናቸውን በአግባቡ ለመጠበቅ በዙሪያቸው ግምብ አጥረው ምሽግ በመገንባት አድማ የሚያሴሩባቸውን ለመግታትና ከድንገተኛ ጥቃት ለመሸሸግ ይሞክራሉ፡፡ በርግጥ ይህ ዘዴ ከጥንት ጀምሮ የነበረ በመሆኑ አልቃወመውም፡፡ ይሁን እንጂ ባለንበት ዘመን ኒኮሎ ቪቴሊ ሲታዲ ካስቴሎ ውስጥ የነበሩትን ሁለት ምሽጎች አፍርሷል፡፡ የአርቢኖው ልኡል ጋይዶባልዶ፣ ቄሳር ቦርጂያ ካሰናበተው ግዛቱ ሲመለስ ምሽጎቹን ሁሉ ለአገዛዝ ምቹነት ሲል አፈራርሷቸዋል፡፡ ቦንቲቮግሊም ቦሎኛ ሲገቡ ተመሳሳይ እርምጃ ወስደዋል፡፡

ስለዚህ የምሽጎች አስፈላጊነት እንደየሁኔታው ይለያያል፡፡ በአንድ ጎን ጥቅም ሲኖራቸው በሌላ ጎን ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ጠቅለል ባለ መልኩ ሲቀመጥ ከውጪ ሀይሎች ጣልቃ ገብነት ይልቅ የራሱን ዜጎች ለሚፈራ ልኡል ምሽጎች አስፈላጊ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ከህዝቡ ይልቅ የውጪ ሀይሎችን የሚሰጋ ገዢ ምሽግ የመገንባቱን ፖሊሲ ከነአካቴው መርሳት አለበት፡፡

በመሆኑም ከሁሉ የላቀው መሸሸጊያ ምሽግ የህዝቡን ጥላቻ ማስወገድ ነው፡፡ ህዝቡ ከጠላህ ምሽግ ብትገነባም አይታደግህም፡፡

አንድ ጊዜ ህዝብ ነፍጥ ካነገበ የውጭ ሀይሎችን እርዳታ አያጣም፡፡

አሁን ባለንበት ጊዜ ጠቃሚነቱን ያስመሰከረ ምሽግ አለ ለማለት አይቻልም - የፎርሪሊንዋ ገገር ከገነባችው በቀር፡፡ አጋሯ ካውንት ጂሮላሞ ከተገደለ በኋላ ምሽግዋ የሚላንን እርዳታ አግኝታ እስክታገግም ድረስ ከህዝቡ ጥቃት ታድጓታል፡፡ በወቅቱ ህዝቡ የውጭ ድጋፍ ማግኘት የሚችልበት እድል አልነበረውም፡፡ ሆኖም ምሽጓ ለጊዜው እንጂ ለዘለቄታው ሊታደጋት አልቻለም፡፡ ቄሳር ቦርጂያ ከተማዋን ከቦ ሲያጠቃ የጠሏት ወገኖች ከወራሪው ጋር አበሩባት፡፡ እራሷን በግምብ ከልላ ከመመሸግ መጀመሪያውኑ የህዝቡን ጥላቻ ለማስወገድ መሞከሩ የተሻለ ነበር፡፡

ሁሉንም ነገር ከግንዛቤ ከተን ስንመለከት፣ በበኩሌ ምሽግ የሚገነቡትንም ሆነ የማንዱትን በተመለከተ የህዝቡን ጥላቻ ንቆ በምሽጎች የሚመካ ለውድቀት ይዳረጋል እላለሁ፡፡

## 20. አንድ ልኡል ከበሬታን መጎናጸፍ የሚችለው እንዴት ነው?

አንድን ልኡል ከፍተኛ ከበሬታ ለማጎናጸፍ ከታላላቅ የጦርነት ዘመቻዎችና ደማቅ ሰላማዊ ሰልፎች የላቀ ዋጋ ያለው ነገር የለም፡፡ ባለንበት ዘመን ታላላቅ ወታደራዊ ዘመቻዎች የሚያስገኙትን ከበሬታ ለማመላከት የስፔይኑ ንጉስ ፈርዲናንድ አይነተኛ ማሳያ ነው፡፡ ፈርዲናንድ ከትንሽዬ ሀገረ ገዥነት ተነስቶ ከፍተኛ ዝናና ታላቅነትን ተቀናጅቶ የመላው

ክርስቲያናዊ ግዛት ንጉስ መሆን የቻለ ሰው ነበር፡፡ የፈርዲናንድን ጉዞ ጠለቅ ብለን ስናጤን እርምጃዎቹ ሁሉ አስገራሚ አንዳንዶቹም ከሰብአዊነት ወጣ ያሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በስርወ መንግስቱ መጀመሪያ ፈርዲናንድ ግሬናዳን አጠቃ፡፡ የግሬናዳው ዘመቻ የሀይሉ መሰረተ ድንጋይ ሆነ፡፡ መጀመሪያ ላይ ግዛቲቱን ሳያወድም ተቆጣጠረና ያለምንም ፍራቻ ተቀናቃኞቹ የነበሩትን የካስቲል ከበርቴዎችን በዘመቻው ላይ አሳተፋቸው፡፡ ከበርቴዎቹ ሙሉ ትኩረታቸው ጦርነቱ ላይ ስለነበር በቤት ውስጥ አመፅ ስለመቆስቆስ የሚያስቡበት አእምሮ አልነበራቸውም፡፡ በዚህ መልኩ ከበርቴዎቹ በሀገራቸው ውስጥ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ሳያውቁ ፈርዲናንድ ስልጣኑንና ሀይሉን አደረጀባቸው፡፡ ከቤተክርስቲያኑና ከህዝቡ የሚያገኘውን ገንዘብ ሰራዊቱን ለመገንባትና ለረዥሙ ዘመቻ ለማብቃት ያውለው ነበር፡፡ በርግጥ በዚህ መልኩ ያዳበረው ሰራዊት ከፍተኛ ዝናና ታላቅነትን አጎናጽፎታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሀይማኖትን ሽፋን በማድረግ መጠነ ሰፊ የግዛት ማስፋፋት ዘመቻዎችን ያካሂድ ነበር፡፡ የሀይማኖት ሽፋንን ምክንያት በማድረግ የሞሪስኮስን ግዛት በግፍ በማጨቅየት ግዛታቸውን ነጥቋቸዋል፡፡ ተመሳሳይ የሆነ ሀይማኖታዊ አጀንዳ በመጠቀም አፍሪካን ወሯል፤ ወደ ጣሊያን ዘምቷል፤ ፈረንሳይን አጥቅቷል፡፡

ንጉሱ ታላላቅ መርሀ ግብሮችን በመዘርጋት እቅዶቹን እውን ያደርግ ነበር፡፡ ይህም ተከታዮቹን ሁሌም በጉጉትና በአግራሞት እንዲዋልሉና በውጤቱ እንዲኮሩ ያደርጋቸው ነበር፡፡ የንጉሱ እንቅስቃሴ አንዱ በአንዱ ላይ የተደራረበ ስለነበር ሰዎች በእርጋታ ተቀምጠው የሚያሴሩበት ጊዜና አጋጣሚ የሚሰጥ አልነበረም፡፡

ከታላላቅ ወታደራዊ ዘመቻዎች ባሻገር በሀገር ውስጥ የአስተዳደሩን ጥንካሬ የሚያሳዩ ደማማቅ ሰላማዊ ሰልፎችን ማዘጋጀትም ከበሬታን ለማግኘት ጠቃሚ ነው፡፡ አንድ ሰው ልዩ የሆነ ውጤት ሲያስመዘግብ ጥሩም ይሁን መጥፎ ሁሉንም በሚጋብዝ መልኩ ለድርጊቱ ሽልማት ወይም ቅጣት ሊቸረው ይገባል፡፡ ከሁሉ በላይ አንድ ልኡል በማንኛውም መልኩ የታላቅነት ሰብእናን የሚያጎናጽፉ ባህሪዎችን ማንጸባረቅ አለበት፡፡

በሌላ በኩል አንድ ልኡል ያለምንም ገደብ አንዱን በመደገፍ ወይም በመጻረር እውነተኛ ወዳጅነቱን ወይም ጠላትነቱን በማንጸባረቅም ከበሬታን ማግኘት ይችላል፡፡ ይህ ፖሊሲ ሁሌም ከገለልተኝነት የተሻለ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ ከአጎራባች ያሉት ሀይሎች በሽኩቻ ሲናጡ አንድም ከመካከላቸው አንዱ አሸንፎ አደጋ ውስጥ ልትወድቅ ትችላለህ፤ አሊያም የበላይ የሚሆን ሀይል ሊጠፉ ይችላል፡፡ በሁለቱም መንገድ ግን ጠቃሚ ሆኖ የሚገኘው ክተት አስነግረህ ጦር ማወጅ ነው፡፡ በሽኩቻው ውስጥ የመጀመሪያው ሁናቴ ተከስቶ አንዱ የበላይ ሲሆን ጦር ሳታውጅ በገለልተኝነት ብትቀመጥ ለአሸናፊው ለመንበርከክ ትገደዳለህ፡፡ የተሸናፊውን ወዳጅነትም ማግኘት አትችልም፡፡ በመሆኑም ገለልተኛ በመሆንህ የተነሳ ከለላም ሆነ ጥገኝነት የምታገኝበት በቂ ምክንያት አይኖርህም፡፡ ምክንያቱም አሸናፊው በችጋር ውስጥ እያለ ያልረዳውን ወላዋይ ወዳጅ አይፈልግም፡፡ ተሸናፊውም ከእሱ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘህ የአቅምህን ለማበርከት ፈቃደኛ ስላልነበረክ ይከዳሀል፡፡

አንሲዮችስ ሮማውያንን ለማስወጣት ከኤቶሊያውያን በተደረገለት ጥሪ መሰረት ወደ ግሪክ አቀና፡፡ ከዛም የሮማውያን

ወዳጅ ለሆኑት አቺያውያን ከውጊያው ገለልተኛ ይሆኑ ዘንድ መልእክት ላከባቸው፡፡ ሮማውያን ደግሞ በበኩላቸው ከጎናቸው ተሰልፈው ይዋጉ ዘንድ ይገፋፉ ነበር፡፡ ጉዳዩ በአቺያውያን ካቢኔ ውስጥ የመከራከሪያ ጉዳይ ሆኖ ቀረበና የአንቲዮቸሶች ቆንስል ገለልተኛ ይሆኑ ዘንድ አጥብቆ ሲወተውት የሮማውያኑ ቆንስል ለአቺያውያኑ እንዲህ ሲል አስጠነቀቀ «ገለልተኛ ከመሆን የከፋ ጥቅማችሁን የሚጻረር አማራጭ የለም፡፡ የኋላ ኋላ ያለ ምንም ጥቅምና ክብር የአሸናፊው ሰለባ ሆናችሁ ትቀራላችሁ፡፡»

ሁሌም እንደሚከሰተው ወዳጅህ ያልሆነው ሀይል ገለልተኝነትህን ይጠይቃል፡፡ ወዳጅህ የሆነው ግን የጦርህን ድጋፍ ይጠይቃል፡፡ ወላዋይ የሆኑ ልኡላን ጊዜያዊ ጉዳቶችን ለማምለጥ ሲሉ ገለልተኛ ይሆናሉ፡፡ መጨረሻቸው ግን ውድቀት ይሆናል፡፡ ሆኖም ለአንዱ ወገን ያለህን ድጋፍ በድፍረት አውጀህ ከጎኑ ስትቆም የቆምክለት ሀይል ከረታ ምንም እንኳን እጣ ፈንታህ በአሸናፊው ችሮታ የተመሰረተ ቢሆንም ባለእዳህ ይሆናል፡፡ በወዳጅነት ለመተሳሰር ይነሳል፡፡ እንደዚህ አይነቱን ጉዳይ በተመለከተ ሰዎች ይህን ያህል ባለውለታቸውን በምስጋና ቢስነት የጭቆና ቀምበር የሚማግዱ ስርአት የለሾች አይደሉም፡፡ በሌላ በኩል አጋርህ ከተረታ መጠጊያ ይሆንሀል፡፡ አቅም ባለው ጊዜ ሊረዳህ ይሞክራል፡፡ በዚህም የጋራ እጣ ፈንታችሁን በተሻለ መልኩ የመወሰን እድል ያላችሁ ግብረ አበሮች ትሆናላችሁ፡፡

በሌላ በኩል ተዋጊዎቹ ደካማ በመሆናቸው ሽኩቻው በማንም የበላይነት የማይጠናቀቅ አይነት ከሆነ ደግሞ አሸናፊን የምትፈራበት ምክንያት አይኖርም፡፡ እንዳውም ከተዋጊዎቹ አንዱን ለመደገፍ ይበልጥ አሳማኝ ምክንያት ይኖርሀል፡፡ አንዱን

ወገን በመደገፍ ሌላውን ማጥፋት ይቻልሀል፡፡ አሸናፊ ከሆናችሁ ግብረ አበርህ በመዳፍህ ስር ይውላል፡፡ ምክንያቱም ባንተ እገዛ ሊረታ የሚችልበት አጋጣሚ የለም፡፡

ሆኖም ግድ ካልሆነ በቀር አንድ ልኡል ከራሱ በላይ ሀያል ከሆነ ወገን ጋር ማበር የለበትም፡፡ ምክንያቱም የምትደግፈው ወገን በእጅጉ ሀያል ከሆነ ሲያሸንፍ እስረኛው ለመሆን ትገደዳለህ፡፡ ልኡላን ከሁሉ በላይ የሀያላን እስረኛ ላለመሆን መታገል አለባቸው፡፡ ሆኖም ለአንዱ ወገን መቆም ግድ ከሆነ አስቀድሜ እንደገለጽኩት አንዱን ጎን ደግፎ ሌላውን ተጻርሮ ጦርነት ማወጅ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም ማንኛውም መንግስት ሁሌም አስተማማኝ የሆነውን መንገድ እከተላለሁ ብሎ ማሰብ የለበትም፡፡ በአንጻሩ እያንዳንዱ አማራጭ መንገድ የራሱ የሆነ አደጋ እንዳለው ሊያምን ይገባል፡፡ ነገሮች የሚከናወኑት በዚህ መንገድ ነው፡፡ ሰው አንዱን አደጋ ለማምለጥ ሲታገል በሌላኛው ላይ ይወድቃል፡፡ አስተዋይነት የአንድን አደጋ ውጤት ማመዛዘንና ትንሸዬ ጉዳት ያለውን መምረጥ ነው፡፡

ከዚህም ባለፈ አንድ ልኡል ብቃት ያላቸውን ሰዎች በማበረታታትና በተሰማሩበት መስክ ልቀው የሚገኙትን በመሸለም ለተሰጥኦ ያለውን አክብሮት ማሳየት አለበት፡፡ በንግድ፣ ግብርናም ሆነ በማንኛውም መስክ ላይ የተሰማሩ ዜጎቹ ስራቸውን በሰላም ያከናውኑ ዘንድ ማበረታታት አለበት፡፡ ማንኛውም ዜጋ ሀብቱን ለማስፋፋት ስጋት ሊያድርበት አይገባም፣ ይወሰድብኛልም ብሎ ማሰብ የለበትም፡፡ ንግድ የመጀመር ውጥን

ያለው ዜጋ ከባድ ግብር ይጣልብኛል በሚል ፍርሀት ከእቅዱ መገታት የለበትም፡፡ በእንጻሩ ልኡሉ እንደዚህ አይነት ሀሳብ ያላቸውን ዜጎችና በማንኛውም መልኩ ለግዛቲቱ ማደግና መበልጸግ አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱትን ለመሸለም ዝግጁ መሆን አለበት፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ በአመት ውስጥ ምቹ በሆኑ አጋጣሚዎች ልኡሉ ህዝቡን በትርኢትና በክብረ በአል ማዝናናትና ማስደሰትም ቢችል ይመከራል፡፡ እያንዳንዱ ከተማ በማህበራትና በተለያዩ ቡድኖች የተከፋፈለ በመሆኑ ለነዚህ ነገሮች ትኩረት ሰጥቶ በየጊዜው ሊያገኛቸው ይገባል፡፡ የተወሰነ የትህትናና የቸርነት ልዩ ምሳሌዎችን ቢያሳያቸው መልካም ነው፡፡ ሆኖም ሁሉም ነገር የዘውዱን ግርማዊነት በጠበቀ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ ምላሽ የሚጠብቅ መሆን የለበትም፡፡

## 21. የልኡሉ ባለስልጣናት

ለአንድ ልኡል ሁነኛ ሚኒስተሮችን መሾም ቀላል ሀላፊነት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሚኒስትሮቹ ሚና በልኡሉ የማመዛዘን አቅም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የአንድን ልኡል ብቃት ከሚያስመሰክሩ ነገሮች አንዱ በዙርያው የሚያስቀምጣቸው ሰዎች ጥራት ነው፡፡ በዙሪያው የሚገኙ ሰዎች ብቁና ታማኝ ሆነው ሲገኙ ልኡሉ እንደ ብልህ ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ብቃታቸውን ማወቅና ታማኝነታቸውን ማረጋገጥ ችሏል፡፡ በተቃራኒው ሆነው ሲገኙ ግን ልኡሉ ሁሌም ለሰሉ ትችቶች ይጋለጣል፡፡

ምክንያቱም የስህተቱ መጀመሪያ ሚኒስተሮችን አመራረጡ ላይ ነው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ብሩህ የሆነ የማመዛዘን ብቃት በሶስት መልኩ ይለካል፡- አንደኛው ነገራትን በራስ የመረዳት ብቃት ሲሆን ሊላኛው የሌሎችን የግንዛቤ ብቃት መመልከት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ነገራትን በራሱ የማይረዳ የሰዎችንም የግንዛቤ ብቃት የማይገነዘብ ነው፡፡ የመጀመሪያው አይነት ብቃት በጣም ጥሩ የሚባል ነው፡፡ ሁለተኛውም ጥሩ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ሶስተኛው ግን ረብ አልባ ነው፡፡

አንድ ልኡል የመጀመሪያው ብቃት ከሌለው ሁለተኛው ሊኖረው ይገባል፡፡ አንድ ልኡል ከሰዎች አነጋገርና ድርጊት ጥሩና መጥፎውን ነቅሶ የመረዳት ችሎታ ካለው ነገራትን በራሱ መረዳት ቢያዳግተው እንኳ የሚኒስተሮቹ አድራጎት በጎ ወይም መጥፎ ሲሆን ማወቅ ይችላል፡፡ በዚህም ድርጊታቸውን ማወደስና ስህተታቸውን ማረቅ ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ ሚኒስትሮቹ ልኡሉን የማታለል ቀቢጸ ተስፋ አያድርባቸውም፡፡ እንደውም ስህተት ላለመስራት አበክረው ይጠነቀቃሉ፡፡

አንድ ልኡል በምን መልኩ ሚኒስትሮቹን መገምገም ይችላል የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ሁሌም የሚሰራ እንከን የለሽ መንገድ አለ፡፡ አንድ ሚኒስትር ከልኡሉ ይልቅ ለራሱ የሚያስብ ከሆነ፣ በድርጊቱ ሁሉ የራሱን ጥቅም ለማስከበር የሚጣጣር ከሆነ እንዲህ አይነቱ ሚኒስትር ጥሩ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በምንም ሁኔታ እምነት ሊጣልበት አይችልም፡፡ ምክንያቱም በመንግስት ሀላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጠ ሰው

ለመሪው እንጂ ለራሱ ማሰብ የለበትም፡፡ ከልኡሉ ጉዳይ ውጪ በማንኛውም አይነት ጉዳይ መጠመድ የለበትም፡፡

ሚኒስትሮቹን በሚፈለገው መልኩ መያዝ የሚፈልግ ልኡልም በበኩሉ ሚኒስትሩን መንከባከብ፣ ክብር መስጠትና ማበልጸግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህም ባለፈ ክብሩንና ሀላፊነቱን ከሚኒስትሩ ጋር በመጋራት ባለእዳው ሊያደርገው ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ሚኒስትሩ ምን ያህል የልኡሉ ጥገኛ እንደሆነ ይረዳል፡፡ ከሚገባው በላይ ክብርና ብልጽግናን በማግኘቱም ከዚህ የዘለለ ፍላጎት አይኖረውም፡፡ በልኡላንና በሚኒስትሮቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት በዚህ አግባብ ሲሆን አንዳቸው በአንዳቸው ላይ የመተማመን መንፈስ ያድርባቸዋል፡፡ ሁኔታዎች የዚህ ተቃራኒ ሆነው ከተገኙ ግን ውጤቱ ለሁለቱም ጎጂ ይሆናል፡፡

## 22. ከከንቱ ውዳሴና አሉባልታ እራስን መከላከል

አንድ ሳልጠቅስ የማላልፈው ጠቃሚ ነገር አለ፡፡ ልኡላን ካቢኔዎቻቸውን በሚገባ እስካልመረጡና ተገቢውን ብልህነትና አስተውሎ እስካልተላበሱ ድረስ፣ ለማስወገድ ከሚያስቸግራቸው ከባድ ስህተት ላይ ለመውደቅ ይገደዳሉ፡፡ እዚህ ላይ የማወራው በልኡላን ቤተመንግስት ውስጥ ስለሚርመሰመሱ ሸንጋዮችና አሉባልተኞች ነው፡፡

ሰዎች በገዛ ራሳቸው ጉዳይ የተዋጡና እራስን በማታለል አባዜ የተተበተቡ በመሆናቸው፣ የዚህ በሽታ ሰለባ አለመሆን

በእጅጉ ያዳግታቸዋል፡፡ ችግራችንን እንቅረፍ ሲሉ ደግሞ የመናቅ አደጋ ያንገብገብባቸዋል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ከከንቱ ውዳሴዎች እራስህን መከላከል የምትችለው እውነትን ማድመጥ እንደማያስቆጣህ ሰዎች እንዲረዱ በማድረግ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ሁሉም ሰው እውነትን ሊነግርህ ከቻለ ደግሞ ክብርህን ታጣለህ፡፡

በመሆኑም ብልህ የሆነ መሪ አማካዩን ስፍራ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ለአስተዳደሩ አስተዋይ ሰዎችን በመምረጥ ለነርሱ ብቻ እውነትን የመናገር ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ እነርሱም እውነትን የመናገር ፈቃድ ሊሰጣቸው የሚገባው ሀሳባቸውን እንዲሰጡ በተጠየቁበትና በሚመለከታቸው ጉዳይ ላይ ብቻ ነው - ከተፈቀደላቸው ውጪ ሊናገሩ አይገባም፡፡

ሆኖም ልኡሉ ማወቅ ያለበትን ሁሉ መጠየቅና ምላሻቸውን በሚገባ ማድመጥ ይኖርበታል፡፡ ካደመጠም በኋላ የሰማውን አመዛዝኖ ውሳኔው መወሰን ያለበት በራሱ ነው፡፡ ለካቢኔውና ለአማካሪዎቹ ያለው አመለካከት ይበልጥ በነጻነት በተናገሩ ቁጥር ይበልጥ ተቀባይነት እንደሚያገኙ የሚያሳምን መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ባለፈ ልኡሉ ማንንም መስማት አይጠበቅበትም፡፡ ተማክሮ ከጨረሰ በኋላ ከስምምነት የተደረሰባቸውን ፖሊሲዎች በተግባር ይፈጸሙ ዘንድ በቀጥታ ማውረድ አለበት፡፡ ፖሊሲዎቹ ሳይዛነፉና ሳይለወጡ በጥብቅ መፈጸም አለባቸው፡፡ ይህን አካሄድ የማይከተል ማንኛውም መሪ በአሉባልታዎች ወይም እውነታነታቸው ባልተረጋገጡ ከንቱ ውዳሴዎች ይባክናል፡፡ ወይም እርስ በርሳቸው በሚጋጩ ተጻራሪ ምክሮች አማካኝነት

አእምሮውን በየጊዜው ለመቀያየር ይገደዳል፡፡ በዚህ የተነሳ ለራሱ የሚኖረው አመለካከት ይወርዳል፡፡

አመለካከቴን በምሳሌ ለማስደገፍ አንድ አስረጂ አቀርባለሁ፡፡ ሊቀ ጳጳስ ሉካ፣ ንጉሰ ነገስት ማክሲሚሊያንን በተመለከተ ‹ሰዎችን አማክሮ ስለማያውቅ ነገሮች በሚፈልገው መልኩ አድርጎ አያውቅም› ብለው ነበር፡፡ ይህ ሊከሰት የቻለው የንጉሱ አካሄድ ከላይ ከገለጽኩት በተቃራኒ ስለነበር ነው፡፡ ንጉሱ እጅግ ድብቅ ሰው ነበር፡፡ እቅዱን ለማንም አያጋራም፤ የሰዎችንም ምክር አይቀበልም፡፡ እቅዱን በተግባር ማዋል ሲጀምር ግን በዙሪያው ካሉ ሰዎች ሁሉ ተቃውሞ ይገጥመዋል፡፡ ይህን ጊዜ ንጉሱ ከመቅጽበት ያሰበውን ነገር ይተወዋል፡፡ በዚህ የተነሳ አንድ ቀን የጀመረውን ነገር በነጋታው ይተዋል፡፡

አንድ ልኡል ሁሌም ምክር ያስፈልገዋል፡፡ ሆኖም ይህ መሆን ያለበት እሱ ሲፈልግ እንጂ ሌሎች ሲፈልጉ አይደለም፡፡ ማንም ሰው ካልተጠየቀ በቀር በማንኛውም ጉዳይ ላይ ምክር ከመስጠት መቆጠብ አለበት፡፡ ልኡሉ ማወቅ የሚፈልገው ነገር ሲኖር ግን በማያቋርጥ መልኩ መጠየቅና እውነታውን በትግስትና እርጋታ ማድመጥ ይኖርበታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሰዎች በማንኛውም አይነት ምክንያት ተነሳስተው እውነታውን ሊደብቁት ሲሞክሩ ቁጣውን ማሳየት ይኖርበታል፡፡

በርካቶች፣ አንዳንድ መሪዎች ብልህ መስለው የሚታዩት በተፈጥሯቸው ብልህ ሆነው ሳይሆን ጠንካራ አማካሪዎችን ከጎናቸው አስቀምጠው እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ሆኖም እውነታው ይህ አይደለም፡፡ እዚህ ጋር አንድ የማይቀለበስ ህግ አለ፡፡ እራሱ

አስተዋይ ያልሆነ ልኡል በጥሩ ሁኔታ ሊመከር አይችልም - ሁሉንም ነገር በአንድ ብልህ አማካሪ ላይ ጥሎ እራሱን አሳልፎ ካልሰጠ በቀር፡፡ በዚህ መንገድ ጥሩ የምክር አገልግሎት ሊያገኝ ቢችል እንኳ አማካሪው ያለውን ነገር ሁሉ ስለሚነጥቀው ስልጣኑን ጠብቆ ማቆየት አይቻለውም፡፡

የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን ምክር ለማግኘት ሲሞክር ደግሞ ልኡሉ እራሱ ብልህ ካልሆነ በስተቀር ተቀራራቢ የሆነ ሀሳብ ማግኘት ይቸግረዋል፡፡ ተቃራኒ የሆኑ ሀሳቦችን ማስታረቅ ይሳነዋል፡፡ እያንዳንዱ አማካሪ የየራሱን ፍላጎት ያቀርባል፡፡ ልኡሉ በምን መልኩ ሀሳቦቻቸውን መረዳትና ማረም እንዳለበት ማወቅ ይሳነዋል፡፡

ሰዎች ምግባራቸውን ያርቁ ዘንድ ካልተገደዱ ሁሌም ክፋትን ይቃጣሉ፡፡ በመሆኑም ድምዳሜያችን የሚሆነው የጥሩ ምክር ጥሩነት፣ ምክሩ ከማንም ይፍለቅ ከማን በልኡል ብልህነት ልክ ይወሰናል፡፡ በጥሩ ምክር የሚከሰት የልኡላን ብልጠት አይኖርም፡፡

## 23. ስለምን የጣሊያን ልኡላን ግዛታቸውን ተነጠቁ?

እስካሁን ያስቀመጥኳቸውን መርሆች የሚከተል አዲስ ልኡል በአጭር ጊዜ ውስጥ አስተማማኝ ግዛት መመስረትና ግዛቱን ለረዥም ጊዜ ጠብቆ ማቆየት ይችላል፡፡ የአዳዲስ ልኡላን

አካሄድ ከቀደምቶቻቸው በውርስ ስልጣንን ከተረከቡ መሪዎች በላቀ የሰውን አትኩሮት ይስባል፡፡ በተለይ አካሄዳቸው አስተውሎና ጀግንነት የተላበሰ ሆኖ ሲገኝ በደምና በዘር ግንድ ከሚገኝ ንግስ የላቀ ሰዎችን የመግዛትና አመኔታቸውን የማትረፍ ሀይል ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ካለፈው ይልቅ አሁን ላለው ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ አሁን ላይ እየተሰራ ያለው ነገር መልካም ነው ብለው ካሰቡ በዚሁ ረክተው ሌሎች ነገሮችን መቃኘት ያቆማሉ፡፡

በርግጥ ይህ ከሆነና ልኡሉ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ጉድለት ካልታየበት ዜጎች መሪያቸውን ለመጠበቅ የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም አዲሱ ልኡል እጥፍ ድል ይቀዳጃል፡፡ አዲስ ግዛት በመመስረትና የመሰረተውን ግዛት በጥሩ ህግጋት፣ አስተማማኝ የመከላከል ብቃት፣ ታማኝ አጋሮችና በጠንካራ አመራር በማዳበር መንታ ድል ይጎናፀፋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለልኡልነት ተወልዶ በብቃት ማነስ አማካኝነት ግዛቱን የሚነጠቅ መሪም እጥፍ ውርደትና ሀፍረት ይከናነባል፡፡

እስኪ እነዛ በኛ ዘመን ግዛታቸውን የተነጠቁትን የኔፕልሱን ንጉስ፣ የሚላኑን ሀገረ ገዥና የመሳሰሉትን የጣሊያን መሪዎች እንመልከት፡፡ አካሄዳቸውን ጠለቅ ብለን ስንመለከት ብዙዎቹ የሚጋሩት የመጀመሪያው ደካማ ጎን የራሳቸው የሆነ ጦር አለመገንባት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ በህዝብ ጥላቻ የተተፉ ናቸው፡፡ ህዝቡን ከጎናቸው ማሰለፍ የቻሉ የተወሰኑቱ ደግሞ የመሳፍንቶቻቸውን ተአማኒነት ማግኘት ሲሳናቸው እናያለን፡፡ ከነዚህ መንገዶች በአንዱ ያልተከላከሸ፣ በአደጋ ጊዜ ከጎኑ የሚቆም ሰራዊት ያለው ግዛት በቀላሉ ሊወድም

አይችልም፡፡ የሚቄዶንያው ፊሊጶስ በግሪኮች ሀይል ካጠቁት ሮማውያን ታላቅነት አንጻር ሲታይ ትንሽዬ ግዛት የሚያስተዳድር መሪ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ፊሊጶስ እንዴት የዜጋውን ፍላጎት ማሟላት እንዳለበትና በምን መልኩ የመሳፍንቱን ተገዢነት ማረጋገጥ እንደሚችል በሚገባ የተረዳ የጦር ሰው በመሆኑ ታላቁን የሮማውያንን ሀይል ለረዥም ጊዜ መከላከል ችሎ ነበር፡፡ መጨረሻ ላይ የተወሰኑ ግዛቶችን ቢነጠቅም መላ ግዛቱን ለረዥም ዘመን ጠብቆ ማቆየት ችሏል፡፡

ስለዚህ ለበርካታ አመታት በተደላደለ ዙፋን ላይ ተንፈላሰው የቆዩት የኛዎቹ ገዢዎች ለውድቀታቸው እድላቸውን መርገም የለባቸውም፡፡ ለስህተታቸው ተወቃሽ መሆን ያለበት የራሳቸው ዳተኝነት ነው፡፡ ምክንያቱም ወቅቱ የተረጋጋና ሰላማዊ በነበረ ጊዜ ለውጥ ይመጣል ብለው አስበው አያውቁም (በርግጥ ይህ የመላው የሰው ልጅ ደካማ ጎን ነው - ውቅያኖሱ ሰላማዊ ሲሆን ማእበል ይነሳል ብሎ የሚጠብቅ የለም)፡፡

በመሆኑም አደጋ በተከሰተ ቅጽበት የመሪዎቻችን የመጀመሪያ ሀሳብ መፈርጠጥ እንጂ አደጋውን መቋቋም አይደለም፡፡ ህዝቡ በወራሪዎቹ ጭቆና ተቆጥቶ በአመፅ ሲነሳሳ መልሶ ወደ ስልጣን ያወጣናል በሚል ተስፋ መሸገው ይጠብቃሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ተስፋ ውስጥ ሌሎች ጥንቃቄዎችን መርሳት ተገቢ አይደለም፡፡ ሰዎች የሚወድቁት የሚያነሳቸውን ሰው እርዳታ ጠብቀው ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ ላይከሰት ይችላል፡፡ ቢከሰትም አስተማማኝ መሰረት ላይ የተጣለ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አካሄድህ የፈሪና በራስህ ብቃት ላይ

ያልተመሰረተ ነው። ጠንካራና አስተማማኝ የመከላከል መንገድ በራስህ ድርጊትና ጀግንነት የሚመሰረት ብቻ ነው።

## 24. ዕድል በሰዎች ሕይወት ላይ ያላት የበላይነት እስከ ምን ድረስ ነው? ዕድልን መቃረን የምንችለው እንዴት ነው?

በርግጥ ብዙዎች የሰው ልጅ ሁናቴ በእግዚአብሄርና በዕጣ ፈንታው የሚወሰን በመሆኑ የሰው ልጅ አስተውሎ ሁኔቶችን የመለወጥ አቅም የለውም ብለው እንደሚያምኑ አውቃለሁ። በዚህ አመለካከታቸውም የተነሳ በነገራት ዙሪያ ማማጥ አስፈላጊ አይደለም - ለዕጣ ፈንታችን በጎ ፍቃድ መተው እንጂ ብለው መደምደማቸውም አይቀሬ ነው።

ይህ አይነቱ አመለካከት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ባለንበት ዘመን ሊንሰራፋ የቻለው እስካሁን ባስተናገድናቸውና አሁንም በየእለቱ እያስተናገድናቸው ባሉ ከሰው ልጅ አሳቤ በላይ የሆኑ ታላላቅ ለውጦች አማካኝነት ነው። አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ አይነት ተአምሮች ተከስተው ሳይ እኔ ራሴ በእንዲህ አይነቱ አመለካከት እዋጣለሁ። ይሁን እንጂ እድል ለድርጊቶቻችን ግሚሱን ወሳኝ ፈራጅ ብትሆንም የተቀረው ክፊል ግን ለራሳችን ቁጥጥር የተተወ ነው።

ለእኔ እድል እንደ ደራሽ ጎርፍ ነች። ጎርፍ ሲደነፋ ሜዳውን ያጥለቀልቃል፣ ዛፍና ቤቶችን ይመነግላል፣ አፈሩን

ከአንድ ቦታ ጠራርጎ ወስዶ ሌላ ቦታ ይከምራል፡፡ ማንም ደፋር ሊቋቋመው አይችልም፣ ባይሆን ይፈረጥጣል፡፡ ሁሉም ሰው ለጎርፉ ይማገዳል፡፡ በርግጥ ይህ አይነቱ የጎርፉ ልእለ ሀያል ተፈጥሮ እሙን ቢሆንም ይህ ማለት ግን ጎርፉ በርጋታና በዝግታ ሲፈስ ጥንቃቄ ማድረግ፣ መከላከያ ማበጀት፣ ግድብ መገንባት፣ በዚህም ጎርፉ ሲደነፋ አቅጣጫውን ማስቀየር፣ ቁጣውን መግራት፣ ጉዳቱን መቀነስ አንችልም ማለት አይደለም፡፡

የእድልም ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ እድል ጉልበቷን የምታሳየው የሚቋቋማት፣ በአግባቡ የዳበረ ሀይል ከሌለ ብቻ ነው፡፡ ሁሉንም ባሻችው መንገድ የምትማግደው ጉዞዋን የሚገድብ ግድብ ከሌለ ነው፡፡ የጣሊያንን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት ሀገሪቷ ያለምንም ግድብ፣ ያለምንም ከለላ ተጋልጣ የተቀመጠች ሀገር መሆኗን እንረዳለን፡፡ ጣሊያን እንደ ጀርመን፣ ስፔይንና ፈረንሳይ በሚገባ የተደራጀች ቢሆን ኖሮ ጎርፉ አሁን ያደረሰውን ያህል ታላቅ ለውጥ ባላስከተለ፣ ወይም ከነአካቴው ማጥ ውስጥ የመከተት ሀይል ያልነበረው ሊሆን በቻለ ነበር፡፡

አንዳንድ መሪዎች ዛሬ አብበው ይታዩና በባህሪም ሆነ በማንኛውም መንገድ ሳይቀየሩ በነጋታው ከስመው እናገኛቸዋለን፡፡ እንደኔ አመለካከት ይህ ሊሆን የቻለው ከዚህ ቀደም በስፋት እንዳወሳሁት በእድል ላይ ጥገኛ የሆኑ መሪዎች እድል ሲከዳቸው ለመውደቅ ስለሚገደዱ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጊዜው አመቺነት ፖሊሲዎቹን በአግባቡ ሲያስጠብቅ የቆየ መሪ ጊዜው ምቹ ባልሆነበት ወቅት ፖሊሲዎቹ ውድቅ ይሆናሉ፡፡ ሰዎች ግላዊ አላማቸውን፣ ታላቅነትንና ብልጽግናን እውን ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡ አንዳንዶች

በጥንቃቄ ሲጓዙ አንዳንዶች በስሜታዊነት፣ በችኩልነት ይራመዳሉ፡፡ አንዳንዱ ግትር ጠብ አጫሪነትን ሲጠቀም አንዳንዱ ስልታዊ ብልሀትን ይከተላል፡፡ አንዳንዶች ነገራትን በትዕግስት ሲከውኑ ሌሎች በተቃራኒው ይፈጽማሉ፡፡ ሆኖም ሁሉም ከመንገዳቸው መለያየት በተቃራኒ ከግባቸው ይደርሳሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሁለት ጥንቁቅ ሰዎችን ስንመለከት አንዱ አላማውን ሲያሳካ አንዱ ግን አላማውን ማሳካት ይሳነዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሁለት ሰዎች በተለያየ መንገድ ተጉዘው አንዱ ጥንቁቅ ሌላኛው ችኩል ሆነውም በእኩል ደረጃ ሲሳካላቸው እንመለከታለን፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው የተጓዙበት መንገድ ወቅትና ሁኔታውን ያገናዘበ በመሆኑ ወይም ባለመሆኑ የተነሳ ነው፡፡ አስቀድሜ እንደገለጽኩት በተለያየ መንገድ የተጓዙ ሁለት ሰዎች ከተመሳሳይ ግብ ሊደርሱ ሲችሉ በተመሳሳይ መንገድ የተጓዙ ሁለት ሰዎች አንዱ የፈለገውን ሲያገኝ ሌላው የፈለገውን ሊያጣ ይችላል፡፡ ይህ እውነታ ብልጽግናና ታላቅነት ለምን በፍጥነት በርተው በፍጥነት እንደሚጠፉ ያመላክታል፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው በትዕግስትና በጥንቃቄ የሚጓዝ ከሆነና ጊዜውና ሁኔታዎች ይህን አካሄድ የሚፈልጉ ከሆነ ይበለጽጋል፡፡ ሆኖም ጊዜና ሁኔታዎች ሲቀየሩ መንገዱን ካላስተካከለ ለውድቀት ይዳረጋል፡፡

በርግጥ ፖሊሲዎቹን በዚህ መንገድ የመቅረጽ ብቃት ያለው ብልህ መሪ ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱ አንድም ሰዎች ከተፈጥሯቸው ውጪ መንቀሳቀስ ስለሚከብዳቸው፣ አሊያም አንድ መንገድ በመጠቀም ሁሌም ስኬትን መቀናጀት የለመደ ሰው እራሱን ለለውጥ ማዘጋጀት ስለሚያዳግተው ነው፡፡ ስለዚህ ጥንቁቅ የሆነ ሰው ችኩልነት በሚያስፈልግበት ጊዜ

ሀላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት የማይመጥን ሆኖ ይገኛል፡፡ እናም ለውድቀት ይዳረጋል፡፡ ሆኖም ባህሪውን ከጊዜውና ከሁኔታዎች ጋር መቀያየር ከቻለ እድል አይለዋወጥም፡፡

ጳጳስ ጁሊየስ ሁለተኛ በሁሉም ነገር ችኩል ነው፡፡ ሆኖም ጊዜና ሁኔታዎች ባህሪውን የሚደግፉ ሆነው ስለሚገኙ ሁሌም ስኬታማ ነው፡፡ ወደ ቦሎኛ ያደረገውን የመጀመሪያ ዘመቻ እንደምሳሌ እንውሰድ፡፡ በወቅቱ ቬኒዣውያንም ሆኑ ስፔኖች በእቅዱ አላመኑበትም፡፡ የሰራዊት ድጋፍ ከምታቀርብለት ፈረንሳይ ጋርም ድርድሩን አልጨረሰም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን አስገራሚ በሆነ አስገዳጅነትና ጥድፊያ ዘመቻውን በግሉ ከፈተ፡፡ ድንገተኛ የሆነ ወረራው ቬኒዣውያንንና ስፔኖቹን አደናግሮ ከእርምጃቸው ገታቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፈረንሳዩ ንጉስ ከጳጳሱ ጎን ተሰለፈ፡፡ ንጉሱ ጁሊየስ ወደ ተግባር በመግባቱና ቬኒዣውያንን ለመቆጣጠር ድጋፉ አስፈላጊ በመሆኑ ቅራኔ ላለመፍጠር ወታደሮቹን ላከለት፡፡ በዚህ ችኩል አካሄድ ጳጳስ ጁሊየስ ማንኛውም አስተዋይ ጳጳስ ሊያሳካ የማይችለውን ትልም እውን አደረገ፡፡ ጳጳሱ ሌሎች ያደርጉት እንደነበረው እቅዶቹና ድርድሮቹ ሁሉ እስኪጠናቀቁ ከሮም ሳይወጣ ቢጠብቅ ኖሮ ግቡን ማሳካት ባልቻለ ነበር፡፡ ምክንያቱም የፈረንሳዩ ንጉስ እልፍ አእላፍ ሰበብ አስባብ እየደረደረ ከጉዞው ሲገታው ሌሎቹ በበኩላቸው ተቆጥረው በማያልቁ ማስፈራሪያዎች ያደናቅፉት ነበር፡፡ ሌሎች እርምጃዎቹን መጥቀስ አስፈላጊ ባይሆንም ሁሉም በእንዲህ አይነት አካሄድ ስኬታማ የሆኑ ነበሩ፡፡ በጥድፊያ የተሞላው የጵጵስና ህይወቱ ተቃራኒውን ጽዋ እንዲጎነጭ አላደረገውም፡፡ በጥንቃቄና በርጋታ ይጓዝ ዘንድ የሚያስገድድ

ጊዜ ቢመጣ ጳጳሱ ለውድቀት ይዳረግ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከባህሩው ውጪ ተጉዞ አያውቅም፡፡

ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ስናስቀምጠው፣ እድል ተለዋዋጭ ሆና የሰው ልጅ በአቋሙ ግትር በመሆኑ ሰዎች የሚበለጽጉት እድልና መርሀቸው መገናኘት እስከቻለ ድረስ ነው፡፡ በሁለቱ መካከል መጣረዝ ከተከሰተ ግን ለመውደቅ ይገደዳሉ፡፡

እንደኔ አመለካከት እድልን በተመለከተ ጥንቁቅ ከመሆን ይልቅ ችኩል መሆን የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም እድል እንደ ሴት ነች፡፡ ሰጥ ለጥ ብላ ትገዛ ዘንድ ማሬሌልና መጫን ያስፈልጋል፡፡ የታዘብናቸው ልምዶች እንደሚጠቁሙት እድል ከቀዝቃዞቹ ይልቅ ለእንዲህ አይነቶቹ ወንዶች በጸጥታ ትገዛለች፡፡ ደግሞም ሴት እንደመሆኗ ሁሌም ወጣቶችን ትመርጣለች፡፡ ምክንያቱም ወጣቶች በጥቂቱ ጥንቁቅ በአመዛኙ ደመ-ሞቃት ናቸው፣ በታላቅ ወኔ ሊያዝዟት ይችላሉ፡፡

## 25. ጣሊያንን ከአረመኔዎች ነጻ የማውጣት ተማጽኖ

እስካሁን ያነሳኋቸውን አንኳር ነጥቦች በጥልቀት ከቃኘሁ በኋላ ሀገራችንን ጣልያንን በተመለከተ አንድ ጥያቄ አነሳለሁ - ጊዜው አዲሱን ልኡል በአክብሮት ለማስተናገድ ዝግጁ ነው? ሀገራችን ጣሊያን የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አዲስ የሆነ ስርአት

ዘርግቶ፣ ለራሱ ከበሬታን፣ ለመላው ሀገሪቱና ለእያንዳንዱ ዜጋ ብልጽግና ሊያጎናጽፍ ለሚችል አስተዋይና ጠንካራ መሪ ሁኔቶች አመቺ ናቸው?

እንደኔ እምነት ከሆነ እልፍ አእላፍ የሆኑ ነገራት አዲሱን ልሉል ለመደገፍ አሲሬዋል፡፡ አሁን ካለንበት ጊዜ የተሻለ ምቹ አጋጣሚ ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡ ከዚህ ቀደም እንዳስቀመጥኩት እስራኤል ሙሴን የመሰለ ታላቅ መሪ ታገኝ ዘንድ በግብጾች ባርነት መሰቃየት ነበረባት፡፡ ለሳይረስ ታላቅነት ፐርሽያውያን በሜዲያዎች የጭቆና በትር መንገላታት ነበረባቸው፡፡ የቴሲየስ ልእለ ሀያልነት ገንኖ ይወጣ ዘንድ አቴናውያን ተበታትነውና ተዳክመው መገኘት ነበረባቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የጣሊያናዊነትን የመንፈስ እዳ ፈልገን እናገኝ ዘንድ ሀገራችን ዛሬ ካለችበት የውድቀት ጽንፍ ተገኝታለች፡፡ ከሂብሩዎች በባሰ የባርነት ማጥ ተማግዳ፣ ከፐርሺያውያን በከፋ ተጨቁና፣ ከአቴናውያን በባሰ ተበታትና በጠላት ተወርራ፣ መሪ የለሽነት፣ ህግ አልባነት ሰፍኖ ሀገራችን ተሰብራ፣ ተመዝብራ፣ ጥልቅ በሆነ ግራ መጋባት ተዘፍቃ የመከራ ቀምበሮቿን እንደተሸከመች ተቀምጣለች፡፡

ምንም እንኳ ከቅርብ ጊዜ በፊት አምላክ ሀገራችንን ነጻ የሚያወጣ ሀያል ልኮልን ትናንሽዬ የተስፋ ብልጭታዎችን መመልከት ጀምረን የነበረ ቢሆንም ትልሙን ከማሳካት ጠርዝ ሲደርስ በእድል በደል ሲከዳ ለማየት ተገደናል፡፡ እናም አሁን ጣሊያናችን እስትንፋስ አልባ ሆና ከቁስሏ የሚያድናትና ስብራቷን የሚጠግንላት ሰው በመጠበቅ ላይ ትገኛለች፡፡ የሎምበርዲን፣ የቱስካኒን፣ የመላውን ግዛት ምዝበራ በቃ

የሚልላት፣ እስከ ዛሬ ድረስ ያለማቋረጥ እየመረቀዘ እየመገለ ያለውን ቁስሏን የሚያብስላት አዳኝ በተስፋ እየጠበቀች ትገኛለች፡፡ ሀገራችን ከነዛ አረመኔዎች ጭቆናና ሰቆቃ የሚታደጋት ፍለጋ እንዴት አምላኳን እንደምትማጸን ተመልከት፡፡ ከመካከላችን አንዱ ከፍ አድርጎ ሊያውለበልብላት ከቻለ ሀገራችን ሰንደቋን ለመከተል ምን ያህል እንዳቆበቆበች ተመልከት፡፡

ሆኖም አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ የሀገሪቱን ተስፋ በቀናኢ ዕጣ ፈንታና ጀግንነት፣ በእግዚአብሄርና በቤተክርስቲያኗ ፍቃድ ከዳበረው ግርማዊ መንበርዎ በቀር እውን ሊያደርግላት የሚችል ሀይል የለም፡፡ በርግጥ ይህ ሲሆን ግርማዊ መንበርዎ ሀገራችን ከተዘፈቀችበት ማጥ ይታደጋታል፡፡ በደምሳሳው ሲታይ አዳጋች ሊመስል ቢችልም እንደ ተምሳሌት ያነሳኳቸውን በኛም ሀገር መሪዎች ህይወትና ድርጊት አርአያ ካደረጉ ልዩና ልእለ ሀያል ይቻላል፡፡ እነ ሙሴ፣ ሳይራስና ቴሲየስ ልዩና ልእለ ሀያል መስለው ቢታዩም እንደ ሁላችን ሰዎች ናቸው፡፡ እንዳውም እነሱ አሁን ከቀረበው የተሻለ ምቹ አጋጣሚ አልቀረበላቸውም፡፡ እግዚአብሄር ትልማቸው ከገደብ ያለፈም የወረደም አልነበረም፡፡ እንዳውም የእኛ አጋር ከሆነው በተለየ የነርሱ ወዳጅ አይደለም፡፡ እንዳውም እኛን በተመለከተ ይበልጥ ይሁንታ አለ፡፡ ምክንያቱም በግዳጅ የመጣ ጦርነት ፍትሀዊ ነው፡፡ ተስፋ በጦር ብቻ ሲሆን በርግጥ ያ ጦር ቅዱስ ነው፡፡ በህዝባችን ልብ ውስጥ ታላቅ ተነሳሽነት አለ፡፡ ይህ ባለበት መውደቅ አዳጋች ነው፡፡

ከግርማዊው መንበርዎ የሚጠበቀው አስቀድመን ያወሳናቸውን ተምሳሌቶች መከተል ብቻ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ

ከእግዚአብሄር የተቸሩ ድምጽ አልባ ተአምሮችንም እንመልከት፡፡ ውቅያኖሱ ተከፍሏል፣ ደመናዎቹ መንገዱን እየጠቆሙ ነው፣ ውሀ ከአለቱ እየፈለቀ ማናን እያጥለቀለቃት ነው፡፡ ነገሮች ሁሉ ስለዙፋንዎ ታላቅነት እያሴሩ ነው፡፡ የተቀረው ለግርማዊው መንበርዎ የተተወ ድርሻ ነው፡፡ እግዚአብሄር ሁሉን በራሱ ማድረግ አይሻም፡፡ የራሳችንን ድርሻ እራሳችን መወጣት ይኖርብናል፡፡

እስካሁን ያነሳኋቸው ጣሊያናውያን ተስፋችንን ማሳካት አለመቻላቸው እንደ ተአምር ሊታይ አይገባም፡፡ እነርሱ እውን ያላደረጉትን የእርስዎ መንበር ያደርገዋል፡፡

በርግጥ እነዛን ሁሉ የሀገራችንን አብዮቶችና ወታደራዊ ዘመቻዎች ስንመለከት ጀግንነታችን ተሰልቦ የተወሰደ ሊመስል ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ሊሆን የቻለው ያረጀው ወታደራዊ ስርአታችን መጥፎ በመሆኑና በምን መልኩ አዲስ ወታደራዊ ስርአት መገንባት እንዳለብን የሚያውቅ ሰው ባለመኖሩ ነው፡፡ አንድ መሪ ታላቅ ክበሬታ ማትረፍ የሚችለው ደግሞ በሚመሰርታቸው አዳዲስ ህግጋቶችና ተቋማት ነው፡፡ እነዚህ መሰረቶች በአግባቡ ተጥለው የታላቅነትን ፍንጭ ሲዘሩ መሪው በህዝቡ ዘንድ ውዳሴና ግርማዊነትን ይቀናጃል፡፡ በርግጥ በአሁኗ ጣሊያን ሁናቴ ውስጥ አስፈላጊው ነገር ነባሩን ስርአት ማደስና መጠገን አይደለም፡፡

መሪዎቻችን ጀግነው ሲገኙ ዜጎቻችን ለጀግንነት የሚያህላቸው አይኖርም፡፡ የጣሊያናውያንን የፍልሚያ ብቃት ያጤነ ማንኛውም ሰው ጥንካሬያችንን፣ ክህሎታችንና ስልታችንን

ሊከድ አይችልም፡፡ ወደ ወታደራዊ ተቋሞቻችን ስንመለከት ግን የሚነጻጸሩ አይደሉም፡፡ ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው በመሪዎቻችን ደካማነት የተነሳ ነው፡፡ ብቁ የሆኑት ተቀባይነት አያገኙም፡፡ ሁሉም ሰው እራሱን ብቁ እንደሆነ አድርጎ ያስባል፡፡ ሆኖም እስካሁን ድረስ በጀግንነትም ይሁን በቀናኢ ዕጣ ሁሉንም የመጠቅለል ብቃት ያለው ሰው አላየንም፡፡ በዚህ የተነሳ ይህን ሁሉ ጊዜ፣ ባለፉት ሀያ አመታት ከመላው ጣሊያን የተውጣጣ ጦር ሲመሰረት የሚያስመዘግበው ውጤት ሁሉ አስከፊ ነው፡፡ የታሮ ጦርነት፣ ከዚያም አሌሳንድሪያ፣ ካፑዋ፣ ጄኖዋ፣ ቫይላ፣ ቦሎኛና ሜስትሬ እነዚህ ሁሉ ጦርነቶች ይህንን ሀቅ የሚመሰክሩ ናቸው፡፡

ስለዚህ ግርማዊ ዙፋንዎ ሀገራቸውን ከውድቀት የታደጉትን ብልህ መሪዎች ተሞክሮ ለመድገም ከፈለገ ከሁሉ ነገር ቅድሚያ ከራስ ከራስ ዜጋ የተውጣጣ ጦር መመስረት ነው፡፡ ምክንያቱም ከራስ ጦር የተሻለ ታማኝ፣ እውነተኛና ጠንካራ ሰራዊት ሊኖር አይችልም፡፡ ይህ አይነቱ ሰራዊት በራሱ ልኡል ሲመራና ክብሩ ተጠብቆለት ሲዋጋ አንድነቱን መቋቋም የሚችል ተቀናቃኝ አይኖረውም፡፡ ውጫዊ ወራሪዎቻችን ለመመከት እንዲህ አይነቱን ጦር መገንባት የግድ ነው፡፡ ምንም እንኳ የስፔይንና የስዊዝ እግረኛ ሰራዊት የማይገፋት ሊመስል ቢችልም ከነሱ የተለየ ሶስተኛ ስልት ይዞ ለሚከሰት ሀይል ሊንበረከክ የሚችል ደካማ ጎን አላቸው፡፡ የስፔይን ጦር ፈረሰኛ ሀይልን መቋቋም አይችልም፡፡ ስዊዞች ደግሞ ከራሳቸው ባልተናነሰ ቆራጥነት የሚጋፈጣቸውን እግረኛ የሚሸሹበት ምክንያት አላቸው፡፡ ከዚህ ቀደም የታዩ ተሞክሮዎችን ስንመረኮዝ ስፔኖች የፈረንሳይን


ፈረሰኛ መቋቋም አይችሉም፡፡ ስዊዞች ደግሞ ለስፔይን እግረኛ ሰራዊት ይረታሉ፡፡ ለሁለተኛው ድምዳሜ ፍጹም የሆነ ማረጋገጫ ማቅረብ ባይቻልም በራቬና ላይ የተካሄደው ውጊያ የሚጠቁመን የተወሰነ ሀቅ አለ፡፡ ራቬና ላይ ስፔኖች ከስዊዝ ተመሳሳይ አሰላለፍን ከሚከተለው የጀርመን ባታሊዮን ጋር ተጋጥመው ነበር፡፡ በፍልሚያው ላይ ስፔኖቹ በፈጣን የከቦ ማጥቃት ዘመቻቸው የጀርመንን ባታሊዮን አስጨንቀው አቅም አሳጥተውት ነበር፡፡ የጀርመን ፈረሰኛ ጦር መፈናፈኛ ባያሳጣቸው ኖሮ ስፔኖቹ ሙሉ ለሙሉ የጀርመንን እግረኛ ባታሊዮን መደምሰስ በቻሉ ነበር፡፡

የስዊዝንና የስፔይንን እግረኛ ሰራዊት ደካማ ጎን በማጤን ማንኛውንም ፈረሰኛ የሚቋቋም በእግረኛ የማይገፋ አዲስ ጦር መገንባት ይቻላል፡፡ አዲስ ሰራዊት በመመስረትና አዲስ አሰላለፍ ተግባራዊ በማድረግ አዲስ የጦር ስልት እውን ማድረግ ይቻላል፡፡ በርግጥ ለአንድ አዲስ ልኡል ክብርንና ታላቅነትን የሚያላብሱት እንደዚህ ያሉት አዳዲስ መሰረቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ሀገራችን ከዚህ ሁሉ መከራ በኋላ የሚታደጋት ታገኝ ዘንድ ይህ ምቹ አጋጣሚ መባከን የለበትም፡፡ እናም በውጭ ሀይሎች የጭቆና ቀምበር እየማቀቀች ያለችው ጣሊያን ነጻ የሚያወጣትን መሪዋን በምን አይነት የበቀል ጥም፣ የማያወላውል ቆራጥ ተአማኒነት፣ በምን አይነት መሰጠትና እምባ እንደምትቀበለው ለመግለጽ የሚበቁ ቃላት የሉኝም፡፡ በነጻ አውጪያችን ላይ በሩን የሚዘጋ ማነው? እሱን ለመገዛት አሻፈረኝ የሚል ማነው? ከቶውኑ በፊቱ ላይ የሚቆም ተቀናቃኝ

ማነው? የትኛው ጣሊያናዊ ነው ታማኝነቱን ከማሳየት የሚወላውለው? ይህ የአረመኔዎች አምባገነንነት ሁላችንን አንገሸግሿል።

ይህ ተልእኮ የግርማዊ መንበርዎ ሀላፊነት ሆኖ በፍትሀዊ ትልማችን ባለን ወኔና ተስፋ በርስዎ መሪነት ሀገራችን ትክበር። በዙፋንዎ ግርማዊነት የቅዱሳኖቻችን ትንቢት እውን ይሁን!!!



"በዚህ መጽሐፍ ሥራውንና ሰብዕናውን ትቃኙ ዘንድ ካቀረብንላችሁ ሰው የላቀ በሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ አወዛጋቢ ጸሐፊ መኖሩን እንጠራጠራለን።"

ማኮሌይ

ይህ መጽሐፍ በብልጠት በተሞላ ሥነ-ልቦናዊ አንደምታው፣ የወደፊቱን በመተንበይ ብቃቱ፣ ጥልቀት ባለው አፃፃፉ፣ ከዘመን ዘመን አንባቢያንን የማስደመም ኃይሉ አማካኝነት ጊዜ አይሽሬ ዘመን ተሻጋሪ ሥራ ለመሆን በቅቷል።

"ልኡሉ" የተሰኘው ይህ መጽሐፍ ብቻውን ከተገቢው በላይ የማኪያቬሊን ምጡቅነት ያንፀባርቃል የሚለው ብዙሃኑን የሚያስማማ አስተያየት ነው። በርግጥም ይህ መጽሐፍ መሠረታዊ የፖለቲካ አመለካከቶቹን አጠቃሎ የያዘ ድንቅ የፈጠራ ውጤቱ እንደመሆኑ የማኪያቬሊ ምንነት ቢሰፈርበት ፍርደ ገምድል አያሰኝም። ግልፅነቱና የድፍረቱ አስገራሚነት፣ ጥበበኝነቱ፣ ቀልብን የሚያሸፍት ነገሮችን የመተንተን ብቃቱ፣ በማንኛውም መስዋዕትነት ለሚመጣ ውጤታማነት የሚሰጠው አድናቆት፣ ሁለ-ገብነቱና ዕውቀቱ... በርግጥ [illegible] የሰ [illegible] ሰውሎ [illegible] ሊሰጠው የሚገባ ነው።

ሳተን ሱሬ (ጂ.ቢ.)

ዋጋ [illegible] .00